# አርነታችን የሆነው የእግዚአብሔር ጥሪ

## ክፍል አንድ

በጃኪይ ኦስክ

## ዘፀአት 1-12

ትምህርት 1፡ አዲሱ የግብፅ ንጉስ - መልካም ልጅ ነበር

ትምህርት 2፡ እኔ እኔ ነኝ - እግዚአብሔር ጠራው

ትምህርት 3፡ አወጣችኋለሁ - እኔ ጌታ ነኝ

ትምህርት 4፡ ልቡን አደነደነው - እጅህን ዘርጋ

ትምህርት 5፡ መቅሰፍት ምድሪቱን መታ - ሕዝቤን ልቀቅ

ትምህርት 6፡ ይህን ቀን አስታውስ - ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው

**“……… ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።……….”**

**መቅድም**

ቀሪውን ህይወታችሁን መልክ የሚያስይዘውን የአስገራሚውን ጉዞ ግስጋሴ ቀጥላችኋል። ይህ ጉዟችሁ ልዩ እና ስለመፅሐፍ ቅዱስ ለመረዳት ያላችሁን ጉጉት በከፊል ይወስነዋል ። ይህን ጥናት ለማጥናት ያላችሁ መሰጠትም እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ ለልባችሁ በመናገር ህይወችሁን የሚያበለጽግበትን ተስፋ የያዘ ነው።

ይህን ጥናት ስታጠኑ ለጥናታችሁ የሚረዷችሁን የሚከተሉትን የመርጃ መሳሪያዎች እንድትይዙ እናበረታታችኋለን።

1. *አርነታችን የእግዚአብሄር ጥሪ* የሚለውን የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል ጥራዝ
2. አዲሱን መደበኛ ትርጉም መፅሀፍ ቅዱስ ፡ አዲስ መፅሀፍ ቅዱስ የምትገዙ ከሆነ የሚከተሉትን ነገሮች ቢይዝ መልካም ነው።
   ሀ. ማጣቀሻ ጥቅሶች በምእራፎቹ አካፋይ መካከል ወደታች  የተፃፉበት
   ለ. በጀርባው የቃል ማውጫ ያለው
   ሐ. መሰረታዊ የሆኑ ካርታዎችን የያዘ
3. እስኪብርቶ ወይንም እርሳስ
4. በፎቶ መጠን የተቆራረጡ ካርዶች

በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተዘረዘሩትን ሶስቱን ነገሮች ካሟላችሁ ጥናታችሁን በአግባቡ እና በተሳካ ሁኔታ ማጥናት ትችላላችሁ።ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስን የምታነቡት ለመጀመሪያ ግዜ ከሆነ በቅድሚያ ማጥናት ያለባችሁ ክፍል “*መፅሐፍን ቅዱስ መመርመር*” የሚለውን የጥናት ክፍል  ነው። ይህ የጥናት ክፍል ብቁ የመፅሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የሚያደርጋችሁ እና መፅሐፍ ቅዱስን በብቃት ማጥናት በሚያስችላችሁ መንገድ የተዘጋጁ መፅሐፍ ቅዱስን መመርመር የሚያስችሏችሁን  መሳሪያዎችን የያዘ ነው። በተጨማሪም ደግሞ ይህን ጥናት

አርነታቸ የሆነው የእግዚአብሄር ጥሪ የሚለውን ቀጣዩን የጥናት ክፍል ለማጥናት ስለሚረዳ እንድታጠኑት እንመክራለን፡፡

መፅሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ማድረግ እንዳይከብዳችሁ፤ ምክንያቱም የእናንተ መፅሐፍ ስለሆነ ነው፡፡ አስምሩበት፣ በምልክት ማድረጊያ ማርከራችሁ ምልክት አድርጉበት፣አክብቡበት፣ የራሳችሁ መፅሐፍ አድርጉት፡፡ ማስታወሻ ወይንም ፣ታብሌት (ሞባይላችሁን) ጥያቄዎችን ፣ ሀሳቦችን ፣ ትምህርቱን በአጠቃላይ ለመከታተል መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

እነዚህ ማጥኛዎች የተዘጋጁት መፅሀፍ ቅዱስን በግላችሁ ማጥናት እድትችሉ ተደርገው ነው፡፡ ስለዚህ ያለምንንም ችግር ወይንም በመጠኑ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ልታጠኗቸው ትችላላችሁ ማለት ነው፡፡በተጨማሪም አዳዲስ መረጃዎችን ልታገኙባቸው፣ አዳዲስ መረዳቶችን እንዲሁም አስቸጋሪ የሆኑ መልስ የሚሹ ጥያቄዎችን ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ጥናት ስታጠኑ እንደተለመደው ጓደኞቻችሁን ወደዚህ ጥናት መጋበዝን እንዳትዘነጉ፡፡

በጥናታችሁ ደስታን እንድታገኙ እንመኛለን፡፡እግዚአብሄር በቃሉ ሲናገራችሁ ተቀባይ ልብ ይኖራችሁ ዘንድም እንዲሁ እንመኛለን፡፡ እነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እግዚአብሄር በልጁ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ የገለጠውን ታላቅ ፍቅር እንድትረዱ ያድርጓችሁ፡፡

# ትምህርት አንድ

# መልካም የሆነ ህፃን ነበር

## ዘፀአት 1-2 - አዲሱ የግብፅ ንጉስ

---

**የክፍል 1 ምልከታ**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1፡ ዘፀአት 1-2

- አዲሱ ንጉስ
- ሲፖራ እና ፉሐ
- በቅርጫት ውስጥ ተገኘ
- በባእድ ምድር እንግዳ
- እግዚአብሄር አስታወሰ

## መግቢያ

የእግዚአብሄር ህዝቦች በግብፅ ረክተው እየኖሩ ነው፡፡ በቁጥር እየበዙ እና ፍሬያማ ሆነዋል፡፡ ጥንካሬያቸው እና የቁጥራቸው መብዛት ዮሴፍን ለማያውቀው ለአዲሱ የግብፅ ንጉስ ታላቅ ችግር ሆኖበታል፡፡ በፈርኦን ምድር ተደላድላው የተቀመጡትን እነዚህን ህዝቦች እግዚአብሄር ይህንን ንጉስ ተጠቅሞ ከምቾች ክልላቸው እንዴት እንዳወጣቸው ተመልከቱ፡፡

እግዚአብሄር የፈለገው እርነሱን ከተደላደሉበት ስፍራ ማነቃነቅ ብቻ ሳይሆን ወደፊት እነሱን ከግብፅ የባርነት ኑሮ ነፃ ለሚያወጣበት ቀን መሪ ማስነሳትም ጭምር ነው፡፡እግዚአብሄር ቅዱስ ለሆነው ዓላማው ያዘጋጀውን ህዝብ ለማንቃት እንዴት የተለያዩ ዘዴዎችን አንደተጠቀመ ተመልከቱ፡፡ ጊዜው ለአብርሐም የገባውን የተስፋ ቃል የሚፈፅምበት ጊዜ ነው፡፡

ለእኛም እናትየው ልጇ መልካም እና ያማረ አንደሆነ እንዳየችው የሚተርከው ታሪክ በቀላሉ ነው የተነገረን፡፡ ልጃቸው አንዳች የተለየ ታላቅ ነገር እንዳለበት የተረዱ ቤተሰቦች ላሉት ልጅ ይህ ሁኔታ ምን ማለት እንደሆነ ተመልከቱ፡፡ ይህ ሁላችንንም የሚገዳደር ሁኔታ ነው፡፡ዙሪያችንን ስንመለከት በህይወታችን ውስጥ ታላቅ አላማ ያለባቸውን ሰዎች ተመልክተን ይሆን ፡፡

## ክፍል 1

***መግቢያ*** ፡ ብዙ ዘመን አልፏል ። የያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች በግብፅ በሰላም እየኖሩ ነው። ወደ ግብፅ ያመጣቸው ዮሴፍ ሊሞት አካባቢ ለወንድሞቹ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር።እግዚአብሄር ለአብርሐም፣ ለይስሀቅ፣ ለያዕቆብ ተስፋ ወደገባላቸው ምድር ሲሄዱ አጥንቱን ይዘው እንዲሄዱ አደራ ብሏቸዋል (ዘፍጥረት 50፡24-25)።

እስቲ ለጥቂት ግዜ ወደኋላ ተመልሰን ይህንን ታሪክ እንመልከት።እግዚአብሄር ለእስራኤል ምን አይነት ምድር እንደሰጣቸው እናስታውስ።እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው የእረፍት ምድር ግብፅ አይደለችም። ግብፅን ያዘጋጀላቸው ክፉው የረሀብ ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ይህ ቤተሰብ እንደመጠለያ እንዲቆይባት ነው።የተስፋዋ ምድር ከነአን ነች (ዘፍጥረት 17፡8)። ነገር ግን እነርሱ ግብፅን ለከብቶቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው ምቹ ሆና አግኝተዋታል። ስለዚህም ወደመጡበት ሀገር እንዲመለሱ የሚያደርጋቸው ምንም ምክንያት የለም። ነገር ግን አሁን ግብፅን ለመልቀቅ ግዜው ነው።ይህንን በግብፅ ተመቻችቶ የተቀመጠ ህዝብ እግዚአብሄር ወደተስፋይቱ ምድር እንዴት ነው የሚመልሰው?

ዘፀአት ይህንን ታሪክ ግልፅ በማድረግ ይጀምራል።ይህ አዲስ ቀን ነው።የረሀቡን ዘመን ለማሳለፍ ከከነአን ወደግብፅ የመጡት ቤተሰቦች በሙሉ ሞተዋል።እግዚአብሄርም ለአብርሐም ተስፋ እንደሰጠው የአብርሐምን ዘር አብዝቷል። እናም አሁን ዮሴፍን የማያውቅ አዲስ ንጉስ በግብፅ ነግሷል ታሪኩ እዚህ ጋር ይጀምራል።

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 1፡1-14 ያለውን ክፍል አንብቡ

***መልመጃ፡***

1. ስለዚህ ንጉስ የምናውቀው ነገር ምንድነው (ቁጥር 8)?__________________________

2. በቁጥር 9 ላይ ትኩረቱ ምን ላይ ነበር ? ________________________________

3. ለምንድነው የእስራኤል ሕዝብ የንጉሱን ቀልብ የሳበው (ቁጥር 10)______________

________________________________________________________________

4. ግብፃውያን ከእስራኤላውያን ጋር በሹክሹክታ እየተነጋገሩ ነው (ቁጥር 10)፡፡ይህ አዲስ የግብፅ ፈርኦን ምን ሊያደርግ ወስኗል (ቁጥር 11)?

   ሀ. ________________________________________

   ለ.________________________________________

   ሐ.________________________________________

5. ፈርኦን ህዝቡን በማስጨነቅ ከተቆጣጠረው እንዳይበዛ ማድረግ እንደሚችል አስቧል፡፡ነገር ግን ነሮች እንደታሰበው አልሆኑም፡፡ነገር ግን በተቃራኒው ቁጥር 12 ምን ሆነ ይለናል?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

6. በውጤቱም ግብፃውያን እስራኤላውያንን አስጨነቋቸው፡፡የግብፃውያን ክፉ እና ጨቋኝ ባህሪ ይበልጥ ርህራሄ የለሽነቱ የባሰ ሆነ፡፡ በቁጥር 13 እና 14 ላይ አስጨነቋቸው የሚለው ቃል ሁለት ግዜ ተፅፏል፡፡ታዲያ ፈርኦን ምን እንዲሰሩ አደረጋቸው (ቁጥር 14) ?

   ሀ.________________________________________

   ለ.________________________________________

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 1፡15-22 አንብቡ፡፡

1. አስመራሪ የሆነውን ከባድ ስራ እንዲሁም ጭከና የተሞለበት ግዞት ብቻ አልነበረም ፈርኦን በእስራኤላውያን ላይ እዲደረግባቸው የወሰነው፡፡ቁጥር 15-22 ተመልከቱ፡፡ቀጥሎ ምን አደረገ?

   ሀ. ሁለቱን የዕብራውያን አዋላጆችን ስም ጥቀሱ____________እና____________

   ለ. ንጉሱ ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው ( ቁጥር 16)?______________________

   ሐ. ስለእነዚህ አዋላጆች የተነገረን ነገር ምንድነው(ቁጥር 17) ?______________

   ________________________________________________________

   መ. ፈርኦን እነዚህን አዋላጆች ወደእርሱ አስጠርቶ ስለአለመታዘዛቸው ሲጠይቃቸው የሰጡት ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 19)__________________________

__________________________________________________________________

2. ከፈርኦን ይልቅ እግዚአብሄርን በመፍራታቸው እግዚአብሄር ያደረጋላቸው ምን ነበር? (ቁጥር 20-21)እግዚአብሄር ምን እንዲፈጠር አደረገ?

   ሀ.____________________________________________________________

   ለ.____________________________________________________________

   ሐ.____________________________________________________________

3. ነገር ግን ፈርኦን ይህን ነገር እንዲቀጥል አደረገ፡፡ለህዝቡ ሁሉ ያለው ሀሳብ ምን ነበር (ቁጥር 22)?____________________________________________________

   ________________________________________________________________

## ክፍል 2

**ገለፃ ፡** እነዚህ በዘፀአት ቁጥር 1 ላይ ያሉት ጥቂት ቁጥሮች የግብፅንም የእስራኤልንም ታሪክ ለሚለውጠው ተውኔት መድረክ የሚያዘጋጁ ቁጥሮች ናቸው፡፡ሲፖራ እና ፉሐ በፈርኦን ፊት ቆመው “አይሆንም” አሉ፡፡እግዚአብሄርን መፍራታቸው በፈርኦን ዘንድ እንደ አለመታዘዝ ተቆጠረባቸው፡፡ይህ ቀላል ነገር አይደለም፡፡፡እስቲ ይህ ውሳኔ አንገታችሁን ገመድ ውስጥ የሚያስገባ ቢሆን እናንተ ምን ልትወስኑ እንደምትችሉ አስቡ ፡፡እነዚህ ሴቶች ታላቅ መንፈሳዊ ሴቶች ናቸው፡፡ስራቸው ልጆች እንዲወለዱ ማድረግ እንጂ እንዲሞቱ ማድረግ አይደለም፡፡እስራኤላውያንን በመክዳት ከንጉሱ የጭካኔ ተግባር ጋር አልተባበሩም ነበር፡፡

**ትግበራ፡** የሲፖራ እና የፉሐ ንጉሱን መክዳት አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጉዳይ ጥያቄ ሊሆንብን ይችላል፡፡ እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት ልጆቹ እንደሚወለዱ ንጉሱ እንዲያምናቸው አድርገውታል፡፡

1. መቼ ነው እውነቱን እንድንደብቅ የሚፈቀድልን ? እንደዚህ አይነት ሁኔታስ አጋጥሟችሁ ያውቃል ?________________________________________________

   ________________________________________________________________

2. የሲፖራ እና የፉሐ ውሳኔ ከሰው ይልቅ እግዚአብሄርን መታዘዝ ነበር፡፡እናንተስ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር የሚጋጭ እና ከእግዚአብሄር ጋር ያላችሁን የፅድቅ ኑሮ የሚያበላሽ ትእዛዝ አጋጥሟችሁ ያውቅ ይሆን?________________________________

   ሀ. የተሳተፈው ማነው?________________________________________________

ለ. ሆን ብላችሁ ያለመታዘዛችሁ ውጤት ምን ነበር?________________

ሐ. ምናልባት ሆን ብላችሁ ያደረጋችሁት ለእግዚአብሄር መታዘዛችሁን፤ ወይንም ከፈርኦንን አይነት ትእዛዝ ጋር የማይጋጭ በዘዴ የተፈጠረ መፍትሄ አግኝታችሁ ታውቁ ይሆን?________________________________________

_______________________________________________________________

3. አንዳንድ ሰዎች ሆን ብለው ያደረጉት ነገር ባስከተለባቸው ችግር ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፡፡አንዳንዶች ስራቸውን አጥተዋል፣ሌሎች ስፍራቸውን፣ሌሎች ደግሞ ስልጣናቸውን አጥተዋል ፡፡ መናልባት በመላው ዓለም ከሰው ይልቅ እግዚአብሄርን ለመታዘዝ በመወሰናቸው ምክንያት የተለያየ መከራ እንደደረሰባቸው ስንሰማ ቀላል ይመስል ይሆናል፡፡ብዙዎች አሁን እንኳን ለእየሱስ ክርስቶስ ታማኝ በመሆናቸው ምክንያት ብዙ መከራን ይቀበላሉ ብሎም ህይወታቸውን እስከማጣት ይደርሳሉ፡፡

ሀ. ከሰው ይልቅ እግዚአብሄርን እንድታዘዝ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲገጥመንኝ ምንያህል ታማኝ ነኝ?_______________________________________________

_______________________________________________________________

ለ. ኃላፊነት ተሰምቶኝ፣በበጎ ህሊና እና በታማኝነት ይገኜ እውነትን ለመናገር በጣም አስቸጋሪ የሚሆንብኝ በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ____________________

_______________________________________________________________

ሐ. ከእግዚአብሄር ይልቅ ሰዎችን እና ሁኔታዎችን እንዲሁም ሁኔታዎቹ የሚያስከትሉትን ነገሮች በመፍራት ትክክል ያልሆነ ነገር አድርጌ ይሆን? ለሌሎችስ የመውደቅ ምክንያት ሆኜ ይሆን?ለዚህ የፀፀት እና የጥፋተኝነት ስሜት ምን ማድረግ አለብኝ?

_______________________________________________________________

በእነዚህ በፍርሀት በተሸነፍንባቸው ወቅቶች እንኳን እግዚአብሄር ብቻችንን አይተወንም፡፡ጌታ ታማኝ ነው፡፡ፍቅሩ ከወደቅንበት አንስቶ ተስፋን ይሰጠናል፡፡ይቅር ይለናል እንደገና በሚገጥሙን ተግዳሮቶች ላይ ያበረታናል፤ ፀንተንም እንድንቆም ያደርገናል፡፡

**ማሰላሰል፡** በኤፌሶን 6፡10-11 እና 13-14 የእግዚአብሄር ኃይል በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የእኛ እንደሆነ ዋስትና ይሰጠናል፡፡ "የበረታችሁ ሁኑ!" "ፀንታችሁ ቁሙ!" ይህንን ቁጥር በካርዳችሁ ላይ ፃፉት እያሰላሰላችሁት ተደሰቱበት እያወቃችሁ ከሰው ይልቅ እግዚአብሄርን ማስደሰት እንድትችሉ እንዲያደርጋችሁ እራሳችሁንም በዚህ ቃል አስታጥቁ ፡፡

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ ስለ ሲፖራ እና ስለ ፉሐ እንብቤያለሁ ኃይልህ በእነሱ እየሰራ እንደነበር አውቂያለሁ እባክህ ያው ኃይል በእኔም ይስራ፡፡ትክክለኛውን ነገር እንድናገር እና እንዳደርግ እባክህ ባንተ ላይ እንድደገፍ አድርገኝ፡፡እነዚህ ሰዎች ባንተ አምነው ነበር፡፡በፍቅርህ ፍርሀት ውስጥ በመሆን ላንተ ምላሽን ሰጥተዋል፡፡ እኔም ባንተ አምናለሁ እናም ባንተ ማመኔን በሚገልጥ ሁኔታ ህይወቴን መኖር እፈልጋለሁ፡፡________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

**ክፍል 3፡**

***መግቢያ*** ፡ ለውጥ እዲመጣ ያስፈልጋል፡፡እስራኤላውያን እግዚአብሄር ለአብርሐም ተስፋ ወደሰጠው ምድር መግባት ካለባቸው ግብፅን ለቀው መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን በግብፅ የነበረው ሁኔታ ለእነሱ ምቹ ነበር፡፡ ስለዮሴፍ የማያውቀው ንጉስ እስኪነግስ እና በጭካኔ እስኪነሳባቸው ድረስ እንዲሁም እስራኤላውያን ብዙ ሕዝብ እስኪሆኑ ድረስ  በግብፅ ተመችቷ ቸው ነበር የሚኖሩት፡፡

ስለዚህ እነዚህን ህዝቦች ካሉበት የምቾት ስፍራ ለማስወጣት እረፍት የሚነሳ እና ምቾት የሚያሳጣቸው ነገር መፈጠር አለበት፡፡በዚህ ግዜ ነበር አዲሱ የግብፅ ንጉስ አለቃ ሾሞ ባሪያ ሊያደርጋቸው እና ከባድ ስራ ሊያሰራቸው የተነሳው፡፡ግብፃውያንም ልጆቻቸውን ወደወንዝ እስከመወርወር ድረስ ከፉባቸው፡፡በዚህ ምክንያት በምድሪቱ ሁሉ ላይ ታላቅ ለቅሶን እንዲሆን አደረገ፡፡

ዘፀአት 2 የዚህን ታሪካዊ ክስተት ገፀ ባህሪያት ያሳየናል፡፡ ህዝቡን አስመርረው ወተት እና ማር ወደምታፈስ ምድር ወደ ከነአን ጉዞ እንዲጀምር ለማድረግ ሁሉም የራሳቸውን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 2ትን አንብቡ፡፡ይህን ክፍል ስታነቡ የምታገኟቸውን ስሞች በማስታወሻ ደብተራችሁ በመያዝ አጥኗቸው;;

***መልመጃ፡*** እነዚህ ገፀ-ባህሪያት እነማን ናቸው? በቁጥር አንድ ላይ ከሌዊ ነገድ የሆን አንድ እስራኤላዊ ቤተሰብ በተለየ መልኩ እንመለከታለን፡፡ምናልባት ሌዊ ሶስተኛው የያዕቆብ እና የልያ ልጅ እንደነበር ታስታውሳላችሁ (ዘፍጥረት 30፡40)፡፡

1. በዘፀአት 2፡1 አንድ ሰው ሚስት እዳገባ እና ወንድ ልጅ እንደወለደ እንመለከታለን፡፡እዚህ ስፍራ ላይ ያልተለመደ አዲስ ነገር የለም፡፡ቁጥር 26፡59 እንደ ማጣቀሻ ተጠቀሙበት፡፡
   ሀ. የአባቱ ስም ማን ነበር ?________________________________________
   ለ. የእናቱስ ስም ማን ነበር ?________________________________________
2. ይህቺ እናት የእርግዝናዋን ወራት በሙሉ በማህፀኗ ያለው ልጅ ሴት እንደሆነች ተስፋ አድርጋ ነበር፡፡ነገር ግን የወለደችው ወንድ ነበር፡፡ወንድ ከመውለዷ እና ያልጠበቀችው ነገር ከመፈጠሩ በተጨማሪ ይህቺ እናት በቁጥር 2 ላይ ምን ተመለከተች ይላል?

   ____________________________________________________________
3. የካብድ ለወራት ያክል ልጁን መሸሽግ ችላ ነበር፡፡ወደ ወንዝ ልትወረውረው አልቻለችም ነበር፡፡ነገር ግን ልትሸሽገው ባልቻለች ግዜ ምን ነበር ያደረገችው?__________________

   ____________________________________________________________
4. በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅጥራን ስለመቀባት የተፃፈ ነገር ታስታውሳላችሁ? እስቲ ከዘፍጥረት 6፡14 ጋር አነፃፅሩ፡፡ምን አይነት መመሳሰል አገኛችሁበት?_______________

   ____________________________________________________________
5. በዘፍጥረት 2፡4 እህቱ በርቀት ላይ ቆማ በወንድሟ ላይ የሚሆነውን ነገር ትከታተል እንደነበር ተነግሮናል፡፡በዘሁልቁ 26፡59 የእህቱ ስም ማን ይባል ነበር?_______________

   ____________________________________________________________
6. በቁጥር 5 ላይ የፈርኦን ሴት ልጅ እና ደንገጡሮቿ ወደወንዝ ሊታጠቡ እንደወረዱ ተነግሮናል ፡፡ቅርጫቱን ተመለከተችው፡፡ቀጥሎ የተፈጠረው ነገር ምን ነበር? _________

   ____________________________________________________________
7. ዕብራዊው ህፃን ከውሃ ውስጥ በተገኘ ግዜ የህፃኑ እህት ማርያም ለፈርኦን ልጅ በቁጥር 7 መሰረት ምን አማራጭ አቀረበችላት ? ________________________________

   ____________________________________________________________

ገለፃ፡

1. ማሪያምም ወደ እቤት ተመልሳ የህፃኑ እናት ዮካብድ አገኘቻት ልጇንም ከፈርኦን ልጅ ተቀበለቻት፡፡እስቲ ይህንን ለአንድ አፍታ አስቡ፡፡
   ሀ. ልጃችሁን ወደወንዝ እንደማይጣልባችሁ ማረጋገጫ አግኝታችሁ ልጃችሁን መልሳችሁ ከእቅፋችሁ ማስገባት ምን ሊመስል ይችላል? አሁን የእናንተ የሆነ ዘር ነው መሆንም ያለበት የእናንተ ነው ነገር ግን በፈርኦን ልጅ እየተጠበቀ ነው፡፡______________________________

   ______________________________

   ለ. እርግጠኛ ባንሆንም ልጁ ከአራት እስከ ስድስት አመት ከእናቱ ከዮካቤድ ጋር እደነበር እንገምታለን፡፡በፈርኦን ቤት ለሚኖረው ህይወት ስትንከባከበው፣ ስታዘጋጀው እናትየው በእርሱ ላይ የምታሳድረውን ተፅእኖ አስቡ፡፡ እስቲ እንደ እስራኤላዊ እናት ልጃችሁን ልታስተምሩት የምትችሏቸውን ነገሮች ጥቂቶቹን ፃፉ:

      1. ______________________________
      2. ______________________________
      3. ______________________________

2. በቁጥር 2 ዮካቤድ ልጁን እንደተመለከተችው እና መልካም ልጅ እንደሆነ አንዳየችው አውቀናል፡፡ስለ ህፃኑ ምን የተረዳች ይመስላችኋል? ሌሎች እናቶች ልጆቻቸውን ተመልክተው ሊያስቡት ከሚችሉት የተለየ ነገር አስባ ይሆን እስቲ በተጨማሪ ዕብራዊያን 11፡23ን ተመልከቱ______________________________

   ______________________________

3. እናንተስ ልጆቻችሁን ግዜ ሰጥታችሁ በመደነቅ እና በመገረም ተመልክታችሁ መልካም ልጆች እንደሆኑ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? ወይንስ ጭጋግ አይኖቻችሁን ጋርዷችሁ መልካም መሆናቸውን ለመመልከት ገና በትግል ላይ ናችሁ?__________________

   ______________________________

4. ስለራሳችሁስ? እራሳችሁን በፈጣሪያችሁ እይታ ተመልክታችሁ መልካም ልጆች መሆናችሁን አስተውላችኋል?ጉንጫችሁን በእጆቹ ይዞ አይናችሁን እየተመለከተ “የእኔ ልጅ አንተን መልካም እድርጌ ፈጥሬሀለሁ” እያለ ሲያናግራችሁ ሰምታችሁታል?

ሲመለከታችሁ ተድላውን፣ ደስታውን ፣ እንደገና እናንተን ለፈጠረበት አላማ መኖራችሁን ማረጋገጫ ሲሰጣችሁ ተመልክታችሁታል?__________________________

________________________________________________________________

5. ሶፎንያስ 3፡17 እግዚአብሔር በእኛ ደስ እንደሚሰኝ ያስታውሰናል

   ሀ.__________________________ በመካከልሽ ______________________________

   ለ. ____________________________ በአንቺ__________________________፥

   ሐ. በ_________________________፥ በእልልታም__________________________!

   እስቲ ይህን አስቡ !

**ፀሎት፡** አባት ሆይ ዛሬ ላይ ዙሩያዬን ስመለከት ብዙ አይነት ሰዎችን አገኛለሁ አስተማሪዎችን፣ የቤተክርስቲያን፣ ሰራተኞች፣ አሰሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣የማህበረሰብ አገልጋዮች እንደመልካም ልጅ እንዳያቸው የሚገባኝ እነዚህን ሰዎች አገኛለሁ፡፡እራሴን አሳንሼ ስመለከት እና ውድቀቴን ብቻ ስመለከት እባክህ አንተ በእኔ ደስ እንደሚልህ እና ለአንተ መልካም ልጅ መሆኔን አስታውቀኝ፡፡መልካም ልጅ አድርገኸኛል፡፡የአንተ አድርገህ ነው የሰራኸኝ፡፡እንተን በመፍራት ድንቅ አድርገህ ስለሰራኸኝ በታላቅ ደስታ ምስጋና አቀርብልሀለሁ ፡፡________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## ክፍል 4

**መልመጃ፡** የዮካቤድ እቅድ ተሳክቷል፡፡ ልጇ እስኪያድግ ድረስ በደህና ወደ እቅፏ ተመልሶላታል፡፡አሁን ደግሞ ልጁን ለፈርኦን ልጅ የምታስረክብበት ግዜ ደርሷል ከዚህ በኂላ እንደ ልጇ አድርጋ ታሳድገዋለች፡፡

1. በቁጥር 10 ላይ ልጁ ስም እደተሰጠው አውቀናል፡፡የፈርኦን ልጅ የራሷ ልጅ እንደሆነ አውጃለች ስምም አውጥታለታለች፡፡ስሙም ___________________________ነው፡፡የስሙ ትርጉም ምንድነው?______________________________________________________
2. ሙሴ በግብፃውያን ቤት የተነሳ ዕብራዊ ነው፡፡በራሱ በፈርኦን ቤተመንግስት እና ፍርድ ቤት የተነሳ ሰው ነው፡፡እንዲህ ብለን ማጠቃለል እንችላለን ሙሴ ዕብራዊነቱን አውቆ

ያደገ ልጅ ነው።እንደወጣት ሰው ስናስበው በወገኖቹ እስራኤላውያን ላይ የተጫነውን ከባድ ስራ ያውቃል።አንድ ቀን ህዝቦቹን ሲጎበኝ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 11-14)?______

______________________________________________________________

3. ድርጊቱ ያስከተለው መዘዝ ነገር ምን ነበር?______________________________

4. ሙሴ ወገኑን ለመርዳት ብሎ ግብፃዊውን እንደገደለው ፈርኦን ከሰማ እንደሚገድለው ሲያስብ ያደረገው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 15)?____________________________

5. ቁጥር 15 በቀላሉ እንዲህ ይላል "……ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኰበለለ፥ በምድያምም ምድር ተቀመጠ በውኃም ጕድጓድ አጠገብ ዐረፈ።" ነገር ግን እነዚህን ሶስት ድርጊቶች በቀላሉ ልናልፋቸው አይገባም።

   ሀ. ሙሴ ከፈርኦን ፊት ኮበለለ…."ሙሴ ለፈርኦን ምኑ ነበር? እንደልጁ ልጅ እያየ አደሳድጎት ይሆን?በመላው ግብፅ ላይ ኃይል ባለው ሰው ቤት ውስጥ የልጅ ልጅ ተብሎ ማደግ ምን ማለት እንድሆነ አስቡት።ታዲያ ይኸው ሰው አሁን ሊገድለው መፈለጉ ምን ሊመስል ይችላል?______________________________

   ______________________________________________________

   ለ. "በምድያምም ምድር ተቀመጠ……" ካርታችሁን በመተቀም በዘፀአት ግዜ ከነአንን አሸንፈው በያዙበት ወቅት የነበረችውን ምድያምን በካርታችሁ ላይ ጠቁሙ።እንደገናም በካርታችሁ ላይ በግብፅ ለም መሬት የሚገኙትን ጌሴምን እና ራምሴን በካርታው ላይ  ጠቁሙ። እነዚህ ስፍራዎች ሙሴ ወደምድያም ጉዞውን ከየት እንደጀመረ እንድትረዱ ያደርጋችኋል።በደቡብ ተጉዞ የአባይን ወንዝ አቋርጦ በምዕራብ ወደ ቀይ ባህር ተጓዘ።በደቡብ በምትገኘው የሲና የባህር ሰርጥ ጉዞውን ቀጠለ።በስተምስራቅ የምትገኘው ምድር ምድያም ናት። ምድያም ለመድረስ መንገዱ ቀላል አቋራጭ አልነበረም።በጣምም እሩቅ ነበር።የሲና ተራራ ጉዞውን ይበልጥ አድካሚ እና ረጅም ያደርገዋ የጌቭ በረሀ ደግሞ ምንም መጠለያ የለውም።ከፈርኦን ቁጣ ለማምለጥ ሊሸሽ ያሰበው ይህንን ያክል እርቀት ነበር ይሆን ? ምድያምን ለምን እንደመረጠ አልተፃፈልንም።ለምን ምድያምን የመረጠ ይመስላችኋል?______________________________

   ______________________________________________________

   ሐ. "በውኃም አጠገብ አረፈ" ይህ ውሀ በበረሀ አካባቢ የሚገኝ ለምለም ቦታ እንደሆነ እናስባለን።እረኞችም መንጋቸውን ለማጠጣት የሚመጡበት ስፍራ

ነው፡፡ምክንያቱም ያስፍራ በአካባቢው የሚኖሩት ማህበረሰቦች ውሀ የሚቀዱበት ስፍራ ነው በዚህ ምክንያት መረጃ የሚለዋወጡበት ስፍራ ነው፡፡ታሪኩ ሙሴን ውሀው ዳር በአድካሚው ጉዞ ምክንያት ጥማቱን ሊያረካ እንዲሁም ከድካሙ የተነሳ በዛ እንዳረፈ ይነግረናል፡፡

6. ሙሴ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ  እያለ ምን ተፈጠረ?(ዘፀአት 2፡16 -17)
   ሀ. ማን ውሃ ሊቀዳ መጣ ?____________________________________________
   ለ. አባታቸው ማን ነበር ?____________________________________________
   ሐ. ለምን ነበር ውሃ የሚቀዱት ?______________________________________
   መ. ቁጥር 17 ላይ ምን ተፈጠረ ?______________________________________
   ሠ. ሙሴ ምን አደረገ ?_______________________________________________

7. እህትማማቾቹ ከወትሮ በተለየ መልኩ ፈጥነው ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ይህ ደግሞ በአባታቸው በራጉኤል ዘንድ ጥያቄ አስነሳ፡፡ሙሴ እንደረዳቸው እና እንዴት ቀድመው በጎቻቸውን ማጠጣት እንደቻሉ በዚያ የተፈጠረውን ነገር በሙሉ አስረዱት፡፡ወደ ውሃው ጉድጓድ አካባቢ ከዚህ በፊት እንግዳ መጥቶ ስለማያውቅ የሙሴ በዚያ መገኘት ምንያህል መልካም አቀባበል እንደሚደረግለት አስቡ፡፡ ጥያቄዎቹን በሙሉ ልብ በኋቸው፡፡ከእነዚህ ሰባት ሴት ልጆቹ ጋር የሚኖረው አባት ይህንን ወንድ ለመቀበል ምን ያህል እንደሚጓጓ ማሰብ አይከብድም፡፡ሙሴም የራጉኤልን መስተንግዶ ተቀበለው፡፡በቁጥር 21-22 ላይ በተጨማሪ ምን እማራለን?
   ሀ. የሚስቱ ስም ማን ነበር?_________________________________________
   ለ. የልጁስ ስም ማን ነበር የስሙስ ትርጉም ምን ነበር ?____________________
   ሐ. ስለዚህ ሙሴ በምድያም በእረኝነት ____________አመት ያህል ቆየ ?________

8. ለጥቂት ግዜ ወደ ግብፅ እንመለስ በዘፀአት 2፡23 ላይ ምን እንማራለን ?
   ሀ. የሙሴ አያት በሆነው ፈርኦን ላይ ምን ሆነበት ?______________________
   ለ. በእስራኤላውያን ላይስ ምን ሆነባቸው ?______________________________

**ስለ እግዚአብሄር ምን እንማራለን (ዘፀአት 2፡24-25)፡**

- እግዚአብሔርም የለቅሶአቸውን ድምፅ_____________________________፥
- እግዚአብሔርም _______________ያደረገውን ቃል ኪዳን _______________፡፡
- እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች _________________________________፥

- እግዚአብሔርም_______________________________________::

1. በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት አራት የእግዚአብሄር ስራ ገላጭነት እግዚአብሄርን እናንተ እንደተረዳችሁት እና እናዳወቃችሁት ልክ ግለፁት፡፡እግዚአብሄር የእናንትን ጩኸት ፣ማጉረምረም ፣እንዲሁም ስቃያችሁን እንደሚሰማ ታምናላችሁ? የገባላችሁንስ ተስፋ እንደማይረሳ ታውቃላችሁ? እግዚአብሄር በቅርበት ሆኖ ያላችሁበትን ሁኔታ እንደሚከታተል እና እንደሚመለከትስ ታውቃላችሁ መውጣት መግባታችሁን ፣መሄድ መምጣታችሁን ነገሮቻችሁን ሁሉ በቅርበት አንደሚከታተል ታውቃላችሁ?እግዚአብሄር ስለ የጥፋተኝነት ስሜታችሁ፣ስለብቸኝነታችሁ፣ስለተበላሸው ግንኙነታችሁ፣ሁሉ ግድ ብሎት ትኩረት ሰጥቶ አንደሚከታከተል ታውቃላችሁ? እስቲ የምትፀልዩባቸው ሀሳቦች ምንድናቸው ?_______________________________________________

   _______________________________________________

2. ፈጣሪያችሁ እግዚአብሄር ጩኸታችሁን እንደሚሰማ ፣ቃልኪዳኑን እንደሚያስብ፣እንደልጅ እንደሚያያችሁ እና ስለ እናንተ ግድ እንደሚለው ማውቃችሁ በህይወታችሁ ውስጥ ምን ልዩነት ሊያመጣ ያችላል?_______________________

   _______________________________________________

**ፀሎት፡** እስቲ በራሳችሁ ቃል እግዚአብሄርን እንደ አባት በመቁጠር እንደሚሰማ፣ እንደሚያስታውስ፣ስለ እናንተም ግድ እንደሚለው በማሰብ በራሳችሁ ቃል አናግሩት:_______

_______________________________________________

_______________________________________________

**ክፍል 5**

***መግቢያ*፡** አንድ ሰው ሁሉም ነገር በስፍራው እንዳለ ሊሰማው ይችላል፡፡አሁን ገፀ ባህሪያቱ ተለይተዋል፡፡እስራኤላውያን እርካታ አጥተዋል፡፡ይጮሀሉ ያለቅሳሉ በጣም ታላቅ የሆነ ያለመርካት ይታይባቸዋል በዚህም ምክንያት ህይወታቸው ለለውጥ ተዘጋጅቷል፡፡ነፃ እንዲያወጣቸወ ወደ እግዚአብሄር ጮኸዋል፡፡ጩኸታቸውን እና የስቃይ ለቅሶአቸውን ለምቷቸዋል፡፡እግዚአብሄርም ቃልኪዳኑን አስቧል፡፡ትኩረቱን ወደተመረጡት ህዝቦች አድርጓል፡፡በርህራሄ ተንቀሳቅሷል አሁን በድርጊት የሚገለጥበት ግዜ ነው፡፡

**ገለፃ፡** እግዚአብሄር ለምን እስራኤላውያንን ከተያዙበት ባርነት ለማስለቀቅ ኃይሉን ደረጃ በደረጃ እንደተጠቀመ ስናስብ ሊገርመን ይችላል።ልምን በቀጥታ ወዲያውኑ እንዲለቀቁ አላደረገም?

1. ለቅሷቸውን ከሰማ እንዲሁም ያሉበትን ሁኔታ ከተመለከተ ለምን ምትሀታዊ ድርጊት ወይንም ምትሀታዊ ቃል በመናገር ወዲያውኑ ያሉበትን ሁኔታ የተሻለ አላደረገውም? ያንን ማድረጉ ለሱ ትርጉም ይሰጠው ይሆን? ለምሳሌ የልጆች እና የወላጆችን ግንኙነት ለአፍታ አስቡ።ልጆቻችሁን ከገቡበት አስቸጋሪ እና የማይመች ሁኔታ ውስጥ ማውጣት ያን ያህል አስፈላጊ ነገር ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ልጆች ከዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን አይነት ትምህርቶች ሊማሩ ያችላሉ?በእንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የተማርናቸው ነገሮች ምንድናቸው? በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ አልፈን ያዳበርናቸው ባህሪያትስ ምንድናቸው?__________________________________

   ____________________________________________________________

2. እስራኤላውያን ጮሁ እግዚአብሄርም ጩኸታቸውን ሰማ። በዘፍጥረት 15፡13 ላይ እግዚአብሄር ለአብርሐም ዘሩ ምን እንደሚገጥመው ነግሮት ነበር? በባርነት ስንት አመት ኖሩ? ከያዕቆብ እና አስራሁለቱ ልጆቹ በኋላ በጣም በዙ ትውልድ እንዳለፈ አስታውሱ።ከእግዚአብሄር ጋር ያለው ቅርርብ እንደቀደሙት አባቶች ግዜ የጠበቀ አልነበረም።በእግዚአብሄር እና በህዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት ማደግ አለበት።እግዚአብሄር ማን እንደሆነ፣ማን እንደ ነበረ ፣ከእነሱ ምን እንደሚጠብቅ ማወቅ ይኖርባቸዋል።እሱ አምላክ ሊሆናቸው እነሱ ደግሞ ህዝብ ሊሆኑት ቃል ገብቶላቸዋል ነገር ግን ይህ ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል።ለእነሱ ያለውን ታማኝነት ማወቅ አለባቸው ።መታዘዝንም መማር ይኖርባቸዋል።ሌላስ ተጨማሪ መሆን ያለበት ነገር ምንድነው?______________________________________________

   ____________________________________________________________

3. እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ከነአንን ለመውረስ ከመውጣታችው በፊት እግዚአብሄር ማዘጋጀት የሚያስፈልገው ነገር ምንድነው?_____________________________

   ____________________________________________________________

4. የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ በሚያደርጉት ጉዞ ለሚገጥማቸው ተግዳሮት እንደ አንድ ህዝብ ሆነው ለመውጣት ምን ያስፈልጋቸዋል? ወደ ክነአን ከመውጣታቸው በፊት መዘጋጀት ያለባቸው ነገር ምንድነው?________________________________________

______________________________________________________________________________

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ እንደምታውቀኝ ቀላል የሆነ የመውጫ መንገድ ነው የምፈልገው፡፡ችግር የሚሆኑብኝን እና የማይመቹኝን ነገሮች ከመንገዴ ላይ አወስግዳቸዋለሁ፡፡በአስቸጋሪ ወቅቶች አንተ ከእኔ ጋር ልትሰራ ስትመጣ በችግሮቹ ውሰጥ ታግሼ በመቆም አንተ የምታደርገውን በትእግስት መጠበቅ ሲገባኝ ብዙ ግዜ ይህንን እድል አበላሽቻለሁ፡፡የአንተን ባህሪይ በህይወቴ ውስት እንድትገነባ እፈልጋለሁ፡፡የአንተን ባህሪይ በውስጤ የሚገነባው እኔ በፈለኩት እና በተመቸኝ መንገድ ብቻ እንዳልሆነ እንድረዳ አድርገኝ፡፡ጌታ ሆይ ከሁሉ በላይ ደግሞ ከአንተ ጋር ያለኝ ጤናማ ግንኙነት ከሁሉም በላይ ለይወቴ አስፈላጊ እንደሆነ አስተምረኝ፡፡በህይወቴ ውስጥ ምንም አይነት ነገር ቢፈጠር አንተ ያንን እኔንም ሆነ ሌሎችን በሚጠቅም መልኩ ለበጎ እንደምትለውጥው በማመን እንድፀና እርዳኝ፡፡______________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

# ትምህርት ሁለት

# እግዚአብሄር ጠራው

## ዘፀአት 3- 4 እኔ እኔ ነኝ

---

### የትምህርት ሁለት ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 2፡ ዘፀአት 3-4

- የሚነደው ቁጥቋ ጦ
- የእግዚአብሄር ጥሪ ተግዳሮት
- ቅርብ የሆነው አምላክ
- አመፀኛው መሪ
- ጉዞ ተመልሶ ወደግፅ

**በግቢያ**

ትምህርት አንድ "እግዚአብሄር ሰማ፣.......አስታወሰ......ተመለከተ.......እና አወቀ በሚሉ ቃላት ነው የተደመደመው፡፡ጩኸታቸውን ሰማ፡፡ለአብርሐም ፣ለያዕቆብ ፣እንዲሁም ለይስሀቅ የገባውን የተስፋ ቃል አስታወሰ፡፡የህዝቡን ስቃይ ተመለከተ ተረዳም፡፡በእነዚህ አመታት ውስጥ እግዚአብሄር ከህዝቡ ርቆ እንዳለ አይነት ነው የተገለፀው ነገር ግን እርሱ እሩቅ እንዳልነበረ ስለህዝቡ ግድ እንደሚለው ያውቃል፡፡በዚያን ግዜ ለስራ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡

እግዚአብሄር ሙሴን ያገኘው የት ነበር? ሙሴን ለማግኘትስ የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበር? በህይወታችሁ ውስጥ ለምታደርጉት ውሳኔ እግዚአብሄርን ሰምታችሁ ከወሰናችሁ ህይወት ቀላል እንደሚሆን አስባችሁ ታውቃላችሁ? ሙሴ ለእግዚአብሄር ከሰጠው ምላሽ ተማሩ እንዲሁም ለእግዚአብሄር እንዲሰራለት የተመረጠበትንም ነገር እንዲሁ፡፡ ስለእግዚአብሄር ባህሪም አዲስን መረዳት ተመልከቱ፡፡ የህይወትን ጥቅም ከእግዚአብሄር እይታ አንፃር ተመልከቱ፡፡ እግዚአብሄር ትኩረት ካደረገበት ታላቁ ምስል እርሱም የህዝቡ ህይወት ጋር መታገል ነው፡፡

እግዚአብሄር ቃልኪዳኑን ሊጠብቅ ወስኗል፡፡ሙሴም ይህንን የቤት ስራ እንዲሰራ የተመረጠ የእግዚአብሄር ሰው፡፡ሙሴ በእርሱ የተመረጠ መሪ ነው፡፡ሙሴን ለዚህ ስፍራ ተመራጭ ያደረገው ምን እንደሆነ ልብ በሉ፡፡የማይቻለውን የሚቻል ያደረገው ምን ነበር?

የታሪኩ መንፈስ የሚያርፈው እግዚአብሄር በሾማቸው መሪዎች ላይ ሳይሆን መሪዎቹ ሊከተሉት በሚገባው ነገር ላይ ነው፡፡መሪዎች ይከተላሉ፡፡ሙሴ የተጠራው እንዲከተል ነው፡፡ታሪኩ ውስጥ ግቡ እና ሙሴን የታላቁን "**እኔ**" አገልጋይ ሆኖ ተመልከቱት፡፡

**ክፍል 1**

**በግቢያ፡** ብዙ ስዎች ስለ ሙሴ እና እለምትነደው ቁጥቋጦ ሰምተዋል፡፡ግዜ ውሰዱ እና ይህንን ታሪክ በሙሉ አንብቡት፡፡በካርታችሁ ላይ የሲናን ሰርጥ፣የሲናን ተራራ፣እና ምድያምን አመልክቱ፡፡ጥናታችሁን እየቀጠላችሁ በሄዳችሁ ቁጥር የምታገኟቸውን አዳዲስ ነገሮች ተከታትላችሁ በማስታወሻቸሁ ላይ መያዝን አትርሱ፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 3-4፡17 አንብቡ፡፡

**መልመጃ፡** ሙሴ ለአማቱ የበግ እረኛ ሆኖ እንዳገለገለ ተነግሮናል ፡፡በዚች ልዮ ቀን በኮሬብ ተራራ ወይንም ሲና ተራራ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ላይ ከቤቱ መጠነኛ እርቀት ላይ ሆኖ በጎች ይጠብቅ ነበር፡፡

1. በቁጥር 2 እና 3 ላይ ሙሴ ምንን ተመለከተ ?________________________________

   ____________________________________________________________________
2. ከከፍተኛ ሙቀት የተነሳ በበረሀውስጥ የቁጥቋጦ መቃጠል ብዙም እንግዳ አይደለም፡፡በተለያ እሾሀማ የሆኑት ቁጥቋጦዎች ለዚህ ቅርብ ናቸው፡፡ታዲያ ይህንን ሁኔታ ለየት ያደረገው ምንድነው?________________________________________

   ____________________________________________________________________
3. በቁጥቋጦ ውስጥ ለሙሴ ማን ተገለጠለት?________________________________

   የእግዚአብሄር መላእክ ማን ነበር? አጋርም ከእመቤቷ ከሳራ ቤት ስትሰደድ በዚያ ምድረበዳ የእግዚአብሄር መላእክ ተገልጦ አገልግሏታል፡፡(ዘፍጥረት 16፡7-10) ስለዚህ የእግዚአብሄር መላእክ በሚቀጥሉት ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ በዘፀአት 3 ውስጥ እናያለን፡፡
4. ሙሴ ወደዚህ እንግዳ ወደሆነው ነገር እየቀረበ ሲመጣ ቁጥቋጦው ለምን እንደማይቃጠል በማወቅ ጉጉት ውስጥ ሆኖ ቀረበ፡፡ሙሴ እየሆነ ያለውን ነገር ለማወቅ ወደ ሚነደው ቁጥቋጦ ሲመጣ (በቁጥር 4) ላይ ከቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን የጠራው ማን ነበር?________________________ከቁጥቋጦ ውስጥ የጠራው ምን ነበር ?_________

5. የሙሴ መልስ ምን ነበር? ______________________________

6. በቁጥ 5 ላይ እግዚአብሄር ምን አዘዘው ?______________________________

7. በቁጥር 6 ላይ እግዚአብሄር እራሱን ማን እንደሆነ አወጀ? እራሱን ለሙሴ የገለፀው እንዴት ነበር?______________________________

______________________________

8. ሙሴ ማን እንደነበር እንደሚያውቅ ይታወቃል፡፡በቀጥታ ያደረገው ምን ነበር?_______

______________________________

9. ሙሴ ከግብፅ እንደመነሳቱ፣እንደመሰልጠኑ፣እንደመማሩ እግዚአብሄርን እንዴት ሊያውቀው ቻለ? የፈርኦን ልጅ እሱ እስራኤላዊ እንደሆነ ታስታውሰው እንደነበረ ታስባላችሁ?______________________________

______________________________

10. እግዚአብሄር ለሙሴ የእቅዱን ሶስት ዋና ነጥቦች ነግሮታል፡

ሀ. ቁጥር 7፡ የሰማው እና ያየው ምን ነበር______________ትኩረትስ የሰጠው ለንምን ነበር?______________________________

ለ. ቁጥር 8፡ምን ለማድረግ ነበር የወሰነው?______________እቅዱ እነሱን ከ______________አድኖ ወደ ______________ማምጣት ነበር::

ሐ. ቁጥር 9-10 እግዚአብሄር ለቅሶአቸውን እንደሰማ ጭቆናቸውንም እንደተመለከተ ተናግሯል፡፡ማን ነበር ከግብፅ የሚያወጣቸው?______________________________

______________________________

**ገለፃ፡**

1. እግዚአብሄር ሙሴን "አንተ የእኔ ነህ" በማለት ያበቃል ብሎ ሙሴም ሆነ ማንም ሰው ሊያስበው አይችልም፡፡ሙሴ እግዚአብሄር "ደመናትን ቀድጂ በመውረድ ግብፃውያንን አሸንፌ ህዝቤን ወደ ተስፋይቱ ምድር አስገባለሁ ሲል አልሰማውም ፡፡ሙሴ የጠበቀው

እና እግዚአብሄር የተናገረው ነገር በጣም ይለያያል።ሙሴ እስከመጨረሻው ክፍል ድረስ ከእግዚአብሄር ጋር ተስማምቶ እደነበር አስባችኂል?ስለዚህ ጉዳይ ምን ታስባላችሁ?__

________________________________________________________________

2. እንደገና እግዚአብሄር ይህንን ነግር ለምን እራሱ ብቻውን መስራት እንዳልፈለገ ስናስብ ይገርመናል።ሁሉንም ነገር በቀላሉ እራሱ ብቻውን ሊያደርገው ይችል ነበር።እሱ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ከሆነ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ለማውጣት ለምን የሱ ፍጡር የሆነውን ሰው መጠቀም ፈለገ ?______________________________

________________________________________________________________

<u>**ክፍል 2፡**</u>

**ተጨማሪ ገለፃ፡**

3. ወደሌላው የታሪክ ክፍል ከመሄዳችን በፊት የተማርነውን ነገር እንገልፃለን።"እልክሀለሁ ሂድ…" ሙሴም አለ "የምሄደው እኔ ማነኝ.." አለ። በቁጥር 12 ላይ "እግዚአብሄርም እኔ ካንተጋር እሆናለሁ" እግዚአብሄር እዲህ ሲል ሙሴ ምን እንዲል እንጠብቅ? በርግጥ ያልከኝን አደርጋለሁ።እነዚህን በጎች ወደምድያም እስካደርስ ብቻ ግዜ ስጠኝ አለ። ከእግዚአብሄር እይታ እንፃር ሙሴ ስለተሰጠው የቤትስራ ማወቅ ያለበት አንድ ነገር ምንድነው?________________________________________

4. ጥርጣሬ እና ጥያቄ በምን ያህል ፍጥነት ነው ወደውስጡ የመጣው "እሄድ ዘንድ እኔ ማነኝ ?" ወደ እስራኤላውያን ብሄድ በማን ስልጣን እንደተላኩ ይጠይቁኛል? እኔም ምን እንደምላቸው አላውቅም። ስለዚህ እግዚአብሄር ሆይ ላሰብከው ተልእኮ ትክክለኛውን ሰው ያመረጥክ አይመስለኝም።ያንን ምድር ከ 40 አመት በፊት ለቅቄ ወጣሁ በዛ ላይ ፈርኦን በዛ አለ።እንደገናም ሰዎቹ አያውቁኝም።" "ለንምድነው ካልጠፋ ሰው እኔን የመረጥከኝ? እናስ መሄዴ ግድ ነው?
   ሀ. እንደዚህ አይነት ሁኔታ አጋጥሟችሁ ያውቃል?ከምትችሉት እና ከእናንተ አቅም በላይ የሆነ ነገር እንድትሰሩ ኃላፊነት ተሰጥቷችሁ ያውቃል?________

   ________________________________________________________

**ለ.** የተየቃችሁት ጥያቄስ ምን ነበር? ጥያቄዎቻችሁስ እንደገና ማረጋገጫ ወይንም ዋስትና የሚለምኑ ነበሩ?ወይንስ ለተሰጠው ስራ የምትመጥኑ ሰዎች መሆን አለመሆናችሁን የሚያጠራጥሩ ጥያቄዎች ናቸው?______________________

______________________________________________________

5. እግዚአብሄር በዚህ ዘመን የሚሰጠውስ ተመሳሳይ የቤት ስራ ምንድነው?__________

______________________________________________________

**ትምህርት፡** ሁሉም ክርስትያን ከእግዚአብሄር ዘንድ ጥሪ አለው፡፡እግዚአብሄር በእምነት ብዙዎችን የራሱ ልጆች አድርጓል፡፡ልጆቹም ደግሞ በህይወታቸው ሁሉ በሁሉም ስፍራ እሱን መወከል አለባቸው፡፡እያንዳንዱን ወደዚህ ህይወት ሲጠራ ሁሉም በአንድ ቤተሰብ ጥላ ውስጥ እንዲኖሩ ነው፡፡በዚህ እውነት ብርሀን ውስጥ ለመታዘዝ ያለውን ተግዳሮት ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡

**የቀጠለ ገለፃ፡**

6. እግዚአብሄር ሊልካችሁ ጠርቷችሁ ሳለ ጥሪው ምን ያህል ተግዳሮት ሆኖባችሁ ያውቃል?______________________________________________

______________________________________________________

ምናልባት ጥሪው አንድ ብቻውን ያለን ሰው መጎብኘት፣ ወይንም በሆስፒታል ውስጥ ያሉትን ሰዎች መጎብኘት ይሆና … ወይንም ደግሞ ወደ አእምሮአችሁ የመጣን እንድን ሰው በስልክ ደውላችሁ የሚያፅናን እና ዋስትናን የሚሰጥ ቃል መናገር ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ደግሞ ቤተሰቦቻችሁን ልታገለግሉ ቤት ውስጥ ተጠርታችችሁ ይሆናል……ወይንም ደግሞ በስራ ቦታችሁ የመሪነት ስፍራ ተሰጥቷች ሊሆን ይችላል…….ምናልባት ደግሞ እግዘአብሄር የጎዳና ተዳዳሪዎችን እንድትረዱ እና የተራቡትን እንድትመግቡ ተጠርታችሁ ይሆናል፡፡…..ምናልባትም ደግሞ ለድሆች መጠላያ እንድታዘጋጁ ተጠርታችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ታስባላችሁ______________________________________________

______________________________________________________

7. ምላሻችሁ ምን ነበር? ለምን እኔን ልትልከኝ ፈለክ ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ወይንም ደግሞ እኔ ማነኝ ? ማን ላከኝስ ልበላቸው ብላችሁ ታውቃላችሁ? እነዚህን ጥያቄዎች መልሳችሁ ታውቃላችሁ?________________________________________

______________________________________________________________

8. ለጌታ ጥሪ ምላሽ መስጫ ሌላው መንገድ ምን ይሆን? __________________________

______________________________________________________________

**መልመጃ፡** እናም እግዚአብሄር የሙሴን ጥያቄ መመለስ ጀመረ ነገር ግን እግዚአብሄር ሀሳቡን አልቀየረም፡፡ሙሴ ወደተላከበት መሄድ አለበት!

1. ሙሴ ለእስራኤላውያን መንገር የለበት ምንድነው? ማነው የላከው? ስሙስ ማነው?
2. ሌላው ማለት ያለበት በቁጥር 15 ላይ ያለው ነገር ምንድነው?____________________

   ______________________________________________________________

3. እግዚአብሄር ሙሴን በመጀመሪያ ያመለከተው የሽማግሌዎች ስብሰባ እንዲያደርግ ነው፡፡ለእነሱ ምን እንዲነግራቸው ነው መመሪያ የሰጠው (ቁጥር 16) ?______________

   ______________________________________________________________

4. ቀጥሎ እግዚአብሄር ያደረገውን ነገር ልብ በሉ ቁጥር (16-17)፡፡እግዚአብሄር ለህዝቡ ያሉበትን ሁኔታ በትክክል እደሚያውቅ እና ከዚህ ስፍራ ነፃ ሊያወጣቸው ቃል እንደገባለቸው ነው ሊነግራቸው የፈለገው፡፡ይህ ሁኔታ ለእናንተ ምን አይነት ሀሳብ ይፈጥርባችኋል?________________________________________________

   ______________________________________________________________

5. እግዚአብሄር በሚቀጥሉት አብዛኛዎች ቁጥሮች ውስጥ ከቁጥር 3:18-22 ለሙሴ ቀጣዮን ታሪክ በመንገር ነው የቀጠለው፡፡እነዚን ነገሮች ሙሴ እንዲጠባበቃቸው ከነገረው ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹ ምን ነበሩ?

   ሀ._____________________________________________________

   ለ._____________________________________________________

   ሐ.____________________________________________________

   መ. ___________________________________________________

**<u>ክፍል 3</u>**

ስለ እግዚአብሄር ምን ተማርን? ወደ ምእራፍ 4 ከመሄዳችን በፊት ምእራፍ 3 ስለ እግዚአብሄር የገለጠልንን ነገር እመልከት፡፡አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሄር ከፍጥረቱ እርቆ ያለ አድርገው ያምናሉ፡፡በርግጥ እግዚአብሄር ከፍጥረቱ ጋር ካለ እና ስለፍጥረቱ ግድ የሚለው ከሆነ ፍጥረቶቹ በሙሉ በጥሩ እና መልካም ሁኔታ ውስጥ ይኖሩ ነበር ብለው ያምናሉ፡፡*"የእግዚአብሄር እቅድ እና የእኛ ምርጫ"* በሚለው የትምህርት ክፍላችን ላይ ኃጢአት በምድር ላይ ምን ያህል ጥፋት እዳመጣ እንመለከታለን፡፡እስቲ በምእራፍ 3 ውስጥ የእግዚአብሄርን ለህዝቡ ያለውን ጥንቃቄ፣ርህራሄ፣እና ቀረቤታውን መርምራችሁ አግኙ፡፡

| ማጣቀሻ | የእግዚአብሄር ቅርርብ ከህዝቡ ጋር |
|---|---|
| ዘፀአት 3:4 | እግዚአብሄር ወደሰው ልጆች ወረደ ሙሴንም በስሙ ጠራው |
| ዘፀአት3:6 | እግዚአብሄር እራሱን ለሙሴ አስተዋወቀው |
| ዘፀአት 3:7 | |
| ዘፀአት 3:8 | |
| ዘፀአት3:9 | |
| ዘፀአት 3:10 | |
| ዘፀአት 3:12 | |
| ዘፀአት 3:14-15 | |

1. እግዚአብሄር እሱን እንደ እንደ አምላካቸው እና እንደ አባታቸው ለሚያውቁት የቀረበ ግንኙነት ያለው አምላክ ነው፡፡በዮሐንስ 15፡14-15 እየሱስ ስለ ወዳጆቹ ይናገራል፡፡ደቀመዛሙርቱን ወዳጆች እያለ ይጠራቸዋል ፡፡ " ወዳጆች ብያችኋለሁ____________________________________________________

____________________________________________________________

2. እስቲ ወደ ዘፀአት 3፡16-22 ያለውን ተመልሰን እንመልከት በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ከሙሴ ጋር የመሰረተውን ግንኙነት ተመለከታችሁ? ለሙሴ ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር ያሳውቀዋል፡፡ሌሎች ያላወቁትን ነገር ለሙሴ ይገልጥለታል፡፡እግዚአብሄር ሙሴን ወዳጄ ብሎታል ምክንያቱም የእግዚአብሄር ብቻ ጉዳይ የሆኑትን ነገሮች ይገልጥለት ነበር፡፡
3. እግዚአብሄር ከህዝቡ እና ከፍጥረቱ እርቆ ያለ ፣ለህዝቡ ደንታ የሌለው፣ለዓለም ሁሉ ደንታ የሌለው ይመስላል? እግዚአብሄር ስለእናንተ ግድ የሚለው አምለክ እንደሆነ እንዲሁም እሱን እንደወዳጃችሁ እንድትመለከቱት ስለሚሰራው ነገርም እድታውቁ ይፈልጋል፡፡ወዳጅነቱ እንዴት እየሄደ ነው? እየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ እና አዳኝ በመቀበል ከእግዚአብሄር ጋር በእምነት ወዳጅነት መስርታችኋል?___________________________________________________

____________________________________________________________

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር ሆይ አንተ የቅርብ አምላክ እንደሆንክ እና የምትጠነቀቅልንኝ እንደሆንክ ተመልክቻለሁ፡፡የፈጠርከውን ፍጥረት እንዳልተውክ ነገር ግን ፍቅርህን እና ርህራሄህን በፍጥረትህ ላይ አድርገሀል፡፡ለፍጥረትህ ሁሉ በልብህ ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንዳለህ ለጥቁሩ ለነጩ፣ለድሀው ለሀብታሙ፣ለወጣቱ ለአዛውንቱ ሁሉ እኩል ስፍራ አለህ፡፡ለሙሴ በምድረበዳው በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ እራስህን ገለጥክለት፡፡አንተ ሁለንተናህ ቅዱስ ሆነህ እያለህ እራስህን በስምህ አስተዋወከው እሱንም በስሙ ጠራኸው፡፡ይህ እውነተኛ ወዳጆች የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ ወዳጃሞች እቅዳቸውን ይነጋገራሉ፣ ያስፈራቸውን ፣ ያስጨነቃቸውን ፣ እንዲሁም ፣ ያሳሰባቸውን ነገር ይነጋገራሉ ፡፡ በምድረበዳው ከሙሴ ጋር ዘላቂነት ያለው ወዳጅነት መሰረትክ ፡፡ጌታ ሆይ እኔም ከአንተ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መመስረት እፈልጋለሁ፡፡ ያንተ ወዳጅ መሆን እና አንተን ወዳጄ ብዮ መጥራት እፈልጋለሁ፡፡ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል አንተን በማወቁ

ምክንያት አሁንም ካንተ ጋር ያለኝ ግንኙነት በእርሱ በኩል እያደገ እና እያተነከረ ደግሞም ዘላቂና ዘላለማዊ እንዲሆንልኝ አድርግልኝ፡፡________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## ክፍል 4

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 4 አንብቡ በእግዚአብሄር እና በሙሴ መካከል ያለው ውይይት ቀጥሏል፡፡

**መልመጃ፡** ሙሴ ጥያቄ መጠየቁን ቀጥሏል፡፡እግዚአብሄርም ለሙሴ እሱ ከእግዚአብሄር እደተላከ ህዝቡ ያውቁ ዘንድ ሁለት ምልክቶችን ሰጠው፡፡

1. በ ዘፀአት 4፡1-5 ላይ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ምልክት ምንድነው?______________

   ________________________________________________________________
2. በቁጥር 6-8 የተጠቀሰው ሁለተኛው ምልክት ምንድነው?________________________

   ________________________________________________________________
3. ምናልባት በሁለቱ ምልክቶች ካላመኑ እንደገና እግዚአብሄር ሶስተኛ ምልክት ሰጠው ፡፡ሙሴን ምን እንዲያደርግ ነገረው (ቁጥር 9) ?______________________________

   ________________________________________________________________
4. ሙሴ ነገሩ እንዳገኘው እና የራሱ ፍርሀት እና ድካም እንደያዘው ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ሙሴ ማድረግ ስላልቻለው ነገር አግዚአብሄር ግድ የሚለው ይመስላችኋል? የእግዚአበሄር ትልቁ ፍላጎቱ ምን ይመስላችኋል?______________________________

   ________________________________________________________________
5. ሙሴ ይቅርታ የጠየቀበት በዘፀአት 4፡10 ላይ ምንድነው?______________________
6. እግዚአብሄር እዴት ነበር ምላሽ የሰጠው ቁጥር 11 ላይ?______________________
7. እስከዚህ ደረጃ ድረስ እግዚአብሄር ሙሴን እግዚአብሄር በጣም እንደታገሰው እና እንደተረዳው አትስማሙም? እግዚአብሄር የኃጢአተኛን ሰው ሁኔታ በደንብ ይረዳል፡፡እግዚአብሄር የሰውን ሁኔታ ይወቅ እንጂ እስራኤልን ነፃ ለማውጣት

የመረጠውን ሰው እንቢታ ግን አይቀበለውም።ነገር ግን ሙሴ በዘፀአት 4፡13 ላይ የተናገረው የመጨረሻ ነገር ምንድነበር?_______________________________

8. ሙሴ ሊያደርገው አልፈልገም ።በዚህ ግዜ የእግዚአብሄር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ።ሙሴ ይህንን ተልእኮ ላለመፈፀም በሚያደርገው ትግል ውስጥ እግዚአብሄር አልተሸነፈለትም።በየስፍራቸው ላይ ሊሆኑ የሚገባቸው ጥቂት ነገሮች ነበሩ ።ለመሆኑ እነዚህ ነገሮች ምንድናቸው (ቁጥር 14)?

   ሀ. _______________________________________________

   ለ._______________________________________________

   ሐ._______________________________________________

9. በቁጥር 15 ላይ እግዚአብሄር እዲህ አለ "አንተም…"
   - አንተም ___________በአፉ ታደርገዋለህ። ። እሱም እዲህ አለ "እነ_______________________________"

10. እሱም እንዲህ አለ፡ "እኔ…."
   - እኔ _______________ ከአፉ ጋር እሆናለሁ ፥ የምታደርጉትንም ______________________

11.እንዲህ አለው፡ "አሮን…"

   ሀ. እርሱ ስለ አንተ ከሕዝቡ ጋር ይናገራል እንዲህም ይሆናል እርሱ ________ ይሆንልሃል አንተም _________________________ትሆንለታለህ።

   **ለ. ጉዳዩ ተዘጋ!**

12.እግዚብሄር ከሙሴ ጋር ያለውን ትግል ከመጨረሱ በፊት አንድ የመጨረሻ መመሪያ ሰጠው።ይህ መመሪያ በዘፀአት 4፡17 ላይ ያለ ሲሆን ምን የሚል ነበር?

   ሀ. ከእሱ ጋር ምን እንዲወስድ አዘዘው?________________________________

   ለ. አብረውት ያሉት ለምን አላማ ነበር ሙሴን የሚያገለግሉት?____________

   በሚቀጥሉት ጥናቶቻችን ሙሴ እነዚህን የስራ ባልደረቦቹን ሲጠቀምባቸው እንመለከታለን።የእግዚአብሄር ለሆነው ህዝብ እነዚህ ሰዎች የፀጋ እና የምህረት ቡድን ነበር።የእግዚአብሄር ህዝብ ላልሆኑት ደግሞ የፍርድ ቡድን ነበሩ።

***ገለፃ፡*** *ይህንን ታሪክ በወቅቱ ከአሌክአንደሪያ የምትዘግቡ ዘጋቢዎች ብትሆኑ ኖሮ ከሙሴ ጋር የምታደርጉት ቃለመጠይቅ ምንን ያጠቃልል ነበር? በመጀመሪያ ገፁ ላይስ የምታወጡት ፎቶስ ምንን የያዘ ነበር የሚሆነው? አርእስተ ዜናዎቹስ ምን ይሆኑ ነበር፡፡___________________*

______________________________________________________________________

## <u>ክፍል 5</u>

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 4፡18-23 እና 4፡27-31 አንብቡ፡

***መግቢያ፡*** *ሙሴም በጎች ይጠብቅበት ከነበረበት ከኮሬብ ተራራ ወደ አማቱ ቤት ተመለሰ፡፡የእግዚአብሄር ህዝብ የሆነውን እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ያወጣ ዘንድ ከአባቶቹ አምላክ ከእግዚአብሄር የተቀበለውን ትእዛዝ ይዞ ሚስቱን ሲፖራን እና ልጁን በጎቹን እዲጠብቁ አድርጎ ተመለሰ፡፡ወደቤት ሲመለስ በመንገድ ላይ ውስጡ የሚመላለሰው ሀሳብ ምን ይሆን? ለአማቱ ለዮቶር ሊነግረው ያለው ነገር ምን ይሆን?ለሚስቱ ለሲፖራ እና ለሁለቱ ልጆቹ ይህንን ነገር እዴት አድርጎ ያብራራላቸዋል ፈፅሞ ከዚህ በፊት ወደማያውቁት ስፍራ ያላቸውን ነገር ሁሉ ጥለው ወደግብፅ አንደሚሄዱ ሲነግራቸው ጥያቄዎች በሙሉ አሁን መልስ እንደሌላቸው ሲነግራቸው ነገሮች ምን ይመስሉ ይሆን?*

*ልጅ ሆኖ በፈርኦን ቤት ያሳለፈውም ነገር ወደሀሳቡ ይመጣል፡፡አሁን ሙሉ ሰው ሆኗል፡፡የሰማንያ አመት ሰው ነው፡፡ በምድያም አርባ አመት ተቀምጧል በምድረበዳ ውስጥ በጎች እየጠበቀ በህይወቱ ውስጥ እርጋታን ተለማምዷል፡፡እግዚአብሄርም ነገሮችን አስፍቶ የሚመለከትበትን ልምምድ እንዲሁም እድል ሰጥቶታል፡፡ግብፅ ውስጥ ባሉ ምርጥ አስተማሪዎች ተምሯል፡፡ዕብራዊ እንደሆነ እና የሱ ወገኖች በግብፅ ምንያህል በባርነት እየተሰቃዩ እና እየተጨቆኑ እንዳሉ አይቷል፡፡የእግዚአብሄርን ህዝቦች ወደተስፋቸው ምድር ሊመራ ባለበት ሀገር ኖሯል፡፡እንደ እረኛ በጎቹን በደንብ ተርድቷቸዋል፡፡ለምለም ሳር እና ቀዝቃዛ ውሀ የት እደሚያገኝ ያውቃል፡፡በህይወት ዘመኑ ሁሉ የተለማመደው ይህ ልምምድ እግዚአብሄር ለሰጠው ለዚህ ተልእኮ ወደፈርኦን ሄዶ “ እስራኤልን ከግብፅ ነፃ ሊያወጣ ነው፡፡*

***መልመጃ፡***

1. *ሙሴ ወደ ምድያም ሲመለስ ወደ ማን ነበር የሄደው* (*ቁጥር* 18) ?_______________
2. *ምን ነበር የጠየቀው?*____________________________________________________

3. በቁጥር 19 ላይ እግዚአብሄር ለሙሴ ምን አይነት መረጃ ሰጠው?________________

4. ሙሴ እና ቤተሰቡ ወደ ግብፅ መመለስ ጀመሩ።እግዚአብሄር እንዳዘዘው ሙሴ በእጁ ______________________________ይዞ ነበር (ቁጥር 20)

5. በመንገዱ ላይም እግዚአብሄር የሆነ ስፍራ ላይ ለሙሴ አንድ መመሪያ ሰጠው።ፈርኦን ምን እንደሚያደርግ እና ሙሴ ምን ማድረግ እንዳለበት አስቀድሞ መረጃ ሊሰጠው ፈልጓል።ቁጥር 21-23 ያለውን ክፍል አንብቡ።

   ሀ. ሙሴ ወደግብፅ ሲመለስ ምን ነበር የሚያደርገው?____________________

   ለ. ነገር ግን የፈርኦን ልብ ምን ሆነ?________________________________

   ሐ.እግዚአብሄር ሙሴ ለፈርኦን ምን እንዲለው ነገረው?_____________”እስራኤል__________ልጄ ነው ______ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልኩህ.....”

   መ. ነገር ግን ፈርኦን የእግዚአብሄር (የበኩር ልጅ) የሆነውን እስራኤልን አልለቅም አለ።ስለዚህ እግዚአብሄር ምን ሊያደርግ ነው?______________

   ____________________________________________________________

6. አሮን የሙሴ ታላቅ ወንድም ነው።እግዚአብሄር አሮንን ምን እንዲያደርግ መመሪያ ሰጠው (ዘፀአት 4፡27) ?______________________________________________

   ሀ. ወደ እግዚአብሄር ተራራ (ወደ ሲና ተራራ ) በመጓዝ ሙሴን አገኘው።ምን አይነት የሚገርም ቅልቅል ነው? ከተገናኙ ምን ያህል አመት ሆናቸው? ወደ አርባ አመት ያክል ይሆን?

   ለ. ሙሴ ከአሮን ጋር በመጋራት የሚያደርገው ምንድነው(ቁጥር 28)?

   - ________________________________________________
   - ________________________________________________

7. ሙሴ እና አሮን በጋራ ለእስራኤል ሽማግሌዎች ይናገሩ ነበር።

   ሀ. አፈጉባኤው ማን ነበር ?__________________________.(ቁጥር 30)

   ለ. ምን አይነት ምልክት አደረገ?________________________________

   ሐ. የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር(ቁጥር 31)?

   - ________________________________________________

- ________________________________________________
- ________________________________________________

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ አንዳንድ ግዜ ተልእኮ ሙሉ ኃላፊነት በእኔ ላይ ይመስለኝ እና በጣም እጨነቃለሁ፡፡እንዲረዳው እና እንዲያበረታታው ለሙሴ አሮንን አዘጋጀህለት፡፡ለእኔም እንዲሁ አደረክልኝ፡፡ለእኔም ቤተሰቦቼን ፣ጓደኞችን ፣እንዲሁም የቤተክርስቲያኔን ሰዎች በተለይ በጣም በተጨነኩበት እና እርዳታ በሚያስፈልገኝ ወቅት በተቸገርኩበት ግዜ እንዲረዱን እና እንዲያበረታቱኝ እነዚህን ሰዎች ስለሰጠኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡በእነሱ በኩል ወደእኔ መጥተሀል፡፡ህልውናህን በእነሱ አፅናኝ ቃል እና በመልካም ስራቸው ውስጥ ተመልክቼዋለሁ፡፡እባክህ እኔም በሰዎች ሀዘን እና ደስታ ግዜ ለሰዎች ድጋፍ እና ማበረታቻ አደርግ ዘንድ አስችለኝ፡፡ሁለት ወይንም ሶስት ሆነን በስምህ በተሰበሰብንበት እንደምትገኝ እናውቃለን፡፡________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# እኔ እግዚአብሄር ነኝ

## ዘፀአት 5-7- ከግብፅ ምድር አወጣችኋለሁ

---

**የትምህርት ሶስት ቅኝት**

**ቅኝት**

*መግቢያ*

ትምህርት 3፡ ዘፀአት 5-7

- ውጊያው ተጧጧፈ
- ገለባ የለም ነገር ግን ተጨማሪ ስራ
- ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ
- አሁን ትክክለኛው ግዜ ነው
- እወቁኝ
- የሙሴ እና የአሮን የትውልድ ዝርዝር

## መግቢያ

አንድ ሰው በተለይ የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲያስፈፅም ከተጠራ ህይወት ቀላል እንደሚሆንለት ሊያስብ ይችላል፡፡ለሙሴ እግዚአብሄር አንዲህ ነው ያው "ህዝቤን ነፃ ለማውጣት ልኬሀለሁ እና ሂድ" ይሁንና የእግዚአብሄርን ፈቃድ ነው እየፈፀማችሁ ያላችሁት፡፡ ከዛም ሙሴን እንዲህ ብሎ ማረጋገጫ ሰጠው "እኔ ካንተ ጋር እሆናለሁ" ፡፡ነገር ግን ሙሴ የእግዚአብሄር ጥሪ ቀላል እንዳልሆነ አውቋል፡፡ግብፃውያን የስራ ኃይላቸውን ለመልቀቅ ዝግጁዎች ናቸው? እስራኤላውያንስ ሙሴ ነፃ ሊያወጣቸው አንደተላከ አምነው ተቀብለውታል? በእርግጥ ሙሴ የእነሱ ነፃ አውጪ ነውን?

የተፈጠረው ነገር ማንም አንደሚያስበው እግዚአብሄር የተገለጠው እንደ አንድ ምትሀተኛ አይደለም፡፡ይልቁንም የሁሉንም ትኩረት አግኝቷል በፈርኦን እና በአስማተኞቹ ዘንድ፣ በእስራኤላውያን እና በሽማግሌዎቻቸው ዘንድ፣ እዲሁም በሙሴ እና በአሮን ዘንድ " እኔ ጌታ እግዚአብሄር ነኝ" ብሎ አውጇል፡፡ ሙሴን "ለፈርኦን እንደ አምላክ" ሲያደርገው ምን እንደተፈጠረ ተመልከቱ፡፡እግዚአብሄር ሙሴን እስራኤልን ነፃ ለማውጣት ከምድያም ካመጣው ጀምሮ እስራኤላውያን ህይወት ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ ከብዶባቸዋል፡፡

ነገር ግን እግዚአብሄር አልተሸነፈም፡፡ የእስራኤል ጀግና ነው ጠላቶቹንም ሊገጥም ተዘጋጅቷል፡፡ፈርኦንም በአልሸነፍ ባይነቱ አለ፡፡ እግዚአብሄርም ሊጠቀምበት የመረጠውን መሳሪያ ለሙሴ አስታጥቆታል፡፡ይህን መሳሪያ ለህዝቡ ምህረት ለፈርኦን እና ለሰራዊቱ ደግሞ ለፍርድ እዴት እንደተጠቀመበት ተመልከቱ፡፡

እግዚአብሄር ሁሉም ሰው እሱ እግዚአብሄር እንደሆነ እንዲያውቅ ፈልጓል፡፡እኛም ብንሆን ይህንን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡እንዳንዴ የእሱን ነፃ አውጪነት እና አዳኝነት እንድንመለከት እና እንድስብ ባሪያ ከሆንብት ነገር ነፃ ሊያወጡን የሚችሉ ሰዎችን ይልክልናል፡፡

**ክፍል 1**

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 5 አንብቡ

**ትምህርት፡** *ግዜው መጥቷል።ሙሴ እና አሮነ ፈርኦንን ፊት ለፊት አግኝተውታል። እነሱ በግላቸው የሚፈልጉትን ሰይሆነ የነገሩት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር ያዘዛቸውን ትእዛዝ ነው።ፈርኦን ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ እንኳን ፍላጎት አላሳየም።በትእቢት "ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፥ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅቅም አለ።" ፈርኦን እነዚህን ሰዎች ህዝቡን በከንቱ ስራ የሚያስፈቱ ተራ ሁከት አስነሺዎች አድርጓአዋል።*

*አሁን የውጊያው በስመር ተሰምሯል።ይህ ታላቅ ጦርነት ነው።እግዚአብሄር ከጨካኞቹ የግብፅ ገዢዎች ህዝቡን ሊያስለቅቅ ወጥቷል።በመጀመሪያ ሲታይ ፈርኦን እና ሙሴ ባላንጣዎች ይመስላሉ።*

1. *እውነታው ሲታይ የሚዋጉት ሁለቱ ኃይላት እነማን ናቸው?* ዘፍጥረት 3፡14-15 *ያለውን ክፍል ተመልከቱ*_____________________*እና*_____________________*ናቸው።*
2. *ከኤደን ገነት በኋላ የተለወጡ ነገሮች አሉ?*_________________________________*ለሰው ህይወት የሚደረግ ጦርነት።*

*ፈርኦን ለእግዚአብሄር እደማይታዘዝ ግልፅ ነው።ስለማያውቀው በእርግጠኝነት ሊታዘዘው አይገባም።ስለዚህ የላካቸውንም አምላክ እንዲሁም የተላኩትን አሮን እና ሙሴ የሚባሉትን መልእክተኞች ፈርኦን ከቁብ አልቆራቸውም።*

1. *ህዝቡ ወደ ምድረበዳ እንዲሄድ የተፈለገበት ምክንያት ምንድነው?*____________________
2. *እስራኤላውያን ወደምድረበዳ ካልሄዱ ምን እንደሚፈጠር ነው ለፈርኦን የነገሩት (ቀጥር* 3) *አንብቡ*__________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

**መልመጃ፡** የመጀመሪው ሙከራ አልተሳካም ጥሩ አይመስልም፡፡በቁጥር 4 እና 5 ላይ ፈርኦን ሀሳቡን ሊለወጥ አልቻለም ምክንያቱም ሙሴ እና አሮን ህዝቡን እንዲለቅ የሰጡት ምክንያት ለፈርኦን አሳማኝ አይደለም፡፡አሁን የበላይ የሆነ የሚመልሰው ማነው? የግብፅ ንጉስ ቀጥሎ ያደረገው ምን ነበር?

1. ፈርኦን ባሮቹን ለሚቆጣሩት ኃላፊዎች ምን አይነት ትእዛዝ አስተላለፈ (ቁጥር 6-7)?______________________________________________________________

   ________________________________________________________________

   ተቆጣጣሪዎችም እሰሪዎችን ከራሳቸው ከእስራኤላውያን መካከል መረጡ፡፡

2. የፈርኦን ትእዛዝ የስራ ሁኔታውን በምን መልኩ ለወጠው (ቀጥር 8)?______________________________________________________________

   ________________________________________________________________

3. ፈርኦን እስራኤላውያንን እንዴት ነበር ያሰባቸው? ምክንያታቸው በምድረበዳ ለእግዚአብሄር አምላካቸው መስዋእት ሊሰዉ አንደሆነ ሲያውቅ ምንድነው ያለው?_____

   ________________________________________________________________

4. የስራውን ኃይል ለመቆጣጠር የተጠቀመው ዘዴ ምን ነበር?______________________

   ________________________________________________________________

5. እስቲ በዚህም ዘመን ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ መቀጣት አንዳለባቸው የሚያምኑ ሰዎችንም አስቧቸው፡፡እስቲ በዚህም ዘመን ተመሳሳይ ጭቆና የሚካሄዱባቸው የምታውቋቸው ህዝቦች ካሉ ጠቁሙ፡፡ያንን የሚያደርጉት አንማን ናቸው?ሁኔታውስ ምን ይመስላል?__________________________________________________

   ________________________________________________________________

6. በቁጥር 10 ላይ የባሪያ ተቆጣጣሪዎቹ እና አሰሪዎቹ ለህዝቡ ምን ነበር ያሏቸው?__________________________________________________________

   ________________________________________________________________

   ገለባ የለም፡፡ስራውን ተጨማሪ ጡቦችን ስሩ፡፡ያ ሁኔታ እስራኤላውያንን ዝም የሚያሰኝ ሁኔታ አልነበረም፡፡ አሰሪዎቻቸው በቀኑ ሰርተው ማስረከብ ያለባቸውን እንዲሰሩ ያስጨንቋቸው ነበር በቀን ውስጥ መስራት የሚገባቸውን ካልሰሩ ምን ነበር የሚያደርጓቸው (ቁጥር 14)?________________________________________________

7. የእስራኤል ሽማግሌዎች ምን የሚል ጥያቄ ወደ ፈርኦን ይዘው ገብተው ጠየቁት (ቁጥር 15) ?____________________________________________

____________________________________________

8. ምላሹ ምን እንደሚሆን ይጠበቃል?____________________________

9. የፈርኦን ምላሽ ምን ነበር ?____________________________________

____________________________________________

10. ሀሳቡን በምንም መንገድ ቀይሮ ነበር____________________ገለባ ሳያቀርብላቸው የቀኑን ድርሻ እንዲያስረክቡ አስገደዳቸው፡፡

11. ለዚህ አይት ወቅት የተለያዩ አነጋገሮችን ልንጠቀም አንችላለን፡፡ እንደዚህ ልንል አንችላለን "ከድጡ ወደማጡ "የሚለውን አባባል ልንጠቀም አንችላለን፡፡ወይንም ደግሞ "የባሰ አታምጣ" የሚለውን አባባል ልንጠቀም አንችላለን፡፡ ይህንን ሁኔታ በተለያዩ አባባሎች ልንገልፃቸው አንችላለን ይሁን እንጂ እነዚህን ቃላት መጠቀማችን ችግራችንን አያቀልልንም፡፡በእስራኤል ላይ የተሾሙት አለቆች ይህ ነገር ተስፋ እንደሌለው አዩ፡፡ታዲያ የወሰኑት ውሳኔ ምን ነበር ቀጥር 19 ምን ይለናል?"____________

____________________________________________

12. አላወቃችሁም? በእስራኤል ላይ የተሾሙት አለቆች ከፈርኦን ጋር ያደረጉትን ንግግር ከጨረሱ በኋላ ማን ነበር የሚጠብቃቸው? (ቁጥር 20) ምን አይነት ሰላምታ ነው? ለሙሴ እና ለአሮን ምን አሏቸው (ቁጥር 20)?____________________

____________________________________________

13. ሁኔታው ጥሩ አይመስልም፡፡ሙሴ ምን አይነት እርምጃ ወሰደ (ቁጥር 22 )?________

____________________________________________

14. ሙሴም ስለህዝቡ ወደ እግዚአብሄር ፀለየ፡፡ የፀለየው ፀሎት ምን ነበር?__________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**ክፍል 2**

***መግቢያ፡*** *ነገሮች ጥሩ ጅማሬ አልነበራቸውም ።ከፈርኦን ጋር የነበራቸው ስብሰባ የተጠናቀቀው ፈርኦን ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጣቸው በቀደመው አቋሙ አንደፀና ነበር። ሰርተው ማስረከብ ካለባቸው ጡብ ምንም ሳያጎድሉ እንዲያስረክቡ በማዘዝ ለአምላካችሁም አውቅና አልሰጠውም በማለት ነበር ቁርጣቸውን የነገራቸው።የፈርኦን አለቆች ህዝቡ ሰርቶ ማስረከብ የነበረበትን ጡብ ሳያስረክብ ሲቀር በእስራኤል ላይ የተሾሙትን አሰሪዎች ይገርፏቸው ነበር በተለይ ደግሞ ፈርኦን ጋ ጥያቄ ይዘው መቅረባቸው ነገሩን አንዲብስ አድርጎታል።መፈፀም የሚገባቸው ግዳጅ ዛሬም ተመሳሳይ ነው።*

*በእስራኤል ላይ የተሾሙት አለቆችም በፈርኦን እና ሊገድሏቸው በሚፈልጉት የፈርኦን ሹሞች ፊት አፀያፊ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ሙሴ እና አሮንን ለእግዚብሄር ፍርድ አሳልፈው በመስጥ ይናገሯቸው ጀመር።*

***ገለፃ፡*** *እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? እስቲ እራሳችሁን በሙሴ ቦታ አስቀምጡ።በምድያም ምድረበዳ የአማታችሁም በጎች አሰማርታችሁ ስለራሳችሁ ኑሮ ታስቡ ነበር።በምድረበዳ ሳላችሁ የሚነድ፤ ነገር ግን የማይቃጠል ቁጥቋጦ ተመለከታችሁ በመገረምም ያንን ሁኔታ ልታዩ ሄዳችሁ።ከዛም ከሚነደው እሳት ውስጥ የእግዘአብሄር ድምፅ ወደግብፅ ሄዳችሁ ህዝቡን ነፃ እንድታወጡለት ነገራችሁ።ከዛም ወደ ቤት ተመለሳችሁ ለሚስታችሁ ነገራችሁ ወዲያውም ለጉዞ ተዘጋጃችሁ።ቤተሰባችሁንም ይዛችሁ እረጅም ጉዞ ወደግብፅ አደረጋችሁ።በመጀመሪያ ከእግዚአብሄር የሰማችሁት ነግራችኋቸው በደስታ የተቀበሏችሁን እና ከሀሳባችሁ ጋር የተስማሙትን አስራኤል ሽማግሌዎች አገኛችሁ።ከዛም ወደ ፈርኦን ገብታችሁ አናገራችሁት ነገር ግን ነገሩ እንደተጠበቀው አልነበረም።ከዚህም የተነሳ ህዝቡ በእናንተ መሪነት እምነት አጣ። ወደሌላ ስፍራ መሄድ አትችሉም ያላችሁ አማራጭ አንድ ነው እሱም በቁጥቀቋጦ ውስጥ በእሳት ወደተገለጠላችሁ አምላክ ብቻ ነው መሄድ የምትችሉት።ስለዚህ አሁን እስራኤላውያን ገለባ ሳይሰጣቸው ጡብ ያመርታሉ። አንተም ከዚህ በፊት አስበህ የማታውቀውን ነገር ግን ከቁጥቋጦ ውስጥ የጠተራህ አንድትኖር የፈለገውን ኑሮ ትኖራለህ።*

**ትግበራ፡** *ገለባ ሰያቀርብ ጡቦች አንዲሰሩለት ያዘዘውን ፈርኦንን ታሪክ አንብበናል።አንደሚታወቀው ህይወት አስቸጋሪ ናት።በርግጥ ህይወት የማይቻል መስሏል። የፈርኦንን መስፈርት ማሟላት የማይሞከር ነገር ሆኖባቸዋል።አንዳንድ ግዜ ገና በጣም የሚሰራ*

ስራ እያለ ቀድመን ጉልበታችንን ወይንም ኃይላችንን ጨርሰን እንገኛለን፡፡አንዳንዴ ደግሞ ብዙ ሰዎችን ማፅናናት እያለብን የዛን አይነት ፍላጎት ውስጣችን ሳይኖር ይቀራል፡፡አንዳንዴ ያልጨረስነው ብዙ ስራ እያለ ሰአቱ አልቆብን እናገኘዋለን፡፡አንዳንዴ ደግሞ ከአቅማቸን በላይ የሆነ ነገር ከእኛ እንደሚጠበቅ አናስባለን፡፡ ምናልባት ዛሬም ፈርኦንን መሰል ሰዎች ህይወታችሁን ተቆጣጥረው ከምትችሉት በላይ የሆነ ነገር ከእናንት የሚጠብቁ ሰዎች በህይወታችሁ ውስጥ ይኖሩ ይሆናል፡፡

1. እስቲ እናንተም በይወታችሁ ውስጥ ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ነገር እንድትሰሩ የተገደዳችሁበትን ግዜ አስታውሱ?____________________________________________
______________________________________________________________
2. የሚስፈልጋችሁ ነግር ግን የሌለ የሚመስላችሁ ነገረ ምንድ ነው?______________
3. በችግራችሁ ወቅት እርዳታ ፍለጋ የምትሄዱት የት ነው?_______________________
4. ሙሴ ወደ እግዚአብሄር ተመለሰ፡፡እግዚአብሄርንም እንዲህ ሲል ጠየቀው" ጌታ ሆይ ለምን…?.",ሙሴ ለነበረበት ሁኔታ የሰጠው ምላሽ እናንተን ምን ያህል ሊያበረታታችሁ ይችላል?__________________________________________________________
______________________________________________________________

**የምናሰላስለው፡** መዘሙር ፀሀፊው ዳዊት ተመሳሳይ ልምምድ ነበረው፡፡እስቲ የመዝሙር 86፡6-8 ያሉተን ቃሎች ቃል በቃል ፃፏቸው፡፡_____________________________________________
_____________________________________________________________________
_____________________________________________________________________

1. ዳዊት ወደ ጌታ በፀሎት ይቀርብ ነበር፡፡ስለእግዚአብሄር ያወቀው እና እውቅና የሰጠው ጉዳይ ምን ነበር?________________________________________________
______________________________________________________________
2. እግዚአብሄርን በቁጥር 6 ላይ ምን ጠየቀው?________________________________
3. ዳዊት ህይወቱን አሁን ላይ እንዴት ነበር የሚገነዘበው?______________________
4. ዳዊጥ "በችግሩ ቀን" መፍትሄ የሚያገኘው እንዴት ነበር?______________________
5. ለምንድነው እግዚአብሄርን መጥራት የመረጠው (ቁጥር 7)?_____________________

እነዚህ ቁጥሮች በሕይወታችን ውስጥ ችግር ሲገጥመን ተስፋ የሚሆነን ነገር ይሰጡናል፡፡እግዚእብሄር ፀሎታችንን እንደሚሰማን እና በችግራችን ግዜ ምህረት አስፈልጎን ስንጮህ እንደሚሰማን ማረጋገጫ ይሰጡናል፡፡ፀሎታችንን ሊመልስልን ቃል ገብቶልናል፡፡አሁንም መዝሙር 86፡ 6-8 ያለውን ክፍል በካርዳችሁ ላይ ፃፉት እና አጥኑት፡፡ችግር በሚገጥማችሁ ግዜ ይህንን ቃል አስታውሱ፡፡

**ፀሎት፡** እስቲ በህይወታችሁ ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እያለፋችሁ ያላችሁበትን ነገር ከጌታ ጋር ተነጋገሩ፡፡ልክ ሙሴ እግዚአብሄርን "ለምን "ብሎ በግልፅ እንደጠየቀው ማለት ነው፡፡የተስፋ መቁረጥ ጩኸት ሆኖ ሳለ የማይመለስበት ምክንያት ምን እንደሆነ ጠይቁ፡፡ስለዚህ የተስፋ መቁረጥ ጩኸታችሁን ወደሚሰማችሁ፣ወደ ሚረዳችሁ አንዲሁም በትክክል ወደሚመለከታችሁ እግዚአብሄር ጩሁ፡፡በህይወታችሁ ውስጥ እሱ እንደወደደ እና እንደፈለገ እንዲሰራ ፍቀዱለት፡፡________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

**ክፍል 3፡**

***መግቢያ፡*** ሙሴ እና እስራኤላውያን የነበሩበትን አስቸጋሪ ሁኔታ እና ተስፋ መቁረጥ ተመልክተናል፡፡ውጥረቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም ፡፡ሙሴ እግዚብሄርን እንዲህ አለው "እኔን ጠርተህ ያመጣኸኝ በዚህ ህዝብ ላይ መከራ አንድጨምርበት ነውን ?" ነገር ግን አሁንም ሙሴ ወደፈርኦን በመሄድ እግዚአብሄር አንደተናገረው አደረገ የፈርኦን ምላሽ ግን አሁንም የእስራኤላውያንን መከራ ማብዛት ነው፡፡የፈርኦን መደምደሚያ አረፍተ ነገር " ቁርጥህን እወቅ ይህን ህዝብ ነፃ ማውጣት አትችልም " የሚል ነበር፡፡

ይህ በጣም ወሳኝ ግዜ ነው፡፡ሙሴን ጨምሮ የሁሉም አይኖች እግዚአብሄር ላይ ናቸው፡፡ህዝቡ ከፈርኦን የባርነት አገዛዝ እንደማይለቀቁ አውቀዋል ምክንያቱም ሽማግሌዎቻቸው በባርነቱ ሀሳብ ተስማምተዋልና ነው፡፡ሙሴ ከእግዚአብሄር የተሰጠውን መልእክት በመናገር ችሎታው ግሩም የሆነውን አሮንንም ይዞ ወደ ፈርኦን ቢገባም እንኳን አስራኤላውያን እንደማይለቀቁ እርግጠኛ ሆነዋል፡፡ፈርኦን እንዲለቀቁ ስላልፈቀደ እንደማይለቀቁ አረጋግጠዋል፡፡ነገር ግን መለቀቃቸው

አይቀሬ ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር እንዲለቀቁ አዟልና ክብሩን ማንም እንዲሻማው ስለማይገባ በራሱ ክንድ ሊያወጣቸው ወስኗል፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 6፡1-12 ያለውን ክፍል አንብቡ፡፡

**ትምህርት፡** እግዚአብሄር ለሙሴ መለሰለት፡፡በእግዚአብሄር ድምፅ ውስጥ አስደሳች የሆነ ነገር ይሰማችኋል፡፡እስራኤልን ነፃ ለማውጣት የገዓንበት ግዜው እንደደረሰ ያወቀ የመሆኑ ስሜት ይሰማችኋል፡፡በዚህ በባእድ ምድር ውስጥ ጥበቃ እና የሚያስፈልጉትን ነገር እያሟላለቸው አስራሁለት የነበሩት የእስራኤል ልጆች አሁን ታላቅ ህዝብ ሆነዋል፡፡እግዚአብሄር የሰጣቸውን ምድር ለመውረስ እንደዚህ መብዛታቸው ያስፈልጋል፡፡አሁን እግዚአብሄር የሁሉንም ትኩረት አግኝቷል ሁሉም ከእግዚአብሄር ውጪ አዳኝ እንደሌለ አውቀዋል፡፡ህዝቡም በራሳቸው ፈርኦንን ሊያሸንፉ እንደማይችሉ አውቀዋል፡፡

**መልመጃ፡** በዘፀአት 6 ላይ አሁን አግዚአብሄር "አሁን" የሚል አስገዳጅ እና ህይለኛ ቃላ መጠቀም ጀመረ፡፡አሁን ትክክለኛው ግዜ ነው፡፡ሁሉም ነገር ስፍራውን ይዟል፡፡ ለእነሱም እንዲህ አላቸው አሁን መሪው እኔ ነኝ ስለዚህ በስራ የምገለጥበት ግዜ ነው፡፡" ከመጀመሪያው እግዚአብሄር በታላቅ ክንድ ተገልጦ ፈርኦንን ህዙቡን አንዲለቅ እንደሚያደርገው ግልፅ እንዲሆን አድርጓል (ቁጥር1)፡፡

1. አሁንም በድጋሚ እግዚአብሄር ማን አንደሆነ ለሙሴ በድጋሚ ነግሮታል፡፡ሙሴን ጨምሮ ህዝቡ ስለእግዚአብሄር ምን እንዲያውቅ ነው የፈለገው?

   ሀ. ቁጥር 2፡________________________________________

   ለ. ቁጥር 3፡ _______________________________________

*ማስታወሻ፡ ቁጥር 3 ስለእግዚአብሄር ስም ይናገራል ፡፡ለአብርሀም ፣ለይስሀቅ፣ለያእቆብ እራሱን ሁሉን የሚችል አምላክ ወይንም ኤል ሻዳይ (የዕብራይስጥ ቃል ነው) ብሎ ግልጧል፡፡ነገር ግን በዚህ ቁጥር ውስጥ እንደተገለፀው ለእነሱ በዚህ መልኩ አልተገለጠም፡፡ጌታ (ያህዌ)የሚለው ቃል የግል አምላክ፣ ለህዝቡ ቅርብ ሁሉን የሚያደርግ እና የሚሆን ነው፡፡ይህንን እውነት የሚገልፀው ስም እግዚአብሄር ለሙሴ በዘፀአት 3፡13-15 ላይ የሰጠው ሲሆን ቃሉም ከላይ የተተቀሰው ያህዌ የሚለው ነው፡፡*

2. እግዚአበሄር ለእነዚህ ሰዎች ቃል እንደገባላቸው አስታወሳቸው ያም ቃል ____________እና___________ቁጥር 4፡፡በጣም የሚገርመው ወደገዛ ምድራቸው ሲመጡ በመጀመሪ አንደ እንግዳ ነው የተቀመጡት፡፡
3. ከዛም አንዲህ አላቸው "____________________እሰጣቸው ዘንድ______________ ጋር ____________________________አቆምሁ፡፡ደግሞ እኔ________________ የእስራኤልን ልጆች _____________________________ሰማሁ __________________________፡፡"

**ትምህርት፡** ይህ ሁሉ ግዜ ካለፈ በኂላ እና ይህ ሁሉ ትውልድ ካለፈ በኂላ እግዚአብሄር ከአብርሀም ጋር ያደረገውን ቃልኪዳን አሰበ፡፡ይህንን ቃልኪዳን የሚያስታውስ ሰው በህይወት የለም፡፡ስለዚህ ቃልኪዳን ሊጠይቀው የሚደፍር ለው የለም፡፡ነገር ግን እሱ ታማኝ ነው፡፡ቃሉም ለዘላለም ፀንቶ ይኖራል፡፡ለአብርሀም፣ ለይስሀቅ፣ ለያዕቆብ የተናገረውን ቃል ዛሬም ድረስ አልዘነጋውም፡፡ተስፋ የተገባላቸው በሰላም አርፈዋል ፡፡በርግጥ ለአብርሀም ከብዙ መቶ አመታት በፊት እደተናገረው ቃል በቃል አልተፈፀመም ?

1. ዘፍጥረት 15፡13-14 አንብቡ ፡፡ይህ ክፍል ስለምንድነው የሚነግረን ?______________
_________________________________________________________________________
2. እስቲ ያዕቆብን በቤቴል ምን አንዳለው አስታውሱ ዘፍርረት28፡13-15 አንብቡ ይህ ክፍል ስለምንድነው የሚነግረን ?____________________________________________
_________________________________________________________________________

ስለእግዚአብሄር የተማርነው (ዘፀአት 6)፡፡ እግዚአብሄር ሙሴን እሱ ማን እንደሆነ እና ቃልኪዳኑንም ምን አንደሆነ እንዲነግራቸው ላከው፡፡

1. በቁጥር 6 መሰረት እግዚአብሄር ስለእርሱ ምንድነው አንዲረዱ የፈለገው?___________
2. ሌላው እሱ አንዲያውቁ የፈለገው ነገር እሱ ጌታ  አንደሆነ ነው፡፡
   ሀ. ቁጥር 6፡ አመጣለሁ________________________________________________
   ለ. ቁጥር 6፡ ነፃ አወጣለሁ_____________________________________________
   ሐ. ቁጥር 6፡ እታደጋለሁ_______________________________________________
   መ. ቁጥር 7፡ እወስዳለሁ_______________________________________________
   ሠ. ቁጥር 7 ፡ አሆናለሁ_______________________________________________
   ረ. ቁጥር 8፡ አመጣለሁ________________________________________________

ሰ. ቁጥር 8፡ እሰጣለሁ ______________________________________________

ያጠቃለለው የሚከተለውን ቃል በመድገም ነው "_____________________________"

**ገለፃ፡** እስቲ ጥቂት ግዜ ውሰዱ እና ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ ሊነግራቸው ያለውን ነገር አስቡ፡፡እሱ ጌታ ስለሆነ ለወደደው ህዝብ ሁሉንም ነገር ያደርጋል፡፡ከዚህ የዘለለ ነገር ፈልገዋል ? እግዚአብሄር በመልካም ሁኔታ ምድርን በሙሉ ተስፋ ሰጥቷቸዋል፡፡በቁጥር 7 ላይ እርሱ አምላካቸው ሊሆን ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ ሙሴ እና አሮን እግዚአብሄር የነገራቸውን በሙሉ ለእስራኤላውያን ሲነግሩ ምንያህል ደስታ እንደሚሳማቸው አስቡ፡፡ሲነግሯቸው ሄዱ በቁጥር 9 ላይ እንዴት እንደነገሯቸው ነበር የተነገረን?_________________________________________

_____________________________________________________________________________

ልትነቅፏቸው ትችላላችሁ?ምክንያቱም አሮን እና ሙሴ ከሚነግሯቸው ነገሮች ውስጥ አነሱን የሚያስደንቃቸው ነገር የለም፡፡በአሮን እና በሙሴ ተስፋ ቆርጠዋል፡፡እናንተስ በህይወታችሁ ውስጥ መልካም የሆኑ የሚያፅናኑ እና የሚያበረታቱ ቃላትን ለመስማት የተቸገራችሁበትን ግዜ ታስታውሳላችሁ? ተስፋ መቁረጥ ማለት ተስፋ ሆኖ ወደፊት የሚያስኬድ ነገር ማጣት ማለት ነው፡፡ተስፋ መቁረጥ ነገሮችን በድፍረት እንዳንሰራቸው ያደርገናል፡፡ ተስፋ መቁረጥ እለት በእለት መስራት የምንችልበትን ኃይል ያቃጥልብናል፡፡

1. ከተስፋ መቁረጥ ጋር የተያያዘ ነገር ገጥሞአችሁ ያውቃል ?__________________

   ________________________________________________________________

2. እስቲ ተስፋ ለመቁረጥ ምክንያት የሆኗችሁን ሁለት ምክንያቶችን ጥቀሱ ? _____

   ________________________________________________________________

3. ተስፋ ለቆረጣችሁበት ሁኔታ ምን አይነት ምላሽ ነው የሰጣችሁት ?___________

   ________________________________________________________________

4. በዛ ሁኔታ ውስጥ ሆናችሁ ተስፋ ሊሰጧችሁ የሞከሩ አነማን ናቸው ?___________

   ________________________________________________________________

5. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማበረታታቻ መስማት ይከብዳል ?__________________

**ፀሎት**፡ጌታ ሆይ አንዳንድ ግዜ ለመፅናናት እቸገራለሁ።ህይወቴ ስትወርድ ሁሉም ነገር አስቸጋሪ ይሆንብኛል።እባክህ በእነዚህ ግዜያት ያንተን የማበረታቻ ቃል እንድሰማ አድርገኝ።ተስፋህን ተቀብዬ የምንዝበትን ኃይል ስጠኝ።ተስፋ የምትሰጠኝን አንተን እንዳምንህ እርዳኝ።_______________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## ክፍል 4

**መልመጃ፡** (ዘፀአት 6 ቀጠልን)፡ ነገር ግን የእግዚአብሄር እስራኤላውያንን ነፃ የማውጣቱ ነገር በእነሱ ማመን አለማመን ፣መልእክቱን መቀበል አለመቀበል ፣ለተስፋው ብርታት መኖር አለመኖር ጋር የተያያዘ አይደለም።

1. በቁጥር 11 ላይ ጌታ ለሙሴ ያዘዘው ነገር ምን ነበር?_________________________
2. ሙሴስ ለዚህ ሁኔታ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር ?___________________________
3. በእርግጥ በጣም ብዙ መከራ እና ቸግር ያሳለፈ እንደምናውቀውም ለሁኔታዎች ያንገራገረ ሰው ነበር።ነገር ግን እግዚአብሄር ከዚህ በፊት ለሚያውቀው እና የላከውን አምላክ አላውቀውም ትእዛዙንም አልፈፅምም ብሎ ወደመለሰለት ንጉስ እግዚአብሄር መልሶ የላከው ሰው ነው።ፈርኦን ለመጀሪያ ግዜ ገለባውን ከለከለ ።በዚህ ሁኔታ ውስጥ ይህ እስራኤላውያን የጠሉት መልእክተኛ ምን ማድረግ ይችላል?እግዚብሄርን የሚያውቀው የእስራኤል ህዝብ እግዚብሄርን አልሰማም ካለ እግዚአብሄርን የሚያውቀው ፈርኦንማ እንዴት?________________________________________

   _____________________________________________________________

**ትምህርት፡** አሁን የድርጊት መቋረጥ አንመለከታለን።ምንም ምክንያት ቢኖር ታሪከ ይቀየሳል።በዘፀአት 6፡13-27 ላይ የእስራኤላውያንን ቤተሰብ ከፊል የትውልድ ዝርዝር አናገኛለን። የተጠቀሱትም የቤተሰብ መሪዎች ስም ዝርዝርም የተጠቀሱት ከሮቤል፣ስምኦን፣እዲሁም ከሌዊ ወገን ነው።እነዚህ ስሞች ብቻ የመጠቀሳቸው ምክንያት እርግጠኛ ሆነን መናግር ባንችልም ነገር ግን አንድ ነገር መገመት አንችላለን።በዚህ በቁጥር 20 ላይ በሚገኘው ስምዝርዝር መካከል ላይ የሙሴን እና የአሮንን የዘር መስመር እናገኛለን።

1. ስለ አምበረም አባት የተነገረን ነገር ምንድነው ቁጥር 20? ማንን ነው ያገባው?ዮካብድ እና አምበረም የሚገናኙት በምንድነው?____________________________________

   ________________________________________________________________

2. አምበረም አክስቱን አገባ፡፡ሁለት ልጆች ወልደዋል ስማቸው ____________________እና ___________________________________ይባሉ፡፡
3. የዘር ግንድ የሚቆጠረው በወንዶች በመሆኑ ምክንያት ያልተጠቀሰች አንዲት ሴት ልጅም አለቻቸው፡፡ዘሁልቁ ምእራፍ 26፡59 አስታውሱ እና በዛውስጥ ሶስት እህት እና ወንድማማቾች ተገልፀዋል፡፡የእታቸው ስም ማን ይባላል?___________________________

**ገለፃ ፡** ይህ የትውልድ ዝርዝር የተፃፈበት ምክንያት እነዚህ ወንድማማቾች እና እህታቸው ከሌዊ ወገን አንደሆኑ ለማሳየት ሲሆን በቁጥር 26 እና 27 በተመሳሳይ መልኩ ህዝቤን እስራኤልን ነፃ አውጡልኝ የተባሉትም አሮን እና ሙሴም በዚሁ የዘር ግንድ ውስጥ ተገልፀዋል፡፡እነዚሁ ሰዎች ናቸው የግብፁ ንጉስ ፈርኦን ጋ ገብተው ህዝቤን እስራኤልን ልቀቅ ይልሀል ብለው የነገሩትለ፡፡ የዚህ ቤተሰብ መዝገብ ይህንን አውነት ያረጋግጥልናል፡፡

እንደምናውቀው የመፅሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ መፃሕፍት የሆኑትን አምስቱን የህግ መፃህፍት የፃፈው ሙሴ ነው፡፡ሙሴ የአግዚአብሄርን ህዝብ ከግብፅ ሊያወጣ እንደተጠራ በታሪክ መመዝገቡ ለሙሴ የሚጠቅመው ነገር ይኖር ይሆን? ሌሎች ሰዎችስ ይህንን ታሪክ ማወቃቸው እና ይህ የዘር ሀረግ እነሙሴ እንደሆኑ ማረጋገጡ ለሌሎች ሰዎች የሚጠቅማቸው ነገር ይኖራል? ምክንያቱን ለመናገር እርግጠኛ መሆን ባንችልም መረጃው ግልፅ ነው፡፡

**ከባድ ጥያቄ፡** እስራኤላውያንን ከፈርኦን እጅ ለማዳን ወይንም፣ እብራዊያንን ነፃ ለማውጣት ዕብራዊ ሰው ያስፈልጋል ብላችሁ ታስባላችሁ?መልሳችሁ አዎ ከሆነ ለምን ?አይደለምም ከሆነ ለምን?____________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

__________________________________________________________________

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 7 አንብቡ

***መልመጃ፡*** በዘፀአት 5፡1-2) ባለው ክፍል ላይ ለመጀመሪያ ግዜ አሮን እና ሙሴ ወደ ፈርኦን ቤት ሲሄዱ ቃል ብቻ በቂ አልነበረም፡፡ነገር ግን እግዚአብሄር ለሙሴ ይሆናሉ ያለው ነገር በሙሉ እየሆነ ተአምራቶችም ቀጠሉ፡፡

1. በዘፍጥረት 6፡30 የትውልድ ሀረግ ዝርዝር ውስጥ ቁጥር 12 ላይ ስንጀምር ተመሳሳይ ቃል ነው የምናገኘው፡፡ቁጥር አስራሁለት እንዴት ነው የሚያልቀው? በቁጥር 30 ሙሴ የጠየቀው ተመሳሳይ ጥያቄ ምንደነው?________________________________________

   ______________________________________________________________________

2. እግዚአብሄር በርግጥ አንድ ነገር ማብራራት አለበት፡፡በቁጥር 7፡1 ላይ እግዚአብሄር ለሙሴ የነገረው ነገር ምንድነው?________________________________________

   ________________________________________________________________ፈርኦን ሙሴን እንደ አምላክ እንዲቆጥረው እግዚአብሄር በፈርኦን ላይ ፍርሀትን፣ድንጋጤ፣እንዲሁም ፣አክብሮትን ሊያደርግ ነው፡፡ግብፃውያን ብዙ አማልክቶች ቢኖሯቸውም ዛሬ ግን ከአማልክት አምላክ ከእግዚአብሄር በድንቅ እና በተአምራት ተግዳሮት ሊገጥማቸው ነው፡፡

3. ሙሴ በእግዚአብሄር የታዘዘውን ትእዛዝ በሙሉ አድርጓል፡፡አሮን እና ሙሴ በመጀመሪያ የታዘዙት ነገር ምንድነው (ቁጥር 2) ?________________________________________

   ______________________________________________________________________

4. እግዚአብሄር ፈርኦን ምን እንደሚሆንበት ተናገረ፡፡

   ሀ. ቁጥር 3፡ "እኔም የፈርዖንን ________________________________________÷"

   ለ.ቁጥር 34 "በግብፅ ምድርም__________ እና______________አበዛለሁ፡፡ፈርዖንም __________________÷ ________________በግብፅ ላይ አደርጋለሁ÷ __________________የእስራኤልን ልጆች ሕዝቤን በታላቅ ፍርድ ከግብፅ አገር አወጣለሁ፡፡

   ሐ. ቁጥር 4፡ እግዚአብሄርም እጁን በግብፅ ላይ ያደርጋል ሰራዊቱንም ____________________በታላቅ____________________፡፡

   ሰራዊቶቹ እነማናቸው?______________________________________________

   መ. ቁጥር 5፡ በውጤቱም ግብፃውያን ምን ያውቃሉ?_________________________

5. ሙሴ እና አሮን እግዚአብሄርን ታዘዙ ልክ እግዚአብሄር እንደነገራቸው አደረጉ።ለመሆኑ ሙሴ ስንት አመቱ ነበር?______________አሮንስ ስንት አመቱ ነበር?_____________

## ክፍል 5

**ትምህርት፡** እግዚአብሄር አሮን እንና ሙሴን በጥንቃቄ የመራበትን መንገድ ስንመለከት በጣም ያስደስታል።እግዚአብሄር ቀጥሎ ሊሆን ያለውን ነገር እየቀደመ ስለመሚነግራቸው ነገሮች ሲከሰቱ አይገርማቸውም ነበር።እንደገናም ምን መስራት እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጣቸው ነበር።ይህ የአመራር ክህሎት 101 ይመስላል ።በመንገዳቸው ሁሉ እግዚአብሄር ይከታተላቸው ነበር።ይህን ሁሉ ስራ እየሰጣቸው ትቷቸው አይሄድም ነበር በሁሉ ነገር አብሯቸው ነበር።ሁሉም ነገር ስፍራ ስፍራውን ሲይዝ እግዚአብሄር ስራውን ጀመረ።

**መልመጃ፡**

1. ፈርኦን ተአምራት እንዲያደርጉ ጠየቃቸው።ለሙሴ እና ለአሮን እግዚአብሄር የሰጣቸው መመሪያ ምን ነበር ቁጥር 9 ?______________________________________
2. ቀላል ነገር ይመስላል፤ስለዚህ ወደፈርኦን ሄደው ልክ እግዚአብሄር አንዳቸው ይሆን ነበር።በርግጥ የሚሆነው አንዳላቸው ነበር? በቁጥር 11 እና 12 ላይ ምን ተነግሮናል?______________________________________
3. ነገር ግን ምን ተከናወነ?______________________________________
4. ይህኛው የታሪክ ክፍል በጣም አሳዛኝ ፍፃሜ ነው ያለው።ቁጥር 13 የልብ መመርመሪያ መሳሪያ ነው የሚመስለው የፈርኦን ልብ ጥሩ አልነበረም።ከዚህ የምንማረው ምንድነው?______________________________________
5. በዚህ ቁጥር መሰረት የፈርኦንን ልብ የደነደነው ምን ነበር?______________________
______________________________________

**መደምደሚያ፡** ወደ ትምህርት ሶስት መደምደሚያ መጥተናል ።ትምህርት ክፍል 4 እግዚአብሄር ህዝቡን ከግብፅ ባርነት ነፃ የሚያወጣበት ታሪክ ለአፍታ ያቆማል።ፃድቅ ለሆነው አላማው አግዘአብሄር በኃይሉ ሙሴን እና አሮንን ሲጠቀምባቸው እንመለከታለን።ሙሴ በእጁ ያለውን ዘንግ ሲዘረጋ አግዚአብሄር ደግሞ ለህዝቡ ምህረት ሲያደርግ እና ሲራራ እንመለከታለን።

ትምህርት 1 እና 2 መድረኩን ሲያዘጋጁ አንመለከታለን፡፡በታሪኩ ውስጥ መሪ ተዋናዮችን ማን እንደሆኑ አውቀናል፡፡እግዚአብሄር ሙሴን በሚነደው ቁጥቋጦውስጥ ተገልጦ ሲጠራው እና “ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ ፡፡” ሲለው አብረን ታሪኩን ተከታትለናል፡፡አንዳንድ ግዜ እኛም ለእኛ ለራሳችን የሚገለጥ የሚነድ ቁጥቋጦ እንዲኖረን እንዲሁም የራሳችን የተቀደሰ ምድር አንዲኖረን እንመኛለን፡፡ልክ እንደ ሙሴ በስማችን ጥርት ባለው ድምፁ ጠርቶን ተልእኮአችንን በግልፅ ቢነግረን እንወዳለን፡፡

ሁላቸንም በልባችን ቁጥቋጦ ውስጥ የሚነድ እሳት አለን እሱም የእግዚአብሄር ቃል ነው፡፡በሉቃስ 24፡32 ላይ ሁለት የእየሱስ ደቀመዛሙርት ከእየሱስ ሞት ጋር በተያያዘ በመንገድ ዝለው እየተነጋገሩ ይሄዱ ነበር፡፡የሚነጋገሩት ስለ ምን ነበር? ___________________________

_______________________________________________________________________________

ወደ እግዚአብሄር ህልውና የመግባት እና በቅድስናው ስፍራ የመቆም መብት አለን፡፡ወደ ህልውናው የምንመጣው በፀሎት ፣በዝማሬ እና በቅኔ፣በምስጋና እና በአምልኮ ወደ እሱ ስንቀርብ ነው፡፡የፈርኦን ልብ የደነደነው እግዘኢአብሄር ማን አንደሆነ ስላላወቀው ነው፡፡በተጨማሪም እሱንም መስማት ሆነ በመልአክተኞቹ በአሮን እና በሙሴ በኩል የመጣለትን መልእክት አልተቀበለም ነበር፡፡ እግዚአብሄር በቃሉ በኩል ሲናገረን ድምፁን የመስማት መብት አለን፡፡

**ፀሎት፡** ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ ከሙሴ እና ከአሮነ ጋር አንደ ነበርክ አንዲሁም ከእኔም ጋር አለህ፡፡ እውነት የሆነውን ቃልህን እሰማ አና እታዘዘው ዘንድ ወደህልውናህም እቀርብ ዘንድ ትፈልጋለህ፡፡ክፍት እና አንተን የሚቀበል ልብ ስጠኝ ፡፡የተናገርከውን ሁሉ የሚያምን ልብ ስጠኝ፡፡በክርስቶስ እየሱስ ለገለጥክልኝ ፍቅርህ ምላሽ ለመስጠት የሚኅኅልብ ስጠኝ፡፡በተለይ ደግሞ በዚህ ቀን የምለምንህ_____________________________________________

_______________________________________________________________________________

# ትምህርት አራት

# እጅህን ዘርጋ

## ዘፀአት 7-8- ልቡን አደነደነ

---

የትምህርት አራት ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4፡ ዘፀአት 7- 8

- የፈርኦን የማይታዘዝ ልብ
- ከእግዚአብሄር ጋር አብሮ ሰራተኞች
- የኃጉንቸር መቅሰፍት
- የእግዚአብሄር የልብ ምት
- የእግዚአብሄር ጣት
- የተለዩ ህዝቦች
- ባለአላማ ህዝቦች

## መግቢያ

ውጥረቱ ተጠናክሯል ፡፡ፈርኦን የእግዚአብሄርን ህዝብ አልለቅም ብሏል ፡፡እግዘኢብሄርም ደግሞ ቅዱስ የሆነውን አላማውን ለማስፈፀም አንና ለ አብርሀም እና ለዘሩ የገባውን ተስፋ ለመፈፀም በትጋት እየተንቀሳቀሰ ነበር፡፡ "እግዚአብሔርም አለ፦ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈስሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ አሞራውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ስፍራ አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ፡፡" እግዚአብሄርን ይህንን ተስፋውን ከመፈፀም የፈርኦንም አለመታዘዝም ሆነ ሌላ ምንም አይነት ነገር አያግደውም፡፡

የማይለወጠውን ታሪክ አና የጦር ሜዳውን ተመልከቱ፡፡የሚዋጉት ማን እና ማን ናቸው? ከባርነት ነፃ ለመውጣት የእስራኤላውያን ድርሻ ምን ነበር ?የእነሱስ ጠበቃ ማን ነበር? እግዚአብሄርስ ጠላቶቹን ለማጥቃት የተጠቀመበት ሀይል ምን ነበር? የእግዚአብሄርን ለህዝቡ ያለውን የርህራሄ ልብ ተመልከቱ፡፡

ሙሴ በትሩን ያዘ እግዚብሄር ደግሞ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ስለ እስራኤል ነፃ መውጣት እግዚአብሄር የሰጠው ትእዛዝ ምን ነበር? ስታጠኑ እስቲ አስተሳሰባችሁን ተጠቀሙ፡፡ታሪኩ ውስጥ ገብታችሁ እግዚአብሄር ህዝቡን ነፃ ለማውጣት የተጠቀመባቸውን የተለያዩ መንገዶች አጥኗቸው፡፡

እሱ ጌታ ነው ማለት ለእስራኤላውያን ምን ማለት ነው? የአኗኗራቸው ሁኔታ የሚፈጥረው ነገር ምንድነው?እንደማንኛውም ህዝብ አይደሉም፡፡በእግዚአብሄር እና ለእግዚአብሄር የተለዮ ህዝቦች ናቸው፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ ይህን ጥያቄ ጠይቁ "እግዚአብሄርን ላገለግለው በእግዚአብሄር ተመርጫለሁ ማለት ለእኔ ምን ማለት ነው?

**ክፍል 1**

***መግቢያ*** **:** *ትምህርት ሶስትን ሙሴ እና አሮን በፈርኦን ፊት ከፈርኦን ጠንቋዮ እና መተተኞች ጋር ሆነው ነበር ያጠናቀቅነው፡፡የአሮን በትር ወደ እባብነት ተቀይሮ ነበር፡፡የአስማተኞቹም በትር ወደእባብነት ቢቀየርም የአሮን በትር ግን የስማተኞቹን እባብ ዋጠቻቸው፡፡እነዚህ ሁሉ ተአምራቶች ይደረጉ አንጂ የፈርኦን ልብ ግን አሁንም እንደደነደነ ነው ያለው እግዚአብሄርን ሊሰማ አልቻለም፡፡*

*ይህ ክፍል አስሩን መቅሰፍቶች ያሳየናል፡፡ብዙዎች እነዚህን መቅሰፍቶች እንደተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሊያይዋቸው ይፈልጋሉ፡፡ለምሳለሌ በየአመቱ የአባይ ውሀ እየሞላ የተለያዩ ማእድናትን ይዞ ይመጣል፡፡እነዚህ መአድናት የአባይን ውሀ ቀለሙን ወደ ቀይነት ይለውጡታል ብለው ይናገራሉ፡፡ሌላው ደግሞ የግብጽ ምድር በየአመቱ በአንበጣ መንጋ መወረሩ እና ሰብል ማጥፋታቸው የተለመደ ነገር ነው ብለው ይናገራሉ፡፡እንዲህ እያሉ ለአስሩም ተአምራቶች ምክንያት ያቀርባሉ፡፡ይሁን እንጂ እነዚን ተአምራቶች እግዚአብሄር እንደሌሎቹ የግብፃውያን አማልክት አንዳልሆነ ሊያሳይ ያደረገው ተአምር ነው፡፡ይሀ የጥናት ክፍል ስለ እስራኤል እና ስለግብፅ ታሪክ ያስተምረናል ፡፡የአብርሀም ፣የይስሀቅ፣የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሄር ህዝቡን በፀናች እጅ ከግብፅባርነት ነፃ አንዳወጣቸው በፈርኦን የታሪክ መዛግብት ላይ ተዘግቦ ይገኛል፡፡*

**የቤት ስራ፡** *እግዚአብሄር በግብፃውያን ላይ ያደረጋችው አስር ተአምራቶች በዘፀአት ምዕራፍ* 7፡14 *አስከ* 11፡10 *ድረስ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ይህንን ምዕራፍ በጥሩ ሁኔታ አጥኑት፡፡ስለእነዚህ መቅሰፍቶች በሰፊው አንመለከታለን ነገር ግን ከታች የተጠቀሰውን ሳጥን በውስጡ የተጠቀሱትን ክፍሎች በማየት በዛክፍል ላይ የተጠቀሱትን መቅሰፍቶች ፃፏቸው፡፡*

| ጥቅሶች | የመቅሰፍቶቹ አይነቶች |
|---|---|
| **ዘፀአት 7:14-24** | |
| **ዘፀአት 8:1-15** | |
| **ዘፀአት8:16-19** | |

| | |
|---|---|
| ዘፀአት 8:20-32 | |
| ዘፀአት 9:1-7 | |
| ዘፀአት 9:8-12 | |
| ዘፀአት 9:13-35 | |
| ዘፀአት10:1-20 | |
| ዘፀአት 10:21-29 | |
| ዘፀአት1:1-10 | |

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 7፡14-24 ያለውን ክፍል አንብቡ

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር 14 ላይ እግዚአብሄር ለሙሴ የፈርኦን ልብ____________________እንደሆነ እና ፈርኦን ህዝቡን__________________________ነግሮታል፡፡
2. በቁጥር 15 ለይ እግዘአብሄር ለሙሴ የሰጠው መመሪያ ምን ነበር?________________

   ____________________________________________________________

   የአባይ ወንዝ አንዱ የግብፅ ጣኦት ነው፡፡ እግዚአብሄር ለሙሴ እንዲጠቀምበት ከሰጠው በትር ጋር በወንዙ ዳር ነበር ፈርኦንን ያገኘው፡፡በዘፍጥረት 7፡1 ላይ እግዚአብሄር ሙሴን ለፈርኦን አንደ አምላክ አንዳደረገው ተመልክተናል፡፡ይህ ስፍራ የግብፃውያን አማልክት እና የእስራኤል አምላክ የሚፋለሙበት ስፍራ ነው የሆነው፡፡
3. በቁጥር 16 ላይ እንደሚናገረው አስከዚህ ግዜ ድረስ ፈርኦን ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ሙሴ እዲህ አለ እግዚአብሄር አንዲህ ይልሀል "በዚህ እኔ እግዚአብሄር አንደሆንደኩ ታውቃለህ….." በቁጥር 17 ላይ ሙሴ ቀጥሎ ምን ሊያደርግ አንዳለ ነው የሚናገረው?__________________________________________________

   ____________________________________________________________
4. ቁጥር 18 ላይ ያስከተለው ነገር ምን ነበር?________________________________እና

   ____________________________________________________________
5. በቁጥር 15 ላይ የእግዚአብሄር ቅጣት ምን ያህል ከባድ አንደሆነ ነው የምናየው፡፡የእግዚአብሄር በትርም ተዘረጋች የአባይን ውሀ መታች ፡፡በቁጥር 21 ላይ

እንደተባለውም መጥፎ ነገር ነው የተከሰተው ፡፡በቁጥር 12 ላይ ምን ነበር የተፈጠረው?_________________________________________________

________________________________________________________________

6. እግዚአብሔርም እንደተናገረ የፈርዖን _________________ጸና፥ __________፡፡ፈርዖንም ተመልሶ ወደ ቤቱ ገባ፥ ______________________________________፡፡

7. ፈርኦን ባለመታዘዙ ምክንያት በግብፅ ህዝብ ላይ የተፈጠረው ነገር ምን ነበር?________________________________________________________

________________________________________________________________

**<u>ክፍል 2</u>**

***ትምህርት፡*** *መፅሀፍ ቅዱስን ስታጠኑ ብዙ ስፍራ ላይ ተደጋግመው የተጠቀሱ ቃላቶችን ትኩረት ሰጥቶ መመልከት ያስፈልጋል፡፡የተደጋገሙበት ምክንያት በጣም ጠቃሚ የሆነ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነት እንደያዙ ያሳየናል፡፡ለምሳሌ በዘፀአት 7፡14-24 ባለው ክፍል ውስጥ አራት ግዜ የተደጋገመ ቃል አለ፡፡እስቲ ከታች ያለውን ሳጥን እናንተ አሟልታችሁ ፃፉት፡፡በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በትር የሚለው ቃል ላይ ምልክት አድርጉበት፡፡*

| ጥቅሶች | ስለ በትር ምን ተነግሮናል |
|---|---|
| ዘፀአት 7:15 | **በትሯ ወደ እባብነት ተቀየረች** |
| ዘፀአት 7:17 | |
| ዘፀአት 7:19 | |
| ዘፀአት 7:20 | |

ስለበትሯ ምን የምናውቀው ነገር አለ? በዘፀአት 4፡20 ላይ ምን ተብሏ?_________________

*በትሯን ለፈርኦን እና ለግብፃውያን የምትታይ የፍርድ ምልክት ወይንም ማሳያ አድርጎ እንደተጠቀመባት በልባችሁ ያዙ፡፡ልክ በትሯ ስትዘረጋ የእግዚአብሄር ፍርድ ይገለጣል ለዚህም ማሳያ የሚሆነን በግብፅ ውሃ ላይ በትሯ ስትዘረጋ የግብፅ ውሃ በሙሉ ወደ ደምነት ተለወጥ፡፡ዘፀአትን ማጥናታችሁን ስትቀጥሉ በትሯን የማይካድ ታሪክ እግዚአብሄር እንደሰራ*

ነቅታችሁ ተከታተሉ።በትር የሚለውን ቃል ስታገኙ በማቅለሚያ ማርከራችሁ ምክት በማድረግ በትሯ ለግብፃውያን እና ለፈርኦን ከፍርድ ጋር ተያይዛ እንደ ቀረበች ተምልከቱ።

በትሯ ለሌላም አላማ አገልግላለች።ለሙሴ ተአምራቱን የሚያደርገው እግዚአብሄር እንደሆነ እንዳይረሳ አድርጎታል።ከፈርኦን ጋር በነበረው ጦርነት ይዋጋ የነበረው እግዚአብሄር ነበር።ህዝቡን ሊያድን የወጣው እግዚአብሄር ነበር።ሁሉን የሚችለው ኤልሻዳይ የሆነው እግዚአብሄር (ዘፀአት 6፡3) እራሱ "እኔ" የሆነው ታላቁ እግዚአብሄር ዘፀአት (3፡14) ነበር ሁሉን የሚያደርገው።ዘፀአትን ክፍል ሁለት ስናጠና ስለበትሯ ተጨማሪ ነገር እንመለከታለን።

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 8፡1-15 ያለውን ክፍል አንብቡ።የደም መቅሰፍቱ እስከ ስንት ቀን እንደቆየ አናውቅም ነገር ግን ከሰባት ቀን በኂላ ምን እንደተፈጠረ እንውቃለን።

**መልመጃ፡** ታላቅ ታሪክ እንደገና ተጀመረ።

1. ቁጥር 1፡ እግዚአብሄር ሙሴን ያዘዘው ትእዛዝ አልተቀየረም።ለፈርኦን የተላከለት መልእክትም አልተቀየረም፡______________________________
2. ቁጥር 2-4 ቀጥሎ ይሆናል የተባለው መቅሰፍት ምን ነበር ከበፊቱስ ምን ያህል ይገዝፋል?________________________________________

   ________________________________________________

   ጓጉንቸር (እንቁራሪቶች) በስፍራው ሁሉ! ነገር ግን ግብፃውያን አስማተኞችም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ችለው ነበር።
3. በዚህ ወቅት ግን አንድ አዲስ ነገር ተከስቶ ነበር።ፈርኦን ሙሴ እና አሮንን ጠርቷቸው ነበር።በቁጥር 8 ላይ ምን ነበር የጠየቃቸው?______________________________

   ________________________________________________
4. በቁጥር 9 እና 10 ላይ ሙሴ እና ፈርኦን በቀጣዮ ቀን መቅሰፍቱ እንደሚቆም ተስማምተው ነበር።እንደ እግዚአብሄር ያለ ማንም እንደሌለ ይታወቅ ዘንድ በቁጥር 11 ላይ ምን ተፈጠረ ?________________________________________

   ________________________________________________
5. በቁጥር 12 ላይ ሙሴ እና አሮን ከፈርኦን ጋ ወጥተው ሄዱ።ሙሴ በእግዚአብሄር ፊት ወጣ ምን ነበር የተነጋገሩት?__________________________________
   ጓጉንቸሮች (እንቁራሪቶች)! ሙሴ ምን ነበር የጠየቀው?________________አግዚአብሄርስ

ምን አቀረበ?________________________________እግዚአብሄር አንቁራሪቶቹ ጨርሰው እንዲጠፉ አላደረገም ቁጥር 13 እና 14 ፡፡ሙሴ የጠየቀው ይህንን ነበርን?ይህ ለፈርኦን እና ለሌሎቹ አስደናቂ ምላሽ ይሆን ? ምን ታስባላችሁ?____________________________

__________________________________________________________________________

6. ኦ አምላኬ !እስቲ ቁጥር 14 ወደራሳችሁ ሀሳብ አምጡት እና ህያው እንዲሆን አድርጉት፡፡በሃሳባቸሁም ማስታወሻላይ ፃፉት፡፡በእነዛ ቀኖች በግብፅ ውስጥ መኖር ምን ይመስል ነበር?____________________________________________________________

   __________________________________________________________________________

7. የፈርኦን ሀሳብ ምን ነበር? ቁጥር 15 ትንሽ እረፍት ሲያገኝ ____________________እና

   __________________________________________________________________________

8. እስቲ ወደ ሳጥን አንድ እንመለስ ! ለምንድነው የተደነቅነው?በርግጥ ተደንቀናል?ቁጥሩ አልቋል?__________________________________________________________________

   __________________________________________________________________________

## <u>ክፍል 3</u>

**ገለፃ :** ለምን ይህን ሁሉ ተደርጋለህ ? የተደረጉት አስር ተአምራቶች ናቸው እኛ ግን እስካሁን ያየነው ሁለቱን ብቻ ነው፡፡የደም እና የጓጉንቸር መቅሰፍቶች ናቸው ከሽታቸው የተነሳ ሙሴ እና አሮንን አስኪ ማፀኑ ድረስ ሆኑ ከፈርኦን ውጪ ማለት ነው፡፡የእግዚአብሄር በትር በእነዚህ ህዝቦች ላይ ከባድ ፍርድ ነው ያመጣችባቸው፡፡እብዚአብሄር ልቡን ባደነደነው እና ሊሰማው ላልቻለውን ለፈርኦንን ምንም ምህረት አላሳየውም፡፡በዘፀአት 7 ላይ እና 8 ላይ የፈርኦን ልብ_____________________________እና_______________________________________ይላል፡፡

የሰውን የደም ዝውውር ስርአት ተመልከቱ ፡፡ፈርኦን ደም ቅዳው ላይ ነው ችግር የተፈጠረበት ስለዚህ መጣም ችግር ውስጥ ነው ያለው፡፡ትእቢተኛ እና ኩሩ ሰው ነው፡፡ የግብፅ መሪ እና ንጉስ በመሆኑ እራሱን እንደ አምላክም ያያል፡፡እስራኤላውያን የእርሱ ባሪያዎች ስለሆኑ እነሱን በተመለከተ ከእግዚአብሄር ምንም አይነት መመሪያ አይቀበልም፡፡ንጉስ በመሆኑ እና ሁልግዜ አዛዥ በመሆኑ ምክንያት ከሌላ ሰው ትእዛዝ አይቀበልም፡፡እሱ ብቻ የሁሉ የበላይ እንደሆነ ነው የሚያስበው፡፡ከሱ ሌላ ማንም የለም ፡፡ሙሴ እና አሮንን ብዙ ግዜ አንደተፀፀተ እና ንስሀ አንደገባ እየነገራቸው ያታልላቸዋል፡፡እንደምናውቀው ግን ያደረገው ሁሉ ማስመሰል

ነበር፡፡ጓጉንቸሮች ከምድሪቱ ላይ እስኪነሱለት ድረስ ነበር ንስሀ የገባ የመሰለው፡፡እግዚአብሄር ግን እንደዛ ከማድረግ ይልቅ ጓጉንቸሮቹን አንዲሞቱ ነበር ያደረጋቸው፡፡ነገር ግን በጓጉነቸሮቹ ሞት ምክንያታት ምድሪቱ በመጥፎ ሽታ ተሞላች፡፡ምንኛ የሚዘገንን ሽታ ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን እናንተ ምን እያደረጋችሁ ነው ፡፡የጋዜጠኝነት ባርኔጣችሁን እድርጋችሁ በምድሪቱ ላይ እየሆነ ስላለው ነገር ሁሉ እየዘገባችሁ ነው ፡፡ሰዎችን መንገድ ላይ ያሉ ሰዎች ምን እያሏችሁ ነው፡፡በራምሴ ከተማ ምን እየሆነ ነው፡፡እስቲ ካናገራችኋቸው ሰዎች መካከል ምን ምን ምላሽ ሰጧችሁ?_____________________________________________________

_________________________________________________________________________

**ስለ እግዚአብሄር ምን ተማርን ፡** “ህዝቤን ልቀቅ” በሚለው የእግዚአብሄር ንግግር ውስጥ የእግዚአብሄርን እውነተኛ ፍቅር እና የልቡን መልካም ሀሳብ ተመለከታችሁ፡፡ቃላቶቹ የእግዚአብሄርን የልብ ሀሳብ ይገልጣለሉ ፡፡እነዚህ በርግጥ የእግዚአብሄር ህዝቦች ናቸው፡፡የእሱ የሆኑት ያኔ በዘፍጥረት 17፡19 ላይ ለአብርሀም ቃል ሲገባለት ነው፡፡ይህ የአብርሀምን ዘሮች በሙሉ ዘመዶችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው ፡፡እግዚአብሄር አስቀድሞ ተመልክቷቸዋል ፣ተጠንቅቆላቸዋል፣ራርቶላቸዋል፣በባርነት ቤት አንኳን አልተዋቸውም፡፡

እግዚአብሄር ፈርኦንን እዝቡን እንዲለቅ አዘዘው፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሄር ህዝቡ በስጋ ከተያዙብት ባርነት ነፃ እንዲወጡ የፈለገ ነው የሚመስለው፡፡ነገር ግን እግዚአብሄርን ትክክለኛ ሀሳብ ካልተረዳን ልንሳሳት አንችላለን፡፡ለህዝቡ ያለው ፍቅር ምርጫ አሳጥቶታል ፡፡ፍቅሩ ህዝቡን አንዲለቀቅ ትእዛዝ እንዲያወጣ አስገድዶታል፡፡ካልተለለቀቁ እነሱን ለማስለቀቅ ይዋጋል፡፡ውጊያውንም እራሱ ብቻውን ይዋጋል፡፡እኛ ሁላችን በተፋፋመ ውጊያ ውስጥ ነው ያለነው ፡፡እግዚአብሄር አና በክፉው ፣በእግዚአብሄር እና በፈርኦን ፣በእግዚአብሄር እና በሰይጣን መካከል ባለ ጦርነት ውስጥ ነው ያለነው፡፡ነፃ የሚወጡትም እሱ ሲፈጥራቸው እንዲሆኑ ለፈለገው ነገር አንዲኖሩለት ነው፡፡እሱ ለአባቶቻቸው ለእነ አብርሐም የብልፅግና ፣የመብዛት፣እና የሀብት ቃልኪዳን ገብቶላቸዋል ያንን ደግሞ መፈፀም አለበት፡፡

የእግዚአብሄር ፍቅር የፀና ነው፡፡የፀና የሚለውን ቃል ለፈርኦንም መጠቀም አንችላለን ምክንያቱም ፈርኦን ራስ ወዳድ እና ልቡ በአመፅ የተሞላ ሰው ስለሆነ፡፡እግዚአብሄር ግን ፍቅሩ የፀና አፍቃሪ ነው፡፡ለሚወዳቸው እስከሞት አንኳን ይዋጋል፡፡የእግዚአብሄር ፍቅር ለእናንተ የፀና

እንደሆነ ታውቃላችሁ በይቅርታ የፀና ፣በጥንቃቄ የፀና፣ለእኛ በሚያስፈልገው ሁሉ የፀና፣በአባትነት ፍቅር የፀና ነው።

1. እንደዚህ አይነት ፍቅር ታውቃላችሁ?እስቲ እነዚህን ሁለት ታሪኮች አንብባችሁ ይህንን ታላቅ ፍቅር ለመገንዘብ ሞክሩ! እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ስለእግዚአብሔር ፍቅር ምን ይገልጡልናል?

   ሀ. ሉቃስ 15:17 ______________________________

   ______________________________

   ለ. ሉቃስ 15: 11-24______________________________

   ______________________________

2. በስፍራዎች ሁሉ የሚፈልግ አምላክ ታውቃላችሁ፣ፈልጎ አግኝቷችሁ ተሸክሚችሁ ለዘላለም በቤቱ እንድትኖሩ የሚወስዳችሁ አምላክ ታውቃላችሁ? በእራስ ወዳድነት ተይዛችሁ የራሳችሁን ነገር በምታሳድዱበት ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን ሆናችሁ ስለእናንተ የሚዋጋ አምላክ ታውቃላችሁ?ከጠፋችሁበት ሲያገኛችሁ እጆቹን ዘርግቶ በፍቅር የሚቀበል አምላክ ታገኛላችሁ? የፀናው ፍቅሩ ለሁላችን ነው ።በዚህ ላይ የምትጨምሩት ሀሳብ ምንድነው?______________________________

   ______________________________

**ፀሎት**: እስቲ የእግዚአብሄርን የማይለወጥ ፍቅር ከተያዛሁበር ባርነት እንና ካነበጣችሁ ጭቆና ነፃ ሊያወጣችሁ የሚፈልገውን አምላክ በራሳችሁ ቃል ፀሎታችሁን ፃፉ።ለጠላታችሁ አንዲህ ይላል "ህዝቤን ልቀቅ" ለፈጠረው ፍጥረት ታላቅ የሆነውን ፍቅሩን ተመልከቱ።በፍቅር ሊቀበላችሁ የተዘረጋውን እጆቹን በአይነ ህሊናችሁ እስቡት።እናንትን በዘላለማዊ ፍቅር መውደዱ ለእናንተ ምን ማለት እንደሆነ እስቲ ንገሩት። ______________________________

______________________________

## <u>ክፍል 4</u>

**የቤት ስራ**: ዘፀአት 8:16-19 አንብቡ ።መቅሰፍቱ ቀጥሏል።ክፍል ሶስት የተጠናቀቀው አፀያፊ በሆነው የጓጉነቸሮቹ እሬሳ ነው።

**መልመጃ፡** በዚህ በሶስተኛው መቅሰፍት የእግዚአብሄር መለልእክተኞች የሆኑትን ሙሴን እና አሮንን ባለመስማቱ ምን እንደደረሰበት አንማራለን፡፡

1. በቁጥር 16 ላይ ለሙሴ ቀጥሎ ምን እንዲያደርግ ነገረው________________________
   ______________________________________________________________________
2. ይህ የ__________________መቅሰፍት ነው፡፡እነዚህ ፍጥረቶች በጣም የሚያበሳጩ ነፍሳት ናቸው፡፡የትም ሄዳችሁ ልታመልጧቸው አትችሉም፡፡ያናድዷችኋል ፤በፊታችሁ ላይ ያርፋሉ ፡፡በሽታንም ያስተላልፋለሉ፡፡አሮንም እጁን ዘርግቶ የምድሩን ትቢያ መታው፡፡አስቡ! ቁጥር 17 የሚነግረን ስለምንድነው?___________________________
   ______________________________________________________________________
3. ይኼኛው መቅሰፍት ከሌሎቹ ከሁለቱ ይለያል፡፡ በቁጥር 18 ላይ ምን አንማራለን_____________________________________________________________
   ______________________________________________________________________
4. አስማተኞቹ በቁጥር 19 ላይ ምን ተረዱ______________________________________

   በምእራፍ 7፡5 ላይ እግዚአበሄር ለሙሴ ምን ነግሮት ነበር “ግብፃውያን ምን ያውቃሉ ብሎት ነበር____________________________________________________________

   በዚህኛው ተአምራት አስማተኞቹ ይኼኛው ተአምራት ከእነሱ ኃይል በላይ እንደሆነ ሲናገሩ እንመለከታለን፡፡በመጀመሪያዎቹ ሁለት ተአምራቶች ውሃውን ወደ ደም መለወጥ እንዲሁም ጓጉንቸሮችን ማውጣት ችለው ነበር አሁን ግን እነዚህን ነፍሳት ማውጣት አልቻሉም፡፡ያ የእግዚአብሄር ስራ ነበር፡፡ ዘፀአት 8፡12-13
5. አሁንም ቢሆን ፈርኦን ሀሳቡን አልቀየረም ዘፀአት 7፡13 የፈርኦን ልብ ደነደነ ብሎ ይነግረናል ፡፡በቁጥር 8፡15 ላይ የሆነ ነገር ሆኗል ______________________ልቡን አደነደነ፡፡ዘፀአት 8፡19 ላይ ምን ተፅፎልናል?__________________________________

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 8፡20-32 አንብቡ

**መልመጃ**

1. የሚቀጥሉት አብዛኛዎቹ ቁጥሮች ስለአራተኛው መቅሰፍት ይናገራሉ፡፡ለመሆኑ አራተኛው መቅሰፍት ምንድነው?________________________________________

2. እሁንም በድጋሚ እግዚአብሄር ሙሴን ፈርኦን ፊት እንዲሄድ አዘዘው እግዚአብሄር በዚህ ወቅት ምን ነበር ያዘዘው?________________________________________
3. ፈርኦን ይህንን ትእዛዝ ካልፈፀመ የሚሆንበት ነገር ምንድነው ቁጥር 21 ?__________
__________________________________________________________________

**ገለፃ፡** እስቲ ዝንቦችን ለጥቂት ደቂቃ አስቧቸው፡፡ምናልባት ከቤት ውጪ ተመግባችሁ ከሆነ ጥቂት ዝንቦች መጥተው አንዴት አንዳበሳጯችሁ አስታውሱ፡፡የሚነሱት ከቆሻሻ ላይ ነው፡፡ደስ ያላቸው ነገር ላይ ነው የሚያርፉት፡፡ሰዎች ዝንቦችን የሚስብ ነገር አያደርጉም ነገር ግን ዝንቦች ሰዎች ያሉበት ድረስ መጥተው ነው የሚያርፉባቸው፡፡ቤተክርስቲያን ውስጥም ብትሆኑ መንገድ ላይ መበሳጨታችሁ አይቀርም፡፡ካፍቴሪያ ውስጥም ብትሆኑ ሱፐር ማርኬት ውስጥ ዝንቦች ይኖራሉ፡፡

ስለዚህ ዘንቦች ግብፅን ወረሯት፡፡ችግር ቢሆኑ አይገርምም፡፡ምክንያቱም የሞቱት ጓጉነቸሮች ሽታ ዝንቦቹን ስቧቸዋል ያደግሞ ጥሩ የመራቢያ ስፍራ ሆኖላቸዋል፡፡እስቲ አስቡት የዝንቦቹ ብዛት እላያቸው ላይ መራመድ እስክትችሉ ድረስ የተከመሩ ነበሩ፡፡አንዴት የሚዘገንን ነገር ነው፡፡

እስቲ ይህንን ሁኔታ በአእምሯችሁ አስቧቸው አና የነበረውን ሁኔታ በራሳችሁ ቃል ግለፁት፡፡_________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________

**<u>ክፍል 5</u>**

**መልመጃ፡**

1. ቁጥር 22–23 ላይ ፡በዝንቦች መቅሰፍት ዙሪያ በደንብ መነጋገር ፈልጓል፡፡በዚህ ግዜ ያደረገው ነገር ምንድነው?_____________________________________________
   የፈርኦን ሹማምንት አንደዚሁም ህዝቡ በሙሉ የሚያወራው ስለ ዝንቦቹ ነው፡፡፡ የተጠቀጠቀ የዝንብ ጎርፍ ወደ የቤታቸው እየመጣባቸው ነው፡፡እግዚአብሄር ግን ነገሮችን በተለየ መንገድ ነበር እየሰራ የነበረው ምክንያቱም ይህ ሁሉ መቅፍት ሲሆን በጌሴም የተቀመጡት የእግዚአብሄር ህዝቦች ግን ከዚህ አይነት ችግር ነፃ ነበሩ፡፡ ይህ ማዳን

እስራኤላውያን በግብፅ ምድር ሆነው ይለማመዱት የነበረ የእግዚአብሄር ማዳን ነው፡፡የእግዚአብሄር የምህረት እጅ በህዝቡ ላይ በመዘርጋቱ ህዝቡ ተዘልሎ ነው የተቀመጠው፡፡ፍርዱ ግን በፈርኦን እና በህዝቡ ላይ ነበር፡፡

2. እግዚአብሄር ፈርኦነ በተለየ መልኩ እንዲያውቀው የፈለገው ነገር ምን ነበር?_________
“እኔ እግዚአብሄር በምድሪቱ ለይ__________ያለው ምን አንደሆነ እዲያውቅ_________”
   ሀ. ፈርኦን ማወቁ የሚጠቅመው ለምንድነው?______________________________
   ______________________________________________________________
   ለ. ለእስራኤላውያንስ ይህን ማወቁ የሚጠቅማቸው ለምንድነው?_________________
   ______________________________________________________________
3. ቁጥር 24 ፡ “እግዚአብሄር ይህን አደረገ” እስቲ የሰራውን ነገር አስቡ፡
   ሀ. በፈርኦን ቤተመንግስት፡____________________________________________
   ለ. በባለስልጣናቱ ቤት፡_______________________________________________
   ሐ. በአጠቃላይ ግብፅ፡________________________________________________
4. ፈርኦን አሁን ድርድር ለማድረግ ተዘጋጅቷል፡
   ሀ. በቁጥር 25 ላይ እንደ ቅድሚያ መደራደሪያ ሀሳብ ያቀረበው ምንድነበር?________
   ______________________________________________________________
   ለ. በቁጥር 26 እና 27 ሙሴ ግድ ያለው ነገር ምንድነው?የሰጠው ምክንያትስ ምን ነበር?__________________________________________________________
   ሐ. በቁጥር 27 መሰረት እግዚአብሄር አቋም ተለውጧል? እስቲ ዘፀአት 3፡18 ተመልከቱ፡፡እግዚአብሄር ከፈርኦን ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ ነበር?___________
   ______________________________________________________________
5. በቁጥር 28 ላይ ፈርኦን በምን ተስማማ?____________________________________
6. ፈርኦን ሙሴን በመጨረሻ የጠየቀው ነገር ምንድነው?_______________________
7. ሙሴም እንደሚፀልይ እና ዝንቦቹን ከምድሪቱ ላይ እንደሚወገዱ አረጋግጦለታል፡፡በቁጥር 29 ላይ ሙሴ የሰጥው ማስጥንቀቂያ ምን ነበር? _________
______________________________________________________________
8. ቁጥር 30-31 ላይ፡ሙሴ ከፈርኦን ጋ ወጣ፡፡ወደ እግዚአብሄር ፀለየ፡፡እግዚአብሄርም ሙሴ የፀለየውን ሰማ፡፡ዝንቦቹም እስከ “_________________________________፡፡ፍርኦን

እንደገና ልቡን ቢያደነድን ይገርመናል ?እኛ አሁን የታሪኩን ፍፃሜ ስለምናውቅ ምንም ላይመስለን ይችላል ፡፡አስቲ እራሳችሁን ፈርኦንን አድርጋችሁ አስቡ?እነዛን ሁሉ መቅሰፍቶች ካያችሁ በኋላ መታዘዝ እና ህዝቡን ለመልቀቅ ለምን አመነታችሁ?እናንተ ፈርኦንን ብትሆኑ ትለቁ ነበር?_______________________________________________

_______________________________________________________________

**ስለ እግዚአብሄር የተማርነው፡** ይህ የዝንብ መንጋ የሚያሳየው የእግዚአብሄርን በህዝቡ ላያ ያደረገውን ምህረት ነው፡፡ከእሱ የተለዮ ህዝቦች ነበሩ ልዮ ነበሩ፡፡እሱም አምላካቸው ነበር፡፡ አብርሀም ከሰጠው ለይስሀቅ እና ለያዕቆብ ባደሰው ቃልኪዳን መሰረት እግዚአብሄር የራሱ ሊያደርጋቸው ፈልጓል፡፡አሁን ደግሞ እሱ አምላካቸው አንደሆነ ዓለም ሁሉ አንዲያውቅ ፈልጓል፡፡እሱ ከህዝቡ ጋር እንሆነ ፈርኦን አንዲያውቅ ፈልጓል፡፡ “በዚያን ቀን በምድር መካከል እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቅ ዘንድ፥ በዚያ የዝንብ መንጋ እንዳይሆን ሕዝቤ የሚቀመጥባትን የጌሤምን ምድር እለያለሁ፡፡”ዘፀአት (8፡22) በጥንታዊ እምነቶች አስተሳሰብ አማልክት ለራሳቸው ድንበር ከልለው ነው የሚኖሩት፡፡ለምሳሌ የግብፃውያን አማልክት ከፍልስጤም አማልክት ይበልጣሉ ፡፡ያህዌ ግን ድንበር ሳይገድበው በሁሉም ስፍራ መስራት የፈለገውን ይሰራል፡፡

በዘፍጥረት 46 ላይ እግዚአብሄር የያዕቆብን ቤተሰብ ወደ ግብፅ ሲልክ ቃልኪዳን ሰጥቷቸዋል፡፡ለመሆኑ ምን ነበር እግዚአብሄር ለያዕቆብ ያለው (ዘፍጥረት 46፡3-4) ? ______

_______________________________________________________________

እግዚአብሄር ሙሴንም ወደ ፈርኦን ሲልከው እንዲህ የሚል ቃልኪዳን ሰጥቶት ነበር “እስራኤልን ከግብፅ ታወጣልኛለህ” ለሙሴ ክርክር እግዚአብሄር የሰጠው ቀጥተኛ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 3፡12) ?__________________________________________________

በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሄር የቀረብን ሁላችን እሱ ከኃጢአት አንዳዳነን ከተገዛንበት የኃጢአት ባርነት ነፃ ያወጣን እሱ አንደሆነ ያመንን ሁላችን ልክ አንደ እስራኤላውያን ከእግዚአብሄረ የተሰጠን የተስፋ ቃል አለን፡፡በማቲዎስ 28፡20 ላይ የተሰጠን የዋስትና ቃል ምንድነው የሚለው?____________________________________ለእየሱስ ክርስቶስ ከተሰጡት ሰሞች መካከል አንዱ አማኑኤል አንደሆነ አናውቃለን፡፡በማቲዎስ1፡23 ላይ

የዚህ ስም ትርጉም ምን እንደሆነ ይነግረናል?______________እግዚአብሄር በህዝቡ መካከል መኖር አለመኖሩ ምንም ጥያቄ የለውም ።

**ማሰላሰል፡** ልክ በእስራኤላውያን እና በግብፃውያን መካከል ልዮነት እንዳደረገ በምናምነው እና በማያምኑት መካከል ልዮነትን ያደርጋል።በ 1 ጴጥሮስ 2፡9፣10 ላይ ምን ተነግሮናል?እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በካርዳችሁ ላይ በመፃፍ አጥኑአቸው። ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሀኑ ያወጣችሁን እግዚአብሄርን በየእለቱ እንዴት እንደምትባርኩት ታላቅነቱንም እንዴት እንደምታውጁ አስቡ።እስቲ እግዚአብሄርን እንዴት እንደምትባርኩት ፣እንደምታመልኩት ያላችሁን ልምምድ ዘግቡት (ፃፉት)።

**በጥልቀት ማየት፡** ስለ እስራኤላውያን ስንማር በነበረው ትምህርት ብርሃን እስቲ ጥቂት ግዜ የሚከተሉትን ነገሮች በማሰብ ግዜ አሳልፉ፡

1. ከታች የተዘረዘሩትን ለእነዚህ ሰዎች ምን ማለት ናቸው

   ሀ. የተመረጠ ዘር____________________________________________

   ለ.የንጉስ ካህናት____________________________________________

   ሐ. ቅዱስ ህዝብ____________________________________________

   መ. ለርስቱ የተለየ ወገን____________________________________________

2. አላማ አላቸው ማለት ምን ማለት ነው፣ ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤የሚለው ቃል ለእነሱ ምን ማለት ነው?______________

   ____________________________________________________________

3. ለዚን ማህበረሰብ እናንተ ቀድሞ__________________አልነበራችሁም አሁን ግን_______________________ናችሁ፤ እናንተ_____________________ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን____________________________አግኝታችኋል። እስቲ በዚህ ቃል ላይ ያላችሁን ሃሳብ ፃፉት፡_____________________________________

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

4. እግዚአብሔር በልጁ በእየሱስ ክርስቶእ ህይወት ፣ሞት ፣እና ትንሳኤ አማካኝነት የእርሱ ህዝብ አድርጎናል፡፡እስቲ ጥቂት ግዜ ወስዳችሁ እነዚህ ቃሎች ለእናንተ ምን ማለት እንደሆኑ ተመልከቷቸው

   ሀ. የተመረጠ ሰው______________________________________________

   ለ. የንጉስ ካህን_______________________________________________

   ሐ. ቅዱስ ህዝብ_______________________________________________

   መ. ለርስቱ የተለየ ወገን__________________________________________

   ________________________________________________________

5. እስቲ ለእናንት ህይወታችሁ ሰአላማ አለው ? ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእግዚአብሄርን በጎነት ልትናገሩ ነው የተጠራችሁት ማለት ምን ማለት ነው?________

   ______________________________________________________________

6. በክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ ወይንም በቤተክርስቲያን ውስጥ "እናንተ ቀድሞ____________________አልነበራችሁም አሁን ግን__________________ናችሁ፤ እናንተ_________________ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን__________አግኝታችኋል፡፡ ማለት ምን ማለት ነው?

   እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን አመለካከት ፃፉት፡______________________________

   ______________________________________________________________

**ፀሎት፡** የእርሱ ምርጦች እንደሆንን እውቅና የሰጠን እግዚአብሄር ይመስገን፡፡የሱን በጎነት እንድንናገር ህይወታችን አላማ አና ትርጉም የሰጠ አምላክ ይመስገን፡፡አካሉ ስለሆነችው ቤተክርስቲያን የሱ ስለሆነው ህዝብ እግዚአብሄር ይመስገን፡፡______________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

# ትምህርት አምስት

# ሕዝቤን ልቀቅ

## ዘፀአት 9 -11-እግዚአብሄር የፈርኦንን ልብ አደንደነ

---

### የትምህርት 5 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 5፡ ዘፀአት 9-11

- ፅድቅን መማር
- መቅሰፍቱ
- የእግዚአብሄር የምህረት እጆች
    - ፍቺ ፡ ፀጋ
    - ፍቺ ፡ ምህረት
- የጨለማ እና አንበጣ መቅሰፍቶች
- የሞት መቅሰፍት
- የበኩር ልጅ ቅስፈት

## መግቢያ

የእግዚአብሄር የፍርድ እጁ በግብፃውያን ላይ ደጋግማ መጥታለች፡፡የግብፅን ምድር በመቅሰፍቱ ተበላሽታለች፡፡በሌላ መልኩ የእግዚአብሄር ምህረት እና ማዳን በህዝቡ በእስራኤል ህዝብ መካከል በዝቷል፡፡አስቲ የምህረት አና የፀጋን ፍቺ ከልሳችሁ ተመልከቱ፡፡በእዚህ ሁለት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በዘፀአት 9፡11 ላይ የትኛውን የእግዚአብሄር ባህሪ ነው የምትመለከቱት?

በመጨረሻ እግዚአብሄር እንዲህ አለ፡፡ “አሁን በፈርኦን ላይ እና በግብፃውያን ላይ አንድ መቅሰፍት አመጣለሁ” አለ፡፡ሙሴም በፈረኦን እና በህዝቡ ዘንድ ክብር አገኘ፡፡በተጨማሪም ሙሴ በእስራኤላውያን አንድ እንደ ችግር ፈጣሪ እየታየ ነው፡፡አሁን በምድሪቱ ላይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ይህንን ለውጥ ያመጣው ምንድነው?

ሙሴ የመጨረሻውን መቅሰፍት ተናግሯል፡፡የፈርኦንን የገዛ ልጁን ጨምሮ የግብፃውያን በኩር መሞቱም የፈርኦንን ልብ አልቀየረውም ልቡ አሁንም እንደደነደነ ነው፡፡ሞት የመጣው በሰው ልጆች እንደዚሁም በእንስሳት በኩር ሁሉ ላይ ነው፡፡ነገር ግን ፈርኦን አሁንም አይሰማም፡፡ለምንድነው? አግዚአብሄር በግብፅ ላይ ሊያመጣ ያሰበው ነገር ምንድነው?ፈርኦን አሁንም ህዝቡን አልለቅም ካለ ቀጥሎ ምን ሊፈጠር ነው?

አንድ ሀይል የሰውን ልጆች ባሪያ ካደረገ እግዚአብሄር እንዴት ነፃ እንደሚያወጣ ተማሩ፡፡

**ክፍል 1**

***ትምህርት፡*** *በዚህ ታሪክ ውስጥ ሙሴ ትልቅ ሚና ነው የተጫወተው፡፡በባርነት እና በጭቆና ውስጥ ያለውን ይህንን ህዝብ ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሄር ተልኮ ነው፡፡ፈርኦንን ፊት ለፊት እንዲገጥመው በእግዚአብሄር ታዞ የወጣ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ በሙሴ በኩል እግዚአብሄር እነዚህን መቅሰፍቶች በግብፅ ምድር እና በህዝቦቿ ላይ ታላቅ መከራ፣ሁከት፣እና ጥፋት ለማምጣት ተጠቅሞበታል፡፡ በዘፀአት 8፡8 ላይ እንዲሁም 8፡28 ፍርኦን ሙሴ እንዲፀልይ መጠየቁ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር በግብፅ ካሉ አማልክቶች እንደሚበልጥ እንደተረዳ ማሳያ ነው፡፡ስለዚን ፈርኦንም ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሄር ቁጣ መዳን ፈልጓል እግዚአብሄርም ደግሞ ተራ በተራ ለተፈፀሙት መቅሰፍቶች መጨረሻ አበጅቶላቸዋል፡፡*

*እግዚአብሄር ፈርኦን ላይ ካደረገው ነገር በተቃራኒው ፈርኦን እስራኤላውያንን መልቀቅ አልፈለገም ግትር እና አልከኛ በሆነው ልቡ ምክንያት ከሚመጣበት መከራ ግን መዳን ይፈልግ ነበር፡፡እግዚአብሄርን ለመታዘዝ ፍለጎት አለው ነገር ግን ሙሴ የፈርኦንን ክፉ መንገድ በማወቁ እግዚአብሄር ፊት ፈርኦን የጠየቀውን ጥያቄ ይዞ ቀረበ፡፡እናም እግዚአብሄር ደግሞ ምላሽ ሰጠ፡፡እግዚአብሄር ፈርኦን የፈለገውን አደረገለት ፈርኦን ግን እግዚአብሄር የፈለገውን አላደረገም፡፡*

*ይህንን ጉዳይ ለመረዳት አስቸጋሪ ሆነባችሁ ይሆን? ፈርኦን እንደማይታዘዝ እና አመፀኛ እንደሆነ በአመፁም እንደሚቀጥል እያወቀ ለምንድነው ፈርኦን የፈለገውን ነገር የደረተለት? ነብዮ ኢሳያስ በ26፡9-11 ላይ ምንድነው ያለው እስቲ ይህንን ክፍል አንብቡት፡፡*

1. በቁጥር 9 ላይ የእግዚአብሄር ፍርድ ሲመጣ በምድር በሚኖሩት ላይ ምን ይሆናል ይላል?________________________________________________

   ______________________________________________________
2. ቁጥር 10 ላይ *"ለ____________ ____________ ቢደረግለት ____________አይማርም በቅኖች ምድር ክፉን ነገር ያደርጋል፥ የእግዚአብሔርንም ግርማ አያይም፡፡"*
3. በቁጥር 10 ላይ ምንን አያይም ይላል?________________________________________

4. ቁጥር 11 ላይ ስለ ኃጢአተኛው ምን አንማራለን የእግዚአብሄር እጅ ትነሳለች ነገር ግን________________________________________________

____________________________________________________

5. በቁጥር 11 ላይ ኢሳያስ ለጌታ እንዲህ አለው "____________________አይተው ________________________እሳትም________________________________

ፅድቅን መማር ባልቻለው ፈርኦን ላይ የእግዚአብሄር ፍርድ መጥቶበታል፡፡የእግዚአብሄር የፍርድ እጅ ተነስታለች ግርማዊነታቸው ግን አላወቁም፡፡እግዚአብሄር ለህዝቡ ያለው ቅናት ግብፅን በሙሉ ኃፍረት ውስጥ የሚጥል ነው፡፡ልክ እንደሌሎቹ ሁሉ ይህ መቅሰፍት በአሳዛኝ ሁኔታ ነው የተጠናቀቀው፡፡ፈርኦን አሁንም በአመፀኝነቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ልቡ ደንድኗል፡፡የእግዚአብሄርን ሰዎች አልለቅም ብሏል፡፡የጌታን ትዕዛዝ አልፈፅምም ብሏል፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት ምእራፍ 9 እና 10 አንብቡ፡፡ እንግዲህ ፈርኦን ልቡን በማደንደኑ እና ባለመታዘዙ ምክንያት በግብፃውያን ላይ የደረሱትን መቅሰፍቶች ተመልክተናል፡፡ቀጣዮቹ መቅሰፍቶች የሚገኙት በቁጥር 9 እና 10 ላይ ነው፡፡የመጀመሪያዎች አራቱ የሚመሳሰል ነገር አላቸው፡፡በፈርኦን አለመታዘዝ ምክንያት በሆነው ነገር ትኩረት ሰጥተን ልንመለከታቸው የሚገባን ቃላቶች አሉ፡፡ግዜ ወስዳችሁ እነዚህን ሁለት ምእራፎች በማንበብ ቀጥሎ የተሰጠውን ሳጥን ሙሉ ስለእያንዳንዱ መቅሰፍት የተሰጠውን መልሱ፡፡ይህ ሲባል ሁሉም ሳጥኖች መልስ አላቸው ማለት እይደለም፡፡

መቅሰፍት ቁጥር 5 የ____________________በቅሰፍት

| ጥቅሶች | ተመሳሳይነታቸው | ምልከታ | የግል አስተያየት |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 9:1 | | | |
| ዘፀአት 9:2-3 | | | |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 9:4 | | | |
| ዘፀአት 9:5-6 | | | |
| ዘፀአት 9:7 | | | |

በቅሰፍት ቁጥር 6፡ የ________________________መቅሰፍት

| ጥቅሶች | ተመሳሳይነታቸው | ምልከታ | የግል አስተያየት |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 9:8-9 | | | |
| ዘፀአት 9:10 | | | |
| ዘፀአት 9:11 | | | |
| ዘፀአት 9:12 | | | |

**ክፍል 2**

መቅሰፍት ቁጥር 7 ፡ የ______________________መቅሰፍት

| ጥቅሶች | ተመሳሳይነታቸው | ምልከታ | የግል አስተያየት |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 9:13 | | | |
| ዘፀአት 9:15-16 | | | |
| ዘፀአት 9:18-19 | | | |
| ዘፀአት 9:20-21 | | | |
| ዘፀአት 9:22-25 | | | |
| ዘፀአት9:26 | | | |
| ዘፀአት9:27-30,33 | | | |
| ዘፀአት9:34-35 | | | |

**ትምህርት፡** እግዚአብሄር ብግብፃውያን እና በእስራኤላውያን መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነትን እያደረገ ነው፡፡መቅሰፍቶቹ ለግብፃውያኑ ለመቋቋም ከባድ ሲሆንባቸው እስራኤላውያን ግን

ተዘልለው ተቀምጠዋል፡፡በእግዚአብሄር የምህረት እና የፍርድ እጆች መካከል ግልፅ ልዩነቶችን እያየን ነው፡፡በእነዚህ መቅሰፍቶች አማካኝነት ፈርኦንን እና ህዝቦቹን የሚያንበረክክ ታላቅ የሆነውን የፍርዱን ኃይል ገልጧል፡፡በአንድ ግዜ ከምድረገፅ ሊያጠፋቸው የሚችል መቅሰፍት ማድረግ ይቸል ነበር፡፡የሚገርም ነው በዚህ ሁሉ አመፃቸው እግዚአብሄር ግብፃውያንን ከምድረገፅ አለማጥፋቱ ምንያህል ታላቅ የምህረት አምላክ መሆኑን ያሳያል፡፡

1. በዘፀአት 9 :16 እግዚአብሄር ህዙቡን እስራኤልን ተዘልሎ እንዲቀመጥ ያደረገበትን ምክንያት ተናግሯል ፡፡ምክንያቱ ምን ነበር?____________________________________

   ____________________________________________________________________

2. ምንም እንኳን እግዚአብሄር ፈርኦን ታዞ ህዝቡን እንደማይለቅ ቢያውቅም በረዶው እና ውሽንፍሩ እንዲቆምለት ሲጠይቅ ቆሞለታል፡፡ዘፀአት 9፡33 ሙሴ ወደ እግዚአብሄር እጁን ዘረጋ እግዚአብሄርም ምላሽ ሰጠ ምህረቱን ለግብፃውያን አደረገ፡፡ምን ነበር ያደረገው?____________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ነገር ግን አሁንም እንደቀድሞው የፈርኦን እና የባለስልጣናቱ ልብ እንደደነደነ ነው ያለው፡፡

**ትግበራ፡** በዚህ ክፍል ውስጥ የትኛውን ከህይወታችን ጋር ማዛመድ እንዳለብን ማወቅ ይህን ያህል ያስቸግር ይሆን? እስቲ ጥቂጥ ግዜ ውሰዱና በዛሬው እለት የእግዚአብሄርን የምህረት እጅ ስንት ግዜ እንዳያችሁ አስቡ፡፡የምንኖረው ህይወት ከእግዚአብሄር ቸርነት የተነሳ ነው፡፡ብዙዎቻችን በርግጥ መልካም ነገር እንደሚገባን እና ምንም አየነት ችግር ሊገጥመን እንደማይገባ አምነን ነው የምንኖረው፡፡ቀደም ብለን ባጠናነው የዘፀአት ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር እጅግ አጥፊ የሆኑ መቅሰፍቶችን ፈርኦን ላይ ቢያመጣም በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ እንደዚሁ ብዙ ምህረት ሲያደርግለት እንመለከታለን፡፡እግዚአብሄር ያደረገው እና ሊያደርግ ይችል የነበረው መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ምናልባት ግብፃውያንን የተቀሩት ዘጠኙ መቅሰፍቶች ሳያስፈልጉ በአንዱ መቅሰፍት ብቻ ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋቸው ይችል ነበር፡፡ነገር ግነ እሱ ሰማይን እና ምድርን የፈጠረ አምላክ መሆኑን እንዲረዱ እድል እየሰጣቸው ነበር፡፡ስሙ በምድር ሁሉ ይታወጅ ዘንድ ታለቅ ሀይሉን እንዳሳየ ይነግረናል፡፡

**የፍቺ ክለሳ፡** እንደ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን  የሚገባን የእግዚአብሄር ቁጣ ፣ቅጣት እና ፍርድ ነበር፡፡ነገር ግን ይገባን ከነበረው ከዚህ ጥፋት በተቃራኒ የእግዚአብሄር ፀጋ እና ምህረት በዛልን፡፡

- ***ፍቺ : ፀጋ***

እግዚአብሄር የማይገባኝን እና በምንም ላገኘው የማልችለውን ፍቅሩን ሰጥቶኛል፡፡የኃጢአት ፍርድ (ደሞዝ) ሞት ነው፡፡ለእኔ የሚገባኝም ያ ነበር፡፡ዘፍጥረት 2፡17 እና ሮሜ 6፡23  ተመልከቱ፡፡ በእየሱስ ክርስቶስ ስቃይእና ሞት አኔ የማይገባኝን የእግዚአብሄርን ፍቅር ፣ፀጋ፣አንዲሁም ይህ ፍቅር ከእግዚአብሄር ጋር በነፃነት ለዘላለም መኖርን ሰጠኝ፡፡ትምህርት 2 ላይ የእግዚአብሄር እቅድ እና የእኔ  ምርጫ የሚለውን ትምህርት ከልሱት፡፡

- ***ፍቺ : ምህረት***

ምህረት ማለት እግዚአብሄር አንዲሆንብን  የሚገባውን ነገር ሲተውልን ማለት ነው፡፡ከኃጢአታችን የተነሳ እና ኃጢአትን ለመስራት ከሚፈልገው ማንነታችን የተነሳ የሚገባን ቅጣት ነበር ፡፡ሞት ይገባን ነበር፡፡በሮሜ 6፡23 ላይ “የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው፡፡” ይላል፡፡የሚገባን ሞት ሆኖ ሳለ እግዚአብሄር ከኃጢአታችህ የተነሳ ሊሆንብን የሚገባውን ነገር ትቶ የማይገባንን ምህረት ሰጠን፡፡ይልቁንም በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ የዘላለምን ህይወት ሰጠን፡፡ትምህርት 4 *የእግዚአብሄር እቅድ እና የሰው ምርጫ* የሚለውን ትምህርት ተመልሳችሁ አንብቡት፡፡

**ገለፃ፡** በክለሳ መልክ አንደገና ግዜ ወስዳችሁ ያጠናችሁትን ክፍሎች በሙሉ ከህይወታችሁ ጋር አዛምዱ፡፡ ሳይገባችሁ የእግዝኢአብሄርን ፀጋ በህይወታችሁ የተለማመዳችሁበትን ግዜ ለእናንት ያለውን ሀሳብ፣መልካምነቱን ያያችሁበትን ወቅት አስታውሱ ፡፡ጥያቄ የምንጠይቅበት ሌላው መንገድ፡የእግዚአብሄርን ምህረት የተለማመዳችሁበትን ወቅት ታስታውሱታላችሁ ሊተውላችሁ የማይገባውን በደል የተተወላችሁን ግዜ?________________________________________

___________________________________________________________________________

እስራኤላውያን በምህረት እና በፀጋ በሚሞሉበት ግንኙነት ነው ከእግዚአብሄር ጋር የኖሩት፡፡እነሱን የርሱ ህዝቦች እራሱን ደግሞ የእነሱ አምላክ አድርጎ ነው ያወጀው፡፡ይህ

ግንኙነት ነው እስራኤልን ከሌላው ህዝብ የተለየ የሚያደርገው ከግብፃውያንን ጨምሮ ማለት ነው፡፡በዘፀአት 8፡23 ላይ እንደተገለፀው እግዚአብሄር በህዝቡ እና በፈርኦን ህዝብ መካከል ልዩነት አድርጓል፡፡ብግብፅ ላይ ካመጣው ሞት ህዝቡ ተዘልሎ እንዲኖር አድርጓል (ዘፀአት 9፡4)

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር አምላኬ ሆይ አንተ አምላኬ ነህ እኔም ከህዝቦችህ መካከል አንዱ አድርገኸኛል፡፡ስለዚህም ደግሞ ክብር እና ምስጋና አቀርብልሀለሁ፡፡መልካምነትህን አሳይተኸኛል፡፡በረከትህንም በእኔ ላይ አድርገሀል፡፡ህይወት አስቸጋሪ በሚሆንብኝ ግዜ እንኳን አንተ አምላኬ እንደሆንክ ሳስብ መፅናናት እና ተስፋ ውስጤ ይሞላል፡፡ዘላለማዊ በሆነው ፍቅርህ ጌታዮ እና መድሀኒቴ በሆነው በልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ ወደኸኛል፡፡ሁልግዜ በህይወቴ ምህረትህን እና ፀጋህን እንዳስብ አድርገኝ፡፡ምህረትህ በእኔ ላይ ይሁንልኝ ሁልግዜ አዲስ በሆነው በጎነትህ ውስጥ እንድኖር አይኖቼን ክፈትልኝ፡፡________________________________

______________________________________________________________________

**ክፍል 3**

***መግቢያ፡*** ቀጣዮቹን ሁለት መቅሰፍቶች ማጥናት ለግዜው ቆም አድርጉ ፡በክፍል 3 እንዳደረጋችሁት አሁንም እነዚህን ሳጥኖች ሙሏቸው፡፡

*መቅሰፍት ቁጥር 8፡ የ___________________________መቅሰፍት*

| ጥቅሶች | ተመሳሳይነታቸው | ምልከታ | የግል አስተያየት |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 10፡1 | | | |
| ዘፀአት 10፡2 | | | |
| ዘፀአት 10፡3-6 | | | |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 10፡7 | | | |
| ዘፀአት 10፡8-9 | | | |
| ዘፀአት10፡10-11 | | | |
| ዘፀአት 10፡12-15 | | | |
| ዘፀአት10፡16-20 | | | |

መቅሰፍት ቁጥር 9 ፡የ_______________________________መቅሰፍት

| ጥቅሶች | ተመሳሳይነታቸው | ምልከታ | የግል አስተያየት |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 10:21 | | | |
| ዘፀአት 10:21 | | | |
| ዘፀአት 10:22-23 | | | |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀአት 10:24-26 | | | |
| ዘፀአት 10:27-29 | | | |

**<u>ክፍል 4</u>**

መግቢያ ፡ ዘጠኙ መቅሰፍቶች ግብፃውያንን የማይፈልጉትን እንዲያደርጉ አስገድደዋቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚደረግ መቅሰፍት የለም፡፡የግብፅ በኩሮች የሞቱበት መቅሰፍት ምንም አይነት ሳይንሳዊ ማብራሪያ የለውም፡፡ እንደሚታወቀው ተራ የተፈጥሮ ክስተት አይደለም፡፡የምድሪቱን በኩራት በማጥፋት እግዚአብሄር ከፈርኦን አማልክት እንደሚበልጥ አሳይቷል፡፡እግዚአብሄር እጅግ ኃይለኛ ነው ይህ ኃይሉ ደግሞ እንደገና መገለጥ አለበት፡፡አሁንም ገና ፈርኦን እስራኤላውያን ሀገሪቱን ለቀው እንዲወጡ እንዲለቃቸው የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ አሻፈረኝ ብሏል፡፡የግብፅን በኩር መምታት እግዚአብሄር በባለስላጣናቱ፣በገዢዎች፣እንዲሁም በመላው ግብፅ ላይ ያደረገው ትልቁ ፍርድ ነው፡፡

**የቤት ስራ፡**

1. ጌታ ለሙሴ በፈርኦን እና በግብፅ ላይ የመጨረሻውን መቅሰፍት ሊያመጣ እንደሆነ ነገረው፡፡ሌላስ ለሙሴ የነገረው ነገር ምንድነው?________________________________
2. ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል፡፡ግዜውም ትክክለኛ ግዜ ነው፡፡በመጨረሻ እስራኤል ከፈርኦን አገዛዝ ነፃ መውጣት አለባቸው፡፡በርግጥ ማብቃት አለበት እስራኤላውያን በሙሉ ከግብፅ ምድር ሙሉ በሙሉ መውጣት አለባቸው፡፡በቁጥር 12 ላይ እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን የሰጠው መመሪያ ምን ነበር?________________________እግዚአብሄር እስራኤላውያንን ግብፆችን ለመበዝበዝ እንዲዘጋጁ ነገራቸው!የግብፅን ብልፅግና መበዝበዝ አለባቸው፡፡

**ክለሳ** ፡እስራኤላውያን ከዚች በመቅሰፍት ከተመታች ሃገር  ብር አና ወርቅ በዝብዘው ሊወጡ ነው፡፡ በባርነት እና በአስከፊ ጭቆና እና በክፉ ገዢዎች ስር ከኖሩባር ግብፅ ሊወጡ ነው የሚወጡትም  አንደባሪያ ሳይሆን አንደ ባለድል  ሆነው ነው፡፡

1. በዘፀአት 3፡21-22 እግዚአብሄር ለሙሴ ቃል የገባለት ነገር ምንድነው?____________

____________________________________________________________

2. እነዚህን ቁጥሮች ማንበብ ከጀመርንበት ግዜ ጀምሮብዙ ነገሮች ተከስተዋል፡፡እግዚአብሄር የተናገራቸው ነገሮች ምንያህል የማይፈፀሙ እና የማይሆኑ ይመስሉ እንደነበር አስታውሱ፡፡ወደኋላ ተመልሰን ስንመለከት ሙሴ ስለመሪነት ችሎታው ከእግዚአብሄር ጋር ሲከራከር አናገኘዋልን፡፡በእስራኤላውያን የተሾሙትም የራሳቸው ወገን ተቆጣጣሪዎችም ሙሴን ተቃውመውታል ምክንያቱም የራሳቸውን ገለባ ሰብስበው ጡቦችን አንዲሰሩ ተደርገዋልና ነው፡፡ስለነበሩበት ሁኔታ ሌላ የምታስታውሱት ነገር ምንድነው?______________________________________________

   ____________________________________________________________

3. ሕዝቡ በእግዚአብሄር ከተመረጠው መሪ ሙሴ ጋር ምን አይነት ግንኙነት ነበራቸው፡፡ከመቅሰፍቱ በኋላስ ግንኙነታቸው በምን መልኩ ተለወጠ?______________

   ____________________________________________________________

4. የእግዚአብሄር ህዝቡን ነፃ የማውጣት ስራ የጀመረው ገና በሁለቱ ህዝቦች መካከል ልዩነት ሲያደርግ ነው፡፡ከታች በተዘረዘሩት ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሄር እስራኤላውያንን ነፃ ለማውጣት ባደረገው ነገር በሁለቱ ህዝቦች መካከል የነበረው ልዩነት ምን ነበር?

   ሀ. ዘፀአት 8፡22______________________________________________

   ለ. ዘፀአት 9፡4_______________________________________________

   ሐ. ዘፀአት 9፡26_____________________________________________

   መ. ዘፀአት 11፡7_____________________________________________

**ስለእግዚአብሄር የተማርነው ነገር** ፡እነዚህ ምእራፎች የሚናገሩት እግዚአብሄር በእስራኤላውያን እና በነፃ መውጣታቸው መካከል ያለውን ልዩነት ማድረጉን ነው፡፡ስለ እግዚአብሄር ማንነት እና ባሕሪ የምንማረው ነገር ምንድነው?________________________________________

______________________________________________________________

**መልመጃ፡**

1. ክፉ እና አመፀኛ ከነበረው ፈርኦን በተቃራኒው ዘፀአት 11፡3 ስለ ፈርኦን ባለስልጣናት እና ስለህዝቡ ምን ይነግረናል?________________________________________
2. በዘፀአት 10፡28 ላይ ፈርኦን ሙሴን " ከእኔ ዘንድ ሂድ ፊቴን ባየህበት ቀን ትሞታለህና ፊቴን እንዳታይ ተጠንቀቅ አለው።"ብሎ ከፊቱ አስወጥቶታል።ነገር ግን ከፈርኦን ፊት ከመውጣቱ በፊት ዘፀአት 11፡4-7 ላይ የመጨረሻው መቅስፍት ምን እንደሚሆን ነገረው።ይህም መቅሰፍት የሰውን ህይወት የሚወስድ ሞት ነበር።የግብፅ በኩር በሙሉ ይሞታል።የእንሰሳት በኩር ሰይቀር ይሞታል።ለዛ በፊት ሆኖ የማያውቅ መከራና ሀዘን በምድሪቱ ላይ ይሆናል።በዚህ ሁሉ እራሱን እንደ አምላክ የሚቆጥረው የፈርኦን ልብ ግን አንደደነደነ ነበር።ነገር ግን የእሱ ንጉስነት እግዚአብሄር በግብፅ ምድር ላይ ከፈረደው ፍርድ በኩሩን እግዚአብሄር ፍርድ ሊያስመልጥለት አልቻለም ነበር።ከታናሽ ጀምሮ እስከ ታላለቆች የሁሉም ግብፃውያን በኩር ይሞታል።ሙሴም የመጨረሻውን ቃሉን ተናግሯል።ለዚህ መቅሰፍት በግብፃውያን ዘንድ የመጣው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 6)?__________________________________________________________

   ______________________________________________________________
3. በቁጥር 7 መሰረት እስራኤላውያንስ?____________________________________ታላቁ ልዩነት መደረግ አለበት።በእስራኤላውያን ሰፈር አንዲትም እንባ አልፈሰሰችም።
4. መቼ ነበር ሙሴ ግብፅን የመልቀቂያ ግዜው አንደደረሰ ያወቀው (ቁጥር 8)?__________________________________________________________

   ______________________________________________________________

ዘፀአት 5፡1-4 ላይ ፈርኦን ሙሴን እና አሮንን ከፊቱ ሲያስወጣቸው አንመለከታለን ከመጀሪያው ግዜ ጀምሮ ብዙ ነገሮች አልፈዋል።ፈርኦን በተደጋጋሚ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሄር እውቅና አልሰጥም በሏል።እግዚአብሄርም በተደጋጋሚ የፍርድ እጁን በግብፅ ላይ ዘርግቷል።አሁን ምድሪቱ ጠፍታለች።ቀጥሎ ሊሆን የሚችለውን ነገር ከመከታተል ውጪ ምንም ማድረግ አንችልም ።ሙሴም ለፈርኦን መጨረሻ ላይ የሚሆነውን መቅሰፍት ነግሮታል።እውነቱን በግልፅ ነው የነገረው።ቁጥር 8 እንዲህ ይላል።"ሙሴም በጽኑ ቁጣ ከፈርዖን ዘንድ ወጣ።"ሙሴ አሁን ከፈርኦን ጋር ጨርሷል።

አስታውሱ በዘፀአት 10፡28 ላይ ፈርኦንም የመጨረሻ ቃሉን የተናገረ እንደሚመስል አይተናል፡፡ዘፀአት 11፡8 ስናነብ ሙሴም የመጨረሻውን ቃል መናገር ብቻ ሳይሆን ቁርጡንም እንደነገረው እንመለከታለን ፡፡ያም ከመጨረሻው መቅሰፍት በኋላ የፈርኦን ባለስልጣናት የእስራኤልን ህዝቦች እንደሚለምኗቸው እንደውም ፈርኦን እራሱ ህዝቡን ከምድሪቱ ለማስወጣት እንደሚነሳ ተናግሯል፡፡እስራኤላውያን ምድሪቱ ለቀው ሲሄዱ ግብፃውያን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ ከዚህ ቀደም ካለቀሱት በላይ ያለቅሳሉ ፡፡አሁን የእግዚአብሄር ድንቅ በግብፅ ምድር በዝቷል(ቁጥር 9)፡፡

<u>**ክፍል 5**</u>

***መግቢያ፡*** ወደ ምእራፍ 12 ከመሄዳችን በፊት እግዚአብሄር ሊያደርጋቸው ያሉትን ነገሮች ጠቀሜታቸውን እንመለከታለን፡፡ቁጥር 5 ላይ ሙሴ ለፈርኦን "በግብፅም አገር ያለ በኵር ሁሉ፥ በዙፋኑ ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በወፍጮ እግር እስካለችው እስከ ባሪያይቱ በኵር ድረስ፥ የከብቱም በኵር ሁሉ ይሞታል፡፡"

**በጥልቀት *መመልከት፡*** ሁሉን አዋቂ የሆነው አምላክ በሙሴ እጅ የተከናወኑት ድንቅና ተአምራት በሙሉ የፈርኦንን ሀሳብ እንደማያስቀይሩት ያውቅ ነበር፡፡እግዚአብሄር ፈርኦን ልቡን እንደሚያደነድን የፈርኦንን ልብ ያደነደነው ደግሞ እራሱ አግዚአብሄር ስለሆነ ማንም ፈርኦንን ልብ መቀየር አይችልም፡፡ህዝቡን ከተገዙበት ባርነት ነፃ ሊያወጣቸው  የሚችለው እግዚአብሄር አንጂ የፈርኦን ፈቃደኝነት አይደለም፡፡

1. በዘፀአት 4፡22-23 ላይ እግዚአብሄር ሙሴን ለፈርኦን ምን እንዲነግረው አዘዘው?እግዚአብሄር እንዲህ ይልሃል "______________የበኵር ልጄ ነው ___________________ዘንድ_________________አልሁህ አንተም _____________ ዘንድ እንቢ አልህ እነሆ እኔ ________________________ ትለዋለህ፡፡"
2. ለመሆኑ የበኩር ልጅ ጥቅም ምንድነው?እስቲ መዝሙር 78፡51 ገልጣችሁ ተመልከቱ፡፡ይህ ክፍል ስለበኩር ልጅ ምን ይናገራል?_________________________

   _______________________________________________________________________
3. የበኩር ልጅ የአንድን ህዝብ ብርታት የሚያሳይ ነገር ነው፡፡የበኩር ልጅ የአንድን አባት ሙሉ ሰው መሆን የሚያሳይ ነው፡፡ የህዝብን ጥንካሬ የሚያሳይ ነው፡፡እግዚአብሄር እስራኤል የበኩር ልጁ እንደሆነ ተናግሯል፡፡በእስራኤል በኩል

የእሱ ብርታት እና ኃይል ይገለጣል።ይህ ግጥሚያ የፈርኦን እና ኃያል እና ሁሉን የሚችል አምላክ የእግዚአብሄር ግጥሚያ ነው።አሁን በዘፀአት 11:5 ላይ እንደምንማረው በመጨረሻው መቅሰፍት የግብፃውያን በኩር ሀሉ ይሞታል።ይህ ለግብፃውያን እና ለፈርኦን ምን ማለት ይሆን ?ለፈርኦን ብረታት እና ጥንካሬስ ምን ማለት ይሆን____________________________________________________

______________________________________________________________አሁን ጠንካራው ማነው?ከሁሉ በላይ ኃይል ያለው ማነው?_______________እግዚአብሄር በኩሩ የሆነውን እስራኤልን በህይወት እና ኃይል አስታጥቆ ግብፃውያንን ግን በኩራቸውን እና የከብቶቻቸውን በኩር በሞት መታ።

*መስታወሻ፡ በዚህ ጥናታችሁ ላይ አንዳንድ ኃሳቦችን ላትረዷቸው ትችላላችሁ።ተስፋ አትቁረጡ።በሚቀጥሉት ጥናቶቻችን በስፋት እንዳስሳቸዋለን።በዚህ ጥናታችን የግብፃውያን በኩር መሞት ለእግዚአብሄር የበኩር ልጆች ለሆኑት ለእስራኤላውያን የአምላካቸውን ታላቅነት እና ኃይለኛነት ማሳያ ነው።*

**ትምህርት፡**ልንደፍረው የማንችለው በኩር በሉቃስ 2:7 ላይ አለ።ምናልባት ይህንን ክፍል በደንብ ታውቁት ይሆናል ቃሉ እንደዚህ ይላል። "_________________ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።"ይህን ክፍል ገና ዛሬ መስማታችሁ ከሆነ ግዜ ወስዳችሁ ሉቃስ 2:1-20 ማንበብ አለባችሁ።ይህ ዘገባ የእግዚአብሄር አንድያ እና ብቸኛ ልጁ የሆነው የእየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ ነው።በዮሐንስ 3:16 ላይ "በእርሱ___________________ሁሉ ___________________እንዲኖረው እንጂ ________________________እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" እግዚአብሄር ኃይሉን እና ብርታቱን በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ገልጦልናል።በበኩር ልጁ ሞት እና ትንሳኤ ነው የሲኦል ኃይል እና ክፋት ሁሉ የተደመሰሰው።ኃጢአት፣ሞት እና ዲያብሎስ ኃይላቸውን ያጡት በክርስቶስ እየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ነው።ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን 1:19:20 ላይ ክርስቶስን ከሞት ያስነሳው ያው መንፈስ ለምናምን ለእኛም እንደሆነ ይነግረናል ።

**ስለ እግዚአብሄር የተማርነው፡** *የመጨረሻው መቅሰፍት ሊከናወን ነው ነገር ግን እግዚአብሄር ያንን ከማድረጉ በፊት ስፍራ ማስያዝ ያለበት ነገር አለ።-ይህን ክፍል ከማንበባችን በፊት*

ትንፋሻችሁን ሰብሰብ አድርጉ፡፡የእግዚአብሄር ምህረት ለእስራኤላውያን እንደበዛላቸው ተመልክተናል፡፡እነሱ ህዝቦቹ ናቸው፡፡ከእነሱ ጋር ያለው ግንኙነት አንድ አባት ከልጁ ጋር እንዳለው አይነት ግንኙነት ነው፡፡ለእነሱ ያለው ፍቅር ከተገዙብት የባርነት ቀንበር ነፃ ሊያወጣቸው እንዲመጣ አድርጎታል፡፡እውነተኛ የሆነው ፍቅሩ ፈርኦን በእነሱ ላይ መከራን ሲያበዛባቸው ፀጥ ብሎ እንዲመለከት አላስቻለውም፡፡እምላካችን መልካም ፣ባለፀጋ፣እና ቅዱስ አምላክ ነው፡፡ሁሉን የሚያውቅ እና ሁሉን የሚችል አምላክ ነው፡፡ለበኩር ልጁ ለእስራኤል ያለው ፍቅር በክፉው ላይ እንዲነሳበት አድርጎታል፡፡እግዚአብሄር ፍቅሩን ለእስራኤላውያን ሲገልፅ እኔ እና ለእናንተም እየገለፀ ነው፡፡

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር ሆይ አንተ ለእኛ መሃሪ ነህ፡፡እራሳቸውን ለማዳን ኃይል እንደሌላቸው ባየህ ግዜ እስራኤላውያንን በእነሱ ፋንታ አንተ ተዋጋህላቸው፡፡ተስፋቢስ እና ደካማ ሆነው ባሉበት ስፍራ መጥተህ ፈርኦንን እና ባለስልጣናቱን ተዋጋህላቸው፡፡ልክ ለእስራኤላውያን ውጊያቸውን እንደተዋጋህላቸው እንደዚሁ ለእኔም እለት ተእለት ውጊያዬን ተዋጋልኝ፡፡በእኔ ፋንታ ስራዬን ስለምትሰራልኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ከአንተ የተነሳ ተስፋ እና ብርታት ያለው ህይወት እኖራለሁ ፡፡____________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# የጌታ ፋሲካ ነው

## ዘፀአት 12-13- ይህን ቀን አስታውሱ

---

**የትምህርት 6 ቅኝት**

ቅኝት

በግቢያ

ትምህርት 6፡ ዘፀአት 12-13

- ተጠሩ
- የፋሲካው መመሪያ
- በበጉ ደም መዳን
- የበኩር ቅስፈት
- የእስራኤል ከግብፅ ነፃ መውጣት
- ነፃ መውጣቴ

## መግቢያ

የፈርኦን ልብ አሁንም አልተለወጠም፡፡አሁን ጌታ እግዚአብሄር የመጨረሻውን ፍርድ ሊያደርግ ነው፡፡ህዝቡንም ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር እያዘጋጀው ነው፡፡

ይህን ነገር ልዮ ያደረገው ምንድነው?ለዚህ ምሽት አንደዚህ አይነት የተለየ መመሪያ ያስፈለገው ለምንድነው? ለምን አንደዛ እንደሆነ በቅርቡ ይገባቸዋል፡፡ይህንን ትምህርት ስታጠኑ የፋሲካን ጥቅም ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡የበጉን ጥቅም ለመረዳት ሞክሩ፣በደም የተቀባውንም ጉበን፣እርሾ ያልገባበት ዳቦ፣አና የተለየው አለባበስ እነዚህን ሁሉ እግዚአብሄር ለዚህ ምሽት በሰጠው መመሪያ ውስጥ ተካተዋል፡፡

እና የመጨረሻው መቅሰፍት ምንድነው? የበኩር መሞት ጥቅሙ ምንድነው?ፈርኦንን አና ግብፃውያን እስራኤላውያን ከሀገራቸው እስኪወጡላቸው ያጓጓቸው ምንድነው?ምድሪቱንም ሲለቁ እስራኤላውያንን ከግብፃውያን ብር እና ወርቅ እንዲጠይቋቸው መብት የሰጣቸው ምንድነው?

በመጨረሻም ከ 430 አመት በኋላ "የእግዚአብሄር ሰራዊት በሙሉ ግብፅን ለቆ ወጣ……ይህ ሌሊት በእግዚአብሄር የመነብኛ ሌሊት ነው፡፡

## ክፍል 1

**መግቢያ፡** እግዚአብሄር ለህዝቡ ይህን ሌሊት የሞት መልአክ የእስራኤላውያንን ቤት እያለፈ በኩርን ከሚገደለው መቅሰፍት ተዘልለው እንዲቀመጡ ይህንንም እንዲያስታውሱት ፈልጓል።የማስታወሻ እራት እንዲያደርጉ መርጧል።ይህ የመጨረሻው ግብዣ ነው ይህንን ታሪካቸውን እንዳይረሱት የሚያደርጋቸው ግብዣ ነው።ይህን ፋሲካ በየ አመቱ ያደርጉታል ከትውልድ ትውልድም ይሸጋገራል።የዚህ ትምህርት አላማ እግዚአብሄር ስለፋሲካ ስለሰጣቸው መመሪያ ስለፋሲካው ስርአት ለመዘርዘር ሳይሆን እግዚአብሄር ህዝቡን እንዴት ከተጨቆኑበት ባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው እንድንረዳ ነው።

**የቤት ስራ፡**ዘፀአት 12፡1-51 ያለውን ክፍል አንብቡ።የምእራፍ አስራሁለት ቀላል ዝርዝር ነው።

- ቁጥር 1-20 እግዚአብሄር እያንዳንዱ ቤተሰብ ለመንገዱ እንዲዘጋጅ ለሙሴ እና ለአሮን መመሪያ የሰጠበት ነው፡
- ቁጥር 21-28 ሙሴ ለሽማግሌዎች መመሪያ የሰጠበት ነው።
- ቁጥር 29-30 የግብፅን በኩር የሚያጠፋው መቅሰፍት
- ቁጥር 31-35 መመለስ የእግዚአብሄር ህዝቡን ነፃ ማውጣት እስራኤልን ከግብፅ ማውጣቱ

**ክለሳ፡** በዚህ ትምህርት እግዚአብሄር በሙሴ እና በአሮን በኩል ለህዝቡ የሰጠውን መመሪያ አንመለከታለን።ሙሴ ልክ መመሪያውን እንደተቀበለ የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰብስቦ በቁጥር 21 ላይ ሊከተሉት የሚገባቸውን መመሪያ ነገራቸው።ጥሪያቸው ይህ ነበር።ነፃ መውጣታቸው ይህ ነው።ከባርነት ነፃ የወጡት እግዚአብሄርን ለማገልገል ነው።እስቲ እግዚአብሄር ህዝቡን ነፃ ለማውጣት ቃል የገባበትን የዘፀአትን መጀመሪያ ክፍል ግዜ ወስዳችሁ ከልሱት።

1. ዘፀአት 3፡7-10 ያለውን ክፍል አንብቡት። እግዚአብሔርም አለ፦ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን___________በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ___________ሰማሁ ________________አውቄአለሁ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ ከዚያችም አገር _________________ና ________________ ወደምታፈስሰው አገር ወደ________ወደ _______________አገር ወደ______________ወደ______________ወደ አሞራውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም __________________ዘንድ

ወረድሁ፡፡አሁንም እነሆ የእስራኤል ልጆች________________ወደ እኔ ወጣ ግብፃውያንም ___________________ደግሞ አየሁ፡፡

2. ዘፀአት 6፡2-5 አንብቡ፡፡ እሱ_____________ነው፡፡እሱ ግብፃውያን___________ነፃ ያወጣቸዋል፡፡

 ሀ. ከእነሱ ጋር ___________________ፈፅሟል______________

 ለ. ለ________________ቃልኪዳን ገብቷል____________በተረዘረጋች__________ በፀናች__________________________

 ሐ. እንደራሱ__________________አድርጎ ሊወስዳቸው ቃል ገብቶላቸዋል እናም የእነሱ___________________ከግብፃውያን ቀንበር ነፃ አወጣቸው፡፡በቁጥር 8 ላይ ለአነሱ________________ቃል ገብቶላቸዋል_________________________ብሎም ሊሰጣቸውም ሎላቸዋል፡፡ለዘሮቻቸውም__________________________ሊሰጣቸው ምሎላቸዋል፡፡እስራኤልም___________________አንደ__________________ሊሰጣ ቸው ቃል ገብቶላቸዋል፡፡

በመጨረሻም ቃልኪዳኑን እንዲህ በሚለው ቃል አተመው “______________________”

**መልመጃ፡** (ዘፀአት 12፡ 1-28)

1. በቁጥር 1 እና 2 እግዚአብሄር ለሙሴ አና ለአሮን የፋሲካ በአልን አከባበር ነገራቸው በአሉም የሚከበረው ሙሉ ጨረቃ በሚሆንበት ወቅት አንደሆነ ነገራቸው፡፡ የመጀመሪያው ወር የኒሳን ወር ይባላል (በአይሁዶች የዘመን አቆጣጠር)
2. በቁጥር 3 መሰረት ሙሉ ጨረቃ በወጣች በአስረኛው ቀን ምን ይሆናል?____________

 ________________________________________________________________________

3. የሚታረዱት በጎች በሙሉ በተሰላ ሁኔታ በጥንቃቄ መከፋፈል አለባቸው፡፡አከፋፈሉም በ______________________________________________የተመሰረተ ነው፡፡(ቁጥር 4)
4. በቁጥር 5 ላይ የረዘረዘሩት ዋና ነገሮች ምንድናቸው?

 ሀ.___________________________________________

 ለ. __________________________________________

5. በጉ የሚመረጠው በ10ኛው ቀን ነው፡፡በአስራአራተኛው ቀን ምን ይሆናል ቁጥር 6?___

 ________________________________________________________________________

6. በቁጥር 7 መሰረት በታረደው በግ ደም ምን ያደርጋሉ ?______________________

____________________________________________________________

7. በቁጥር 13 ላይ የደሙ የሚጠቅመው ለምንድነው?____________________________
8. ስጋው በእሳት ላይ__________________ይደረጋል ከ_________________ጋር ዳቦም ___________________________ሳይኖረው ይጋገራል (ቁጥር 8)

   ስጋው በዛው ሌሊት ተበልቶ ማለቅ አለበት ::ለነገ ቁርስ ወይንም ምሳ በሳንድዊች መልክ ማስቀመጥ አይቻልም።ምግቡ በምን አይነት ፍትነት እንደሚዘጋጅ ልብ በሉ።ለምሳሌ እርሾ የሌለው ዳቦ እርሾ ካለው ዳቦ ፈጥኖ ይዘጋጃል።
9. በቁጥር 9 ላይ አንድ የሚያስደስት ነገር አናገኛለን።የታረደው እንሰሳ ሙሉ በሙሉ መጠበስ አለበት።አጥንቶቹ አይሰበሩም ::ይህን ክፍል ስታጠኑ ይህንን ነገር አስታውሱ።ቁጥር 10 ላይ የተረፈውን ምግብ ምን ነበር የሚያደርጉት?____________

   ____________________________________________________________
10. እንደገና በቁጥር 10 ላይ እስራኤላውያን ለመሄድ ዝግጁ ሆነው እናገኛቸዋለን።እንዴት ነበር የተመገቡት?

    ሀ. ወገብ መታጠቂያ፡ ____________________________________________

    ለ. ጫማ: _______________________________________________________

    ሐ. በትር: ______________________________________________________

    በመጨረሻም በ______________________ብሉት።የጌታም__________________________

<u>**ክፍል 2**</u>

**ትምህርት፡** የእግዚአብሄር መመሪያ ግልፅ እና ቀጥተኛ ነው።ለጉዞአቸው እንዲያደርጉ እንደፈለገ እግዘዚብሄርን ሊከራከረው የሚችል ማንም የለም።አሁን እነዚህ የእግዚአብሄር ህዝቦች ለሚያደርጉት ጉዞ በደንብ ተመግበው እንዲጠነክሩ ፈልጓል፤ይህ ምግብ እንደሌሎቹ አይነት ምግብ አይደለም።ይህ በህብረት የመሰብሰብ እና የመዝናናት ግዜ አይደለም።ሁሉም ሰው ልብሱን ታጥቆ ለጉዞው የተዘጋጀ መሆን አለበት።በቁጥር 12 እና 13 ላይ እግዚአብሄር ለሙሴ እና ለአሮን የፋሲካው በግ በሚበላበት በዛው ምሽት በግብፃውያን መንደር እንደሚያልፍ እና የግብፃውያንን በኩር እንደሚገድል በምድራቱም አማልክት ላይም ፍርዱንም እንደሚያደርግ ነገራቸው።እንደገናም እንዲህ አላቸው፡፤"እኔ እግዚአብሄር ነኝ" በዚህ ሌሊት የእስራኤላውያን ህይወት የተመሰረተው በጉበናቸው ላይ በሚቀቡት ደም ነው።እግዚአብሄር ደሙን እስራኤላውያን የት እንደሚገኙ ለማየት ስለማይችል ለራሱ ምልክት አይደለም የፈለገው ነገር

ግን ደሙ የእምነታቸው ምልክት ነው፡፡ደሙ የተቀባበትን ቤት ሁሉ የሞት መልአኩ እንደሚያልፈው እንዲያውቁ ፈልጓል፡፡ደሙ የእግዚብሄርን ቃል ሰምተው በእምነት ከጥፋት ለሚድኑት ምሳሌ ነው፡፡

**ገለፃ፡** እስቲ ለትቂት ቅጽበት ቆም እንበል፡፡የተፈጠሩትን ሁኔታዎች ከህይወታችን ጋር በማዛመድ እንደመልከታቸው፡፡

1. አንደኛው ገለፃ ካለፈው ነገራችን ጋር ይገኛል፡፡የምታስታውሷቸው ሰዎችን ባህሪ የቀየሩ ክስተቶች ታውቁ ይሆን?ለምሳሌ አሮን እና ሙሴ ወደ ከተማ ተመልሰው ሲመጡ በዘፀአት 29 ላይ በህዝቡ እና በሽማግሌዎቹ ዘንድ ምን አይነት ተቀባይነት ነበር ያገኙት?እግዚአብሄር አነዚህን ሰዎች ምን ሊያደርግ እንዳለ እንደነገራቸው አስታውሱ ፡፡መቅሰፍቶቹን እና የነበረውን ሁኔታ አስታውሱ፡፡______________________________
___________________________________________________________________
2. እስራኤልንም ልናያት ያስፈልገናል፡፡እስቲ አራሳችሁን በዛን ወቅት በአንደኛው ቤት ውስት የምትኖሩ እስራኤላዊ እድርጋችሁ አስቡ፡፡እነዚህ መመሪዎች ተሰጥተዋችኋል፡፡ከ 400 አመት በላይ ከብዙ ትውልድ በኋላ ዛሬ ማታ የኖራቸሁበትን እና የለመዳችሁትን የምታውቁትን ሰስፍራ ትታችሁ ልትወጡ ነው፡፡በዛን ሰአት ልታስቡት የምትችሉት ነገር ምንድነው?____________________________________________
___________________________________________________________________
3. አሁን እናንተና ቤተሰቦቻችሁ በሞላ አንድ አመት በሞላው እንከን የሌለበት በግ ደም በጉበናችሁ በመቀባታችሁ የተነሳ ሞት የእናንተን ቤት አልፎ እንደሚሄድ እና በኩራችሁን እንደማይገድል እንድታምኑ ተነግሯችኋል፡፡ትኩር ብላችሁ ወደልጆቻችሁ አይን እየተመለከታችሁ ነው፡፡እሱ ምናልባት ንፁህ እና ስለሚሆነው ነገር ምንም ያላወቀ ወይንም ደግሞ እድሜው ከፍ ያለ ሆኖ ስለሚሆነው ነገር በደንብ የተረዳ ሊሆን ይችላል፡፡ወይ ደግሞ አናንት እራሳችሁ የበኩር ልጆች ትሆኑ ይሆናል፡፡አሁን ጌታ ሊገለጥ እና የግብፅን በኩር ሊመታ ነው ስለዚህ ጉዳይም ከራሳችሁ ጋር ወይንም ደግሞ እርስ በእርስ ስለምን ትነጋገራላችሁ?______________________________________
___________________________________________________________________

ግብፃውያን ስለሚሆነው ነገር ምንም ማለት አይችሉም ፡፡እሁን የእኩለ ሌሊቱ ሰአት እየቀረበ ነው፡፡

*ማስታወሻ፡ በዚግ ግዜ አንዳንድ ተማሪዎች የታሪኩን መጨረሻ ለማወቅ ከማንጓታቸው የተነሳ ማጥናቱን መቀጠል ሊፈልጉ ይችላሉ ።ሌሎች ደግሞ ይህን የማይሻር ታሪክ በጥልቀት ለመመልከት ፍላጎት ይኖራቸው ይሆናል። የዚህን ታሪክ ቀጣይ ነገር ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት ያደረባቸው ሰዎች ቀጥሎ ያለውን በጥልቀት መመልከት የሚለውን ክፍል መመልከት ይቀጥሉ ከዛም ክፍል ሶስትን ተከትሎ ያለውን የቤት ስራ በደንብ ይስሩት ።*

**በጥልቀት መመልከት፡** በሚቀጥሉት ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለቀጣዩ ትውልድ መመሪያን አስቀምጧል።ይህ የፋሲካ ወይንም እርሾ የሌለው ዳቦ በአል የእግዚአብሄር በአል ሆኖ በቁጥር 14 ላይ እንዲከበር አዟል።በአሉ ለሰባት ቀን ይከበራል ።የበአሉን ዋና ዋናዎቹን ክፍሎች እንመልከት።

1. ቁጥር 15፡ ለሰባት ቀን________________________________________
2. ቁጥር 15 በመጀመሪያው ቀን____________________________________
3. ቁጥር 15 እርሾ ያለው ነገር የበላ________________________________
4. ቁጥር 16 በመጀመሪያው ቀን____________________________________
5. ቁጥር ቀ6 ____________________________________________አትስሩ

**ማጠቃለያ፡** ቁጥር 17-20 ቀድሞ የተባለውን ነገር እንደገና ያሳስባል ።ይህ ቀን የሚከበርበት ምክንያት "እናንተን ከግብፅ ባርነት ያወጣሁበት እለት ስለሆነ ነው።" የሚለቀጥለው ትውልድ ይህንን ነገር ማስታወስ እና ማሰብ እንዲሁም የእግዚአብሄር ህዝብ ለሆነው ለእስራኤል ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል።በዚህ በአል ላይ እርሾ ፈፅሞ የተከለከለ ነው በቤት ውስጥ በምንም ስፍራ መገኘት የለበትም።እስራኤላዊ የሆነ ሰው ይህንን ነገር በምንም መልኩ መብላት የለበትም።ከእስራኤል ውጪ የትም ሃገር ይኑሩ የሚበሉት ነገር በሙሉ ከእርሾ የፀዳ መሆን አለበት።በቁጥር 24 እንዲሁም በቀጣዮቹ ክፍሎች ላይ ይህንን ትእዛዝ ሁሉም ሰው እንዲታዘዘው ይገባል።ይህ በአል እግዚአብሀሄር በሰጣቸው ምድር በገቡ ግዜ እንኳን መከበሩ የሚቀጥል ነው።

በቁጥር 26 ላይ ወላጆች ይህን ስርአት ለልጆቻቸው ማስተማር እንዳለባቸው ያዛል።ለልጆቻቸው ይህ በአለ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያስተምሯቸው ያዛል። ለእግዚአብሄር ምን ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እንዲያስተምሯቸው ይነግሯቸዋል።ቁጥር 27 ምን ይላል?__________________

________________________________________________________________ከዚህ ሁሉ በኋላ ህዝቡ ምላሽ ሰጠ። እነሱም_________________እራሳቸውን እና____________ቁጥር 28 እስራኤላውያን እንደታዘዙ ይነግረናል! ልክ ጌታ_____________________ሙሴ እና አሮን።

__ክፍል 3__

***መግቢያ*:** በዚህ በመጨረሻው መቅሰፍት የሚገርመው መቅሰፍቱን ለማውረድ እግዚአብሄር አሮንንም ወይንም ሙሴን ወይንም በትሩንም አልተጠቀመም።እነሱም እንደማንኛውም እስራኤላዊ አንክን በሌለበት የፋሲካ ደም በተቀባው ቤት ውስጥ ነበሩ ።እግዚአብሄር አብርሐም እና ዘለሩ ተስፋ ወደገባለት ወተት እና ማር ወደምታፈሰው መድር ለሚደረገው ጉዞ ልብሳቸውን ለብሰው ፣ጫማቸውን ተጫምተው ከግብፃውያን የባርነት ጭቆና ቀንበር ነፃ የሚወጡበትን ጉዞ ለማድረግ ተዘጋጅተዋል።

**የቤት ስራ፡** ዘፀአት 12፡29-42

***መልመጃ*:**

1. በቁጥር 29 እና 30 ላይ የተከሰተውን ነገር በራሳችሁ ቃል ግለፁት፡_________________
   ________________________________________________________________________
   ________________________________________________________________________
2. ዘፀአት 4፡21-23 እና ዘፀአት 11፡4-6 ያለውን ክፍል ግዜ ሰጥታችሁ አንብቡት።ሙሴ ለፈርኦን ምን ነበር የነገረው?_________________________________________________
   በዚህ ስፍራ ላይ የሚያስደንቅ ነገር አለው?ሁሉም ነገር በሙሴ በኩል እግዚአብሄር ይሆናል እንዳለው ነው የሆነው።
3. በቀላሉ በቁር 29 -30 ያለው ክፍል እገዚአብሄር የግብፃውያን በኩር በመግደል ታላቅ ጉዳት አንደጎዳቸው ይናገራል።ይህ መከራ የደረሰባቸው ወላጆች ምን አይነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል?ይህ ቅጣት አይበቃቸውም? ግብፃውያን በመሪያቸው ልበ ደንዳና ነት የመጣውን መከራ ተጋፈጡ።በመጨረሻም ሞትን ተጋፈጡ ። "_____የሌለበት__________ አልነበረምና በግብፅ ምድር ታላቅ ልቅሶ ሆነ።"
   **የቤት ስራ፡**ዘፀአት 12፡31-36 ያለውን ክፍል አንብቡ።

**መልመጃ፡** ከግብፅ የመመለሱ ጉዞ ሊጀመር ነው፡በእኩለ ሌሊት ፈርኦን ሙሴ እና አሮንን አስጠራቸው፡፡

1. ፈርኦን በቁጥር 31 አና 32 ፈርኦን ምን ነገራቸው?
   - ሀ. "ተነሱ ______________________________________________::"
   - ለ. "ሂዱም______________________________________________::"
   - ሐ. "______________________________________________ውሰዱ::"
   - መ. "እኔንም ደግሞ______________________________________________::"
2. የግብፃውያንን ጥድፊያ አስቡ፡፡ግብፅ ከእስራኤላውያን ነፃ እንድትሆን ግብፃውያን የፈለጉበት ምክንያት ምንድነው (ቁጥር 33)?______________________________
3. በቁጥር 34 ላይ እስራኤላውያን ግብፅን ለመልቀቅ እንዴት አንደተጣደፉ አብራሩ፡፡እስራኤላውያን በፍጥነት እንደለቀቁ አንዴት ማወቅ አንችላለን?_________

   ______________________________________________________________________
4. በቁጥር 35 እና 36 እስራኤላውያን ግብፃውያንን አንደበዘበዙይነግረናል፡፡እስራኤላውያን ምን ነበር ያደረጉት? __________________

   ______________________________________________________________________
5. እስራኤላውያን ግብፃውያንን አንዲበዘብዟቸው አንዴት አስቻላቸው?___________

   ______________________________________________________________________

## ክፍል 4

**ተምህርት፡** ከግብፅ የመውጣት ጉዞ ተጀመረ፡፡የዘፀአትን ካርታ በመፅሐፍ ቅዱሳችሁ ጀርባ ላይ ተመልከቱ፡፡በመጀመሪያ የጉዞው መነሻ የሆነችውን ራምሴን በካርታው ላይ አሳዩ፡፡ በሶኮት ደቡብ ምስራቅ ያለውን መንገድ ተከትላችሁ ሂዱ፡፡አስታውሱ ይህ መንገድ ለሙሴ አዲስ አይደለም፡፡ሙሴ የምድረበዳን ህይወት ያውቀዋል፡፡ከዚህ በፊት ይህንን ጉዞ አድርጓል፡፡ በዘፀአት 2 ሙሴ ግብፃዊውን ከገደለ በኊላ ህይወቱን ለማዳን በመሸሽ ሚስቱን ሲፖራን ወዳገኘበት ምድያም በዚህ መንገድ ሸሽቷል፡፡

**የቤት ስራ፡**ዘፀአት 12:37-42

**መልመጃ፡**

1. ከሴቶች እና ከህፃናት ውጪ ስንት ወንዶች ነበሩ ሊጓዙ የነበሩት ?________________________የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን የዚህን ክፍል ትርጉም ቁጥር ግምታዊ ወይንም ትክክለኛ ቁጥራቸው እንደሆነ እስካሁን መደምደም አልቻሉም፡፡እኛ ግን መፅሐፉ ላይ በተፃፈው መሰረት የእስራኤላውያን ቁጥር በጣም ብዙ አንደሆነ እናምናለን፡፡
2. ከእስራኤላውያን ጋር ተቀላቅለው የወጡር ቅይጥ ህዝቦእ እነማን ይመስሏችኋል ?__
   ____________________________________________________________
3. ከእስራኤላውያን ጋርስ ለመምጣት የፈለጉት ለምን ይመስላችኋል?_______________
   ____________________________________________________________
4. ከአጠቃላይ  ህዝቡ በተጨማሪ አብረዋቸው የሚጓዝ ምን ነበር?_________________
   ____________________________________________________________
5. በቁጥር 39 ላይ አንደገና የተገለፀው ምን ነበር?________________________________
   ____________________________________________________________
6. "እርሾ ያልገባበት ሊጥ" ህብስት የሚለው ቃል በድጋሚ የተገለፀው ለምንድነው?___________________________________________________
   ይህ ህብስት የተረለፀበትን በምእራፍ አስራ ሁለት ያለውን ቁጥር ግለፁ፡፡
   ሀ. ________________________________________________
   ለ. ________________________________________________
   ሐ.________________________________________________
   መ.________________________________________________
7. በቁጥር 40 መሰረት እስራኤላውያን ብግብፅ ምን ያህል አመት ኖሩ?_______________
8. በእነዚህ አመሮቶች መጨረሻ ላይ ምን ሆነ?_________________________________
9. ቁጥር 42 ስለ እግዚአብሄር ጥበቃ፣እና በእስራኤላውያን ህይወት ላይ የሚያደርገው ነገር በሙሉ ምን ይነግረናል?_____________________________________________
10. እስራኤላውያን ለእነሱ እና የሚመጣውም ትውልዳቸው እግዚአብሄር ላደረገላቸው ነገር በሙሉ ምን አይነት ምላሽ መስጠት አለባቸው?_________________________________

**ገለፃ፡** ይህንን ግዜ  በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ምንአይነት ስፍራ እንደሚኖረው አስቡ፡፡ ለብዙ ዘመን ግብፅ ውስጥ ነው የኖሩት፡፡በምድራቸው ከነአን ላይ ከፍተኛ ረሀብ ስለነበረ እሱን ለማሳለፍ ነበር የመጡት፡፡በዛን ግዜ የመጡት ቤተሰቦች በወንድማቸው እና በፈርኦን መልካም አቀባበል እና መስተንግሶዶ ተደርጎላቸዋል፡፡ከዛም በኋላ ሌላ ፈርኦን መጣ፡፡ዮሴፍን አያውቀውም እስራኤል ህዝብ መብዛት ደግሞ ተግዳሮት ሆኖበታል፡፡ስለዚህም ከባድ ስራ በማሰራት መከራ ያበዛባቸው ጀመር፡፡ለብዙ አመታት እንደባሪያ ተጨቆኑ፡፡ከዛም ጩኸታቸውን እግዚአብሄር ሰማ ሊያድናቸውም መጣ፡፡ሙሴ እና አሮን የተባሉትን ወንድማማቾች  ፈርኦን ፊት  ገብተው "ህዝቤን ልቀቅ" የሚለውን  መልእክት እንዲያደርሱ መረጠ፡፡ ከዛም በኋላ ከብዙ መቅሰፍቶች በኋላ በግብፅ ያሉ በኩሮች በሙሉ ከተገደሉ በኋላ ግብፅውያን እስራኤላውያንን ከሃገራቸው እንዲወጡላቸው ለመኗቸው፡፡ከሃገራቸው እንዲወጡላቸው ብራቸውን ፣ወርቃቸውን፣ልብሳቸውን እንዲሁም የለመኗቸውን ሁሉ ሰጧቸው፡፡እርሾ ሊጥ ውስጥ ተጨምሮ እስኪያቦካው ድረስ እንኳን ግዜ ሊሰጧቸው አልቻሉም፡፡

1. ቀድሞ ጎረቤታችሁ በሆኑ አሁን ግን አይናችሁን ማየት በማይፈልጉ ሰዎች እየተባረራችሁ እንደሆነ አስቡ ፡፡ለጉዞው ተዘጋጃችሁ?ለጎዞው ምንድነው ያዘጋጃችሁት?ጎረቤታችሁንስ ልትተይቁ ያሰባችሁት ነገር ምንድነው? እንድተሄዱላቸው ብቻ የጠየቃችሁትን በሙሉ ሊሰጧችሁ ተዘጋጅተዋል፡፡ግብፅን እንድታስታውሱ የሚያደርግ የምትወስዱት ነገር ምንድነው?በበረሃው ሊጠቅማችሁ የሚችል ልትወስዱት የሚገባችሁ ነገር ምንድነው?__________________________________________

   ____________________________________________________________________

2. ከፊታችሁ ምን እንደሚጠብቃችሁ ታውቃላችሁ?በእነዚህ ሁሉ አመታት የምታውቁት ጡብ መስራት እና ለፈርኦን የማከማቻ ከተማ ነው፡፡ከራምሴ ውጪ ምን ታውቃላችሁ?በርግጥ ሁሉም ሰው ወዴት እየሄደ እንዳለ አታውቁም፡፡የምታውቁት አንድ ነገር ሁሉም ሰው እቃውን ጭኖ እየሄደ ነው ስለዚህ ብቻችሁን ላለመቅረት እናንተም ተነስታችኋል፡፡እስቲ ስለዚህ ነገር ያላችሁን አስተያየት ግለፁ፡______________

   ____________________________________________________________________

3. ምን ያህል እንደምትጓዙ አውቃችኋል? በግብፅ ምድር ያፈራችኋቸውን ጎረቤቶቻችሁን እና ጓደኞቻችሁን በድጋሚ የምታይዋቸው ይመስላችኋል? ቤተአባችሁን እና እራሳችሁን ለመደገፍ ምን ልትሰሩ አስባችኋል? በዚህ ጉዞ ላይ  ስለእነዚህ አይነት ነገሮች

የምታስቡበት ግዜ ስለሌላችሁ መልካም ነው፡፡ይህን ብታደርጉ የጉዞ ሀሳባችሁን ልትቀይሩ እንደምታስቡ ታምናላችሁ?________________________________________

________________________________________________________________

4. ሌሎች ወደ ሀሳባችሁ የሚመጡ ነገሮች ምንድናቸው?_________________________

________________________________________________________________

**ትግበራ፡**

1. የእስራኤልን ታሪክ ስታንፀባርቁ ከእስራኤላውያን ጋር በተያያዘ በህይወታችሁ የሚንፀባረቅ ምን ነገር አለ? በጣም ታላቅ ለውጥ አለ? ድንገተኛ ለውጥስ አለ? ያልተረጋገጠ ለውጥስ አለ?______________________________________________

________________________________________________________________

2. በእነዚህ ሁሉ ግዜያት ለውጥ ይምጣም አይምጣም ነገር ግን በቀጣይነት መሆን አለበት ብላችሁ የምታስቡት ነገር ምንድነው?________________________________________

________________________________________________________________

3. እርግጠኛ እንዳንሆን ሊያደርጉን የሚችሉ ነገሮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?_____________

________________________________________________________________

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ በእነዚህ ሁሉ አመታት በብዙ ለውጦች ውስጥ አልፏል፡፡ ለውጥ ሁል ግዜ ለውጥን እንዳይረጋጋ ያደርገዋል፡፡ለውጥ በቀናነት ስለለውጥ አስቦ መነሳትን ይፈልጋል፡፡ለውጥ ግልፅ የሆነ ፈቃደኝነትን ይፈልጋል፡፡ለውጥን ሳንፀባርቅ ሁል ግዜ ህልውናህ በህይወቴ ዙሪያ ይሰማኛል፡፡ዛሬ ያለሁበት ስፍራ ያደረስከኝ አንተ ነህ፡፡ወትልቅም ሆነ ትናንሽ ለውጦች ስለመሩኝ እጆችህ አመሰግንሀለሁ፡፡__________________________________________________

________________________________________________________________

## ክፍል 5

***መግቢያ፡*** *አሁን ግዜው ሃገሪቱን የመልቀቂያ ነው፡፡እስራኤላውያን እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡የለመዱትን ነገር ሁሉ ጥለው እየሄዱ ነው፡፡ሀሳባቸውን ከመለወጣቸው በፊት ደህና ሁኑ ብሎ መሰናበት ያስፈልጋል፡፡"እግዚአብሄር ለአብርሐም የገባለት ተስፋ እና የእኛ በረከት"*

በሚለው ክፍል ውስጥም ከእንደ እነዚህ አይነት ሀሳቦች ጋር ስንታገል ነበር፡፡አብርሐም እግዘዚብሄር ገና ሊያሳየው ወዳለው ምድር ነው የተጠራው፡፡እግዚአብሄር በዘፍጥረት 15፡13-14 ላይ ዘሩ ከሌላ ምድር እደሚጠራ ነግሮታል፡፡ነገር ግን እግዚአብሄር ልክ ለአብርሐም ፣ለይስሃቅ ፣ለያዕቆብ ቃል እንደገባላቸው ሙሴንም ህዝቡን ከግብፅ መርቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲያወጣ አብሮት ሆኗል፡፡ እስራኤላውያን ህይወታቸው በግብፅ የሚያውቁትን ህይወት እንደሚመስል ነው የተረዱት ፡፡ነገር ግን እግዚብሄር ለአብርሐም እና ለዘሩ በተስፋ ቃል የሰጣቸው የራሳቸው ምድር ያላቸው ህዝቦች እንደሆኑ አያውቁም፡፡እግዚአብሄር ግን ታማኝ ሆኖ ተስፋውን ፈፀመ፡፡

**ትግበራ፡**

1. ህይወታችሁ የተጨቆነ እንደሆነ ታስባላችሁ? ህይወት እሱ ብቻ መስሏችሁ ደምድማችሁ ተቀምጣችኋል? ወይንስ እግዚብሄር ነፃነት ፣መልካም አጋጣሚዎች፣እረፍት ፣ሰላም የተሞላበት አዲስ ስፍራ አዘጋጅቶ ወደዛ እየጠራችሁ እንደሆነ ታስባላችሁ? የእናንተ የተስፋ ምድር ምን ይሆን?________________________

   ______________________________________________________________________

2. ዛሬም እግዚአብሄር እናንተን ከማንኛውም ባሪያ አድርጎ ከገዛችሁ ፣እንዳትንቀሳቀሱ ካደረጋችሁ ነገር ነፃ ሊያወጣችሁ ይፈልጋል፡፡እስቲ ነፃ መውጣት የምትፈልጉበት ነገር ምንድነው ?ወደተስፋይቱ ምድር እንዳትመለከቱ ያደረጋችሁ ነገር ምንድነው ?እግዚአብሄርን ልትጠይቁት የምትፈልጉት ነገር ምንድነው? ምናልባት በክፉ ልምምድ ወይንም ደግሞ የተላያዩ ሱሶች ባሪያ አድርገው ገዝተዋችሁ ይሆናል፡፡ምናልባት ግንኙነታችሁ ፣ዝንባሌያችሁ ባሪያ አድርጓችሁ ይሆን?እግዚአብሄር በሰጣችሁ በረከት ደስ እንዳትሰኙ ያደረጋችሁ ነፃ መውጣት የምትፈልጉበት ነገር ምን ይሆን?___________

   ______________________________________________________________________

**የምናሰላስለው፡** እግዚአብሄር ወደእሱ እንድንመጣ ይጋብዘናል ይጠራናል፡፡እንደእስራኤላውያን በተለያዩ ነገሮች ባሪዎች ሆነን ወይንም ተጨቁነን ከሆነ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል ኑ! እስቲ ማቴዎስ 11፡28 ለማየት ግዜ ውሰዱ ፍላጎቱ ካላችሁ ቁጥር 29 እና 03 ጨምራችሁ እዮ፡፡ቁጥሮቹ በጣም አጭር ናቸው፡፡በካርዳችሁ ላይ ፃፏቸው እና አሰላስሏቸው፡፡እየሱስ ወደ እሱ እንድንመጣ ይጋብዘናል፡፡ከህይወት ሸክም ሊገላግለን ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ጥሪው ምላሽ ሰጥታችሁ ነግሳችሁ በእረፍት የተሞላ ነፃነታችሁን አግኙ፡፡

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ ወዳንተ እንድመጣ ጠርተህኛል፡፡ፍቅርህን እንድቀበል ጋብዘህኛል፡፡እባክህ በመንፈስህ አስታጥቀኝ፡፡ባሪያ ካደረገኝ ነገር ሁሉ ነፃ ወጥቼ በኃይል አንና በደስታ አንድኖርልህ አድርገኝ፡፡አንተ ጌታዬ ነህ፡፡አንተ አምላኬ ነህ፡፡የወደድከኝ እና የፈጠርከኝ ልጅህ ነኝ፡፡ከህይወት እስራት ስለፈታኸኝ ከተያዝኩበት ባርነት ነፃ ስላወጣኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡___________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

# ክለሳ

# አርነታችን የሆነው

# የእግዚአብሄር ጥሪ

## ክፍል 1

**ክለሳ**

በመጀመሪያዎች  የዘፀአት አስራሁለት ምዕራፎች ውስጥ ብዙ መረጃዎችን ተመልክተናል

1. በዚህ ታሪክ ውስጥ ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን አምስት ገፀ ባህሪያት ግለፁ

   ሀ.______________________________

   ለ.______________________________

   ሐ.______________________________

   መ.______________________________

   ሠ .______________________________

2. በማቅለሚያ ማርከራችሁ በዘፀአት 6፡6-8 ያሉትን እግዚአብሄር ለሙሴ የሰጠውን የተስፋ ቃሎች ምልክት አድርጉባቸው።እነዚህ አስፈላጊ የተስፋ ቃሎች በዚህ ወሳኝ ግዜ ለምንድነው እግዚአብሄር  የሰጠው ?
3. ዘጠኙን መቅሰፍቶች ዘርዝሩ

   ሀ.______________________________

   ለ.______________________________

   ሐ.______________________________

   መ.______________________________

   ሠ.______________________________

   ረ.______________________________

   ሰ.______________________________

   ሸ.______________________________

   ቀ.______________________________

4. እነዚህን ተአምራዊ ምልክቶች እግዚአብሄር አድርጓቸዋል፡፡በዘፀአት 7፡4-5 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር አነዚህን ተአምራቶች የደረገው ግብፃውያን ምን እንዲረዱ ፈልጎ ነው?______________________________________________
5. ከበኩር ጋር በተያያዘ ትርጉም ያለው ምን መረዳት አነኛችሁ?____________________

______________________________________________________________
6. የፋሲካው መብል ምን ነበር?ለምንድነው ይህ መብል ለእስራኤላውያን የመጨረሻው መብል የሆነላቸው?______________________________________________

______________________________________________________________

***ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ጥሪ የሚለው ትምህርት መዝጊያ*-1 :** *ጥናታችሁን እንድትገፉበት እናበረታታችኋለን፡፡በብዙ እየተማራችሁ ነው፡፡በቀላሉ መፅሐፍ ቅዱስን እየቃኛችሁ ነው፡፡እናንተን ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚያቀራርቧችሁን ታሪኮች አንብባችኋል፡፡በጥናታችሁ ውስጥ እግዚአብሄር ለእናንት በግላችሁ በሚናገራችሁ ቃል ብዙ መፅናናት እያገኛችሁ ነው፡፡እግዚአብሄር ለእናንት ያለውን ፍቅር እና ከእናንተ ጋር ምን ያህል መቀራረብ እንደሚፈልግ እየተማራችሁ ነው፡፡*

***ፀሎት፡*** *ጌታ ሆይ ለአብርሐም ፣ለይስሃቅ፣ለያዕቆብ የገባኸውን ተስፋ በታማኝነት ፈፅመሀል፡፡ህዝብህን ባሪያ ካደረገው ነገር ሁሉ ነፃ አውጥተሀል፡፡ልክ ለእነሱ ታማኝ እንደሆንክ ለእኔም ታማኝ ነህ፡፡በህይወቴ ውስጥ በሰዎች ወይንም በሁኔታዎች እንደተጨቆንኩ ሲሰማኝ አንተ ከእኔ ጋር እንዳለህ አስባለሁ፡፡አንተ ከእኔ ጋር ነህ ፣ታስታጥቀኛለህ፡፡ለየእለቱ የሚበቃኝን ኃይል ታስታጥቀኛለህ፡፡ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥተህ አዲስ ህይወትን ስለሰጠኸኝ አመሰግናለሁ፡፡*________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________